# የኤፌሶን ቤተክርስትያን ዘመን

ጌታ ይባርካችሁ።

ታርጋ ቁጥር WX-2129፡ ዶጅ—መኪና፡ በመንገድ ማዶ ያቆመ ሰው ካለ፡ አዲስ ዶጅ መኪና የሚነዳ ሰው አለ? የፊት መብራት፡ ሌሎችም መብራቶች ሁሉ፡ በርተዋል። ስለዚህ፡ ባለ መኪናው እዚህ ካለ፡ ሾልከህ ውጣና መብራቶቹን አጥፋ። በመንገድ ሰምንት፡ በሰተ-ግራ በኩል ቆሟል። የኒው አልባኒ ታርጋ ይመስለኛል፡ WX-2129። ቀይ ዶጅ፡ አዲስ ዶጅ፡ ቢያንስ የ59፡ የ60፡ ወይም መቼም ከዚያ አያልፍም። እንደው ከዚህም ይሁን... ከሌላ ሰፍራ እንዲህ አይነቱን ያለው ይኖራል ብዬ አልገመትኩም ነበር። እሺ፡ ልዩ ነው። በጣም መልካም ነገር ነው። እንግዲህ፡ የረሱት ሴቶች ናቸው ለማለት አልፈልግም፡ እኔም እረሳለሁና።

2 እንደው፡ ዛሬም እንደገና ወደዚህ ጉባኤ መምጣታችን፡ እና በቃሉ ዙርያ በአንድነት ሕብረት ማድረጋችን በእውነት መልካም ነው። እየተባረካችሁ ነው? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] ኦህ፡ እውነት ነው፡ አሰደናቂ፡ አሰደናቂ ጊዜ እያሳለፍን ነው። አሁንም እንድንቀጥል እግዚአብሔር እንደሚረዳን እናምናለን።

3 ወንድሜ ሄደ፡ ጥቁር ሰሌዳ ይዞ ወደዚህ መጥቷል፡ ይሁን እንጂ—በጣም አጭር ነው፡ በቂ ከፍታ የለውም። ስለዚህ ለነገ፡ እንደው፡ ለማሰተካከል እሞክራለሁ፡ ወደላይ በማንጠልጠል እናሰተካክለዋለን... ለማብራራት የምፈልጋቸውን አንዳንድ የተለያዩ ነገሮችን መሳል እፈልጋለሁ፡ ስለዚህ እናንተም... በደንብ እንደምትይዙት እርግጠኛ ሁኑ።

4 መቼ ነበር... ትናንት ማታ ይሁን፡ ትናንት መሰለኝ፡ ትንሿ ልጄ፡ ሳራ፡ የሚያስቅ ነገር አደረገች። እኔ እና እናትየው ትንሽዬ ወረቀትዋን እያየንባት ነበር፡ እና የትምህርቴን ማሰታዎሻዎች ጽፋበታለች። ኢሳያስ እና ማቴዎስ፡ እና እያንዳንዷን ነገር በትክክል ጽፋ ይዛለች። ልክ መጨረሻው ላይ—ወረቀቱ ላይ፡ እንዲህ ጽፋለች “ሞትም—ቢሆን... መቃብርም ሊይዘው አልቻለም፡ ሞትም መውጊያውን አንዴ ወርውሯል።” ገና ሰባት አመትዋ ናት። “ሬቨለሽን” ለማለትም፡ “የሪቮሉሽን መጽሐፍ፡” ብላዋለች። መቼም፡ ይህ የሚያሳየው፡ እንደው የሆነ ነገር ለማግኘት የመሞከር ፍላጎት እንዳላቸው ነው፡ አይደል? የወንድም ኮሊንስ ትንሿ ልጅ፡ ከኋላ ቁጭ ብላለች፡ አብረው (“ሪቮሉሽን”?) ብለው የጻፉ ይመስለኛል፡ ወንድም ኔቪል “ዴይ ኦፍ ሪቮሉሽንስ፡” አለ። ከሷ ጋር እየተሰማማበት ነው። እኛም መሰማማት እንዳለብን እገምታለሁ።

5 አቤት፡ ጌታ እየባረከን ነውና። እንደው፡ ጥሩ ጊዜ እያሳለፍን ነው። ጠዋት ልጆች ትምህርት ቤት አድርሼ፡ ክፍል ውሰጥ፡ እያጠናሁ ቆየሁ፡ እና ጥሩ ጊዜ አሳልፌ፡ ቅርብ ጊዜ ላይ ወጣሁ። ትናንት ማታም፡ ጥናት ላይ አምሸቼ፡ ነበር።

6 ከጠዋቱ ሁለት-ተኩል ገደማ ሰዎች ከወደ ሰሜን መጡና፡ ሞት አፋፍ ላይ ላለች... ህጻን ልጅ እንድጸልይላት ጠየቁ። ጌታም ደህና እንደሚያደርጋት እርግጠኛ ነኝ። ለትንሿ ልጅ እንዲጸለይላት፡ ጥያቄ ለመጠየቅ ከቤድፎርድ፡

ኢንዲያና እዚህ ድረስ ወረዱ። ሁለቱ ሰዎች ትናንት ማታ ጉባኤ ውስጥ ነበሩ፡ እና ይህ ርቀት ሁሉ ነድተው ተመለሱ፡ እንደገናም ወደ ኋላ መጡ፡ እንደገናም ተመልሰው ሄደዋል። ምናልባትም ሌሊቱን በሙሉ እየነዱ ይሆናል። እና ስለዚህ፡ ሰዎች እንደዚህ አይነት እምነት እንዳላቸው እና እግዚአብሔርን እንደሚያምኑ ማወቁ መልካም ነው።

7 አቤት፡ ይህ እኛ የምንኖርበት ዘመን ታላቅ ነው። አሁንም በእነዚህ የቤተክርስቲያን ዘመናት፡ የበለጠ እና የተሻለ ነገር፡ ለማግኘት እየጠበቅን ነው።

8 ስለዚህ በጊዜ ለመጨረስ፡ በእያንዳንዱ ምሽት ቀደም ብለን ለመጀመር እየሞከርን ነው። አይሻላችሁም? ይህ ደግሞ ሥራ ያለባቸው ሰዎች፡ ወደ ሥራ እንዲሄዱ ወደ ቤት እንዲመለሱ ያስችላቸዋል። ትናንት ማታ ስንወጣ፡ ወይም እኔ ስጨርስ፡ ዘጠኝ ከአምስት ወይም ከአስር ሆኖ ነበር። እናም ዛሬ ማታ ከእኛ ጋር ለመገኘት ስለጎበኙን አገልጋዮች ደስተኞች ነን። እና—እነ... ውንድም ጁኒየር ጃክሰን፡ ወንድም ካርፔንተር፡ እዚያ ካለው ቤተ ክርስትያን የመጣኸው ወንድማችን፡ እና እዚህ መድረክ ያላችሁ እና በጉባኤው ለተቀመጣችሁ ሁላችሁ።

9 ሌላው ዛሬ እንደተነገረኝ በሚሽን መስኮች ከእኔ ጋር የነበረ አንድ በጣም ውድ ጓደኛዬ፡ ወንድም እና እህት አንድሩ ከሩቅ ምድር ከቻይና፡ ትናንት ማታ በዚህ ጉባኤ እንደነበሩ ሰምቻለሁ። ባለፈው አመት ጃማይካ ላይ እንዴት ያለ ልዩ ጊዜ አብረን አሳልፈናል። ጥሩ ጊዜ አሳልፈናል፡ ቤታቸው ድረስ ሄጃለሁ። እንደው ይገርማል፡ ምናልባት... ወንድም እና እህት አንድሩ ዛሬ ማታ እዚህ በስብሰባው ላይ—ይኖሩ ይሆን? እንደው ይህ ሕንፃም በትክክል አልተሠራም፡ እና... አዎ፡ ከኋላ መጨረሻ ላይ ቁጭ ብለዋል። ወንድም እና እህት አንድሩ፡ እባካችሁ ለአፍታ ያህል፡ ተነስታችሁ መቆም ከቻላችሁ በእግራችሁ ቁሙልን። ጌታ ይባርካችሁ። ወንድም እና እህት አንድሩ፡ እናንተን በማየታችን በጣም ደስ ብሎናል። እምና እዚያ በነበርኩ ጊዜ እንዲመጡ ጋብዣቸው ነበር።

10 አሁን፡ በፊታቸው አልናገረው (ብዙ ልናገር ነበርና፡ አሁን ግን ዝም ልበል)፡ እኔ ግን እውነተኛ ሚሽነሪ የምላቸው እነሱን ነው። ነገ ማታ ከመጡ፡ ከመግባታችን በፊት እዚህ እንዲናገሩ ሰጧቸው። የመስክ ሚሽን ምን ማለት እንደሆነ እንድትሰሙ እፈልጋችኋለሁ፡ ምንም እስከማይመስላቸው ድረስ ወደ ውስጥ ዘልቀው በመግባት... እንግዲህ፡ እነሱ... እንደሚመስለኝ ለብዙ ዓመታት እና ለዓመታትና ዓመታት ኖረውበታል፡ ለብዙ ዓመታት እና ለዓመታት፡ መኪና ወይም ባቡር፡ ወይም ሌላ ነገር አይተው እስከማያውቁ ድረስ ይመስለኛል። እና እህታችን ዳቦ ስትጋግር እንዴት እንደምትሰራ... እንዴት እንደምትደበድበው። እና... ትክክለኛ ሚሽነሪነት ማለት፡ ይህ ነው። ወንድም አንድሩ ዶክተር ነበር፡ መርፌ እና ክር ይይዛል ሲቀደዱ በደንብ ይሰፋቸዋል። እና ልጅ ሲመጣ... ልጆች ሲደርሱ፡ እህት አንድሩ አዋላጅ ወንድም እንድርያስም ዶክተር ናቸው። ሌሎቹ ጥገኞቻቸው ናቸው።

11 ከዚያ በኋላ... የሚሽኑ ስራ ከኢንግላንድ፡ የእንግላንድ የጴንጤቆስጤ ሚሽኖች፡ "ወደ መስክ ለመውጣት ዕድሜ ገፍታችኋል" ባሏቸው ጊዜ፡ (ምን ያህል ሚሲዮናውያን እንደሆኑ እነግራችኋለሁ፡ በቀላሉ ወንበር ይዘው አልተቀመጡም) በራሳቸው መንገድ ለመንቀሳቀስ ተመለሱ፡ ወደ ጃማይካ

ተመልሰው የሚሽነሪ-ስራ እየሰሩ ይገኛሉ። እኔና ወንድም ፍሬድ ሶትማን ወደ ቤታቸው በመሄድ ቤታቸውን ለመጎብኘት ዕድል አግኝተናል፡ አቤት አንድ ሰው ሊያደርገው የሚችለውን፡ እንዴት ያለ—ክርስትያናዊ ጊዜ አሳይተውናል። እላችኋለሁ፡ ይህን ዝም ብዬ አልናገርም... ካለፉ በኋላ የአበባ ጉንጉን ከማስቀመጥ ይልቅ፡ አሁን እንቡጥ አበባ ብሰጣቸው ይሻላል። እውነት እላችኋለሁ፡ የእውነት ክርስቲያኖች ናቸው። እናም እህት አንድሩ ሰው ሊያገኛቸው ከሚችላቸው በጣም መልካም፡ እና ደግ ክርስቲያን ሴቶች አንዷ እንደሆነች ለባለቤቴ ነገርኳት። እንደው እሷ... ባህሪዋ የክርስቶስ ሆኗል፡ ወንድም አንድሪውም፡ እንዲሁ ነው። ስለዚህ፡ አሁን ቆመው የነበሩትን ሁላችሁ አይታችኋቸዋል ብዬ አስባለሁ፡ እና ቤተ ክርስትያን ሁሉ እጃቸውን እንድትጨብጧቸው ከመሄዳቸው በፊትም እንድትስሟቸው እፈልጋለሁ።

12 አሁን፡ ነገ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ እንደው፡ ነገ... ምሽት ሁለተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን እንጀምራለን። ዛሬ ማታ የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ዘመን እንጀምራለን። ጌታ ለእኛ ያዘጋጀው በረከት እንዳለው እርግጠኛ ነኝ።

13 እና አስቀድሜ እንዳልኩት፡ አስታውሱ፡ ሥነ መለኮትን በተመለከተ—አንዳንድ ጊዜ በእነዚህ ነገሮች ላይ ላንስማማባቸው እንችላለን። እና አብዛኛዎቹን ቀናቶቼን ከትክክለኛዎቹ የታሪክ ተመራማሪዎች የወሰድኳቸው፡ በእውነቱ የየትኛውንም ወገንተኝነት ከሌላቸው፡ ምንም ይሁን ምን፡ አብያተ ክርስቲያናት ያደረጉትን፡ እውነታ ብቻ የጻፉ ናቸውና። ሌላው... በርግጥ፡ መለኮታዊ ክፍሉ በተመለከተ፡ እኔ እንደማውቀው፡ የበለጠውን ትርጉም በራሴ ለማስቀመጥ ሞክሬአለሁ። አንዳንድ ጊዜ ትንሽ ጨካኝ ወይም ከባድ ንግግር ብናገር፡ እንደዚያ ለመናገር መፈለጌ አይደለም። እኔን የሚያውቀኝ ሰው ሁሉ፡ እንደዚያ ለመናገር፡ እንደማልፈልግ ያውቃልና። ብቻ ፍላጎቴ... አንድን ነጥብ በደንብ እንዲጠብቅ ከመፈለጌ የተነሣ፡ ልክ... በስሌዳ ውስጥ ሚስማርን እንደመምታት ነው፡ ዝም ብላችሁ ካጣበቃችሁት፡ አይዝላችሁም። በደንብ አጥብቆ መያዝ እንዲችል፡ እስከ ውስጥ እንዲዘልቅ ማድረግ አለባችሁ። እና ይህን ለማድረግ እየሞከርኩ ነው። ስለዚህ ላለመስማማት እሞክራለሁ ማለት አይደለም፡ ምክንያቱም ለሁሉም የሐይማኖት ተቋማት እናገራለሁ፡ ስለዚህ... ያ ማለት አይደለም።

14 ከብቶች ላይ መለዮ ስለ ማድረግ፡ ብዙ ጊዜ ተናግሬአለሁ። ከብዙ ዓመታት በፊት አንድ ቀን በጸደይ ወራት ከብቶች ወደ ግጦሽ ሲወሰዱ... ትዝ ይለኛል፡ ከብቶቹን ወደ ጫካው ሲወስዱ፡ ከብቶቹን እየነዳሁ በመውሰድ አግዛቸው ነበር፡ የሄሬፎርድ ማህበር የሚያስማራበት ሰፊ አጥር—ትሮብልሳም ሸለቆ በሚባለው ወንዝ ነበር። እና እግሬን በኮርቻው ቀንድ ላይ አንጠልጥዬ እዚያ ተቀምጬ፡ ከብቶቹ አጥር አልፈው ሲገቡ የግጦሹ አለቃ ሲመለከታቸው እመለከተው ነበር።

15 እንግዲህ፡ ከብቶችን ወደ ግጦሽ ለማስማራት... ማለት የመንግስት ይዞታ ለመጠቀም፡ አንድን ከብት ከማስማራታችሁ በፊት አንድ ቶን ሳር ማከማቸት ይጠበቅባችኋል። እና እያንዳንዱ እርባታ ብዙ ሳር ያከማቻል፡ ይህም ብዙ ከብቶች፡ እንዲመገቡት ነው።

16 አሁን፡ ሁሉንም ዓይነት መለዮዎች በላያቸው ላይ አንግበው በዚያ በኩል እያለፉ ነበር። አንዳንዶቹ “ባር X” ይባላሉ። ከአጠገባችን የሚሰተር ግሪምስ “ዳይመንድ T፡” በዳይመንዱ ጫፍ ላይ T ነበረበት። በዚያ በትርብልሳም ወንዝ “ሌዚ K፡” እንዲሁ ነበር። የእኛም ድግሞ “ተርኪ ትራክ” ነበር። ከኛ በታች “ትሪፖድ” ነበር። እና በዚያ በር በኩል ሁሉም ዓይነት መለዮ ያላቸው ያልፉ ነበር።

17 እና የግጦሹ አለቃ ስለ መለዮአቸው ያን ያህል አትኩሮት አያደርግባቸውም፡ ፈጽሞም አይቷቸው አያውቅም። እንደውም አንዳንዴ በከብቱ በግራ በኩል ስለሚደረግ፡ መለዮውን ሊያየው አይችልም። ስለዚህ—መለዮውን አያየውም ነበር። አንድ ነገር ግን እርግጠኛ ነበር፡ በጆሮዋ ላይ የደም ታግ ካላት ላም በስተቀር፡ ወደዚያ ማለፍ አትችልም። ንጹሕ ሄሬፎርድ ካልሆነ በስተቀር በዚያ ጫካ ላይ ማለፍ አይቻልም። የምርት መለዮው ብዙ ለውጥ አያመጣም፡ ዋናው ነገር ግን የደም ታጉ ነበር። እና በፍርዱ ጊዜ ላይም ይህ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። የምንለብሰው የትኛውን መለዮ ለውጥ አይኖረውም፡ የደም ታጉን ግን ይፈልገዋል፡ “ደሙን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።”

(እኔ ይሆን ጂን፡ አሁን፡ የሆነ ነገር፡ አጥፍቻለሁ? ) [ወንድም ጂን ጎድ “**ይህ** ማይክራፎን ያስተጋባል፡” አለ።—አርታዒ።] (ያስተጋባል። እሺ... በሁለቱ መካከል የሚፈጠር ሽግግር ነው፡ ልክ ነው አይደል? ) [“**ይሄኛው** ጥሩ ነው እና **ያኛው** በጣም ጥሩ አይደለም።”] (እሺ። አመሰግናለሁ ወንድም ጂን። እሺ።)

18 አሁን ነገ ማታ ተመልሰን እንድንመጣ እነዚህን ዘመናትም መረዳት እንድንችል፡ ዛሬ ምሽትም ቶሎ መውጣት አለብን። እና እላችኋለሁ፡ በመንገድ ዳር የወዳደቁትን አንዳንዶቹን ታላላቅ ነገሮችን በአንድ ጀምበር ላለማውጣት መሞከር፡ ለእኔ እጅግ ከባድ ነገር ነው። ታውቃላችሁ፡ ይህ የኔ ተፈጥሮ ነው፡ ይሁን እንጂ ለእያንዳንዱ ምሽት በጥቂቱ ማስቀረት አለብን።

19 አሁን፡ ታላቁን መጽሐፍ መክፈት ከመጀመራችን በፊት፡ ለአፍታ ብቻ መቆም ከቻልን እጠይቃለሁ... የምትችሉ ሁላችሁ... አሁን ስንነሣ፡ አቅጣጫችሁን ቀይሩ። እና አሁን ለጸሎት ቃል፡ በትህትና፡ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ፡

20 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ እምነታችን ሳይናወጥ፡ ወደ ታላቁ ቅዱስ ዙፋንህ እንደገና እንቀርባለን፡ የመጣንበት ምክንያትም እንድንመጣ ስለተገደድን ነው። በአንድ ቤተ ክርስቲያን ሰም ወይም ቤተ እምነት፡ ወይም በዚህች ቤተ ክርስቲያን ወይም በራሳችን ሰም፡ መጣን ማለት አንችልም፡ ምክንያቱ በእግዚአብሔር ዘንድ መሰማትን እናገኛለን ብለን ለማሰብ፡ በዚያ እርግጠኞች አልነበርንም። ኢየሱስ ሲነግረን ግን፡ “አብን በሰሜ ማንኛውንም ነገር ለምኑት፡ እኔ አደርገዋለሁ ብሎናል፡” በኢየሱስ ሰም እንደመጣን እናውቃለንና፡ አንተም አባት ሆይ፡ ትሰማናለህ።

21 ባለፉት ዘመናት ስለነበሩ ሰማዕት በመሰማታችን ተባርከናል፡ እነርሱ በገዛ ደማቸው ምስክርነታቸውን እንዳተሙ ነው፡ ይህም፡ አባት ሆይ፡ በዚህ ዘመን በጣም ትንሽ ነገር እንደሰራን እንዲሰማን ያደርገናል። ጌታ ሆይ፡ አቤቱ በሰራህ ጉዳይ ላይ፡ ስለቸልተኛነታችን—እንዲህም—ስለመሆናችን፡ ይቅር እንድትለን፡

እለምንሃለሁ። አሁንም ይህን የአንተው ቃል ሰናነበው እንደገና እንድትቀባን እጸልያለሁ፡ የተቤዠሃትን ታላቋ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ለመመሥረት ባለፋት ዘመናት የተከሰተውን መከራ ማየት እንድንችል እርዳን።

22 የሰማይ አባት ሆይ፡ ምን እንደምንል ስለማናውቅ፡ በእኛ እንድትናገር እለምንሃለሁ፡ በእግዚአብሔር ፊት በቤተክርስቲያኑ ተገኝተናልና ይህን ጸሎት በፊቱ በማቅረብ እንጠባበቃለን፡ በእነዚህ ሰዎች ላይ ያለው መንፈስ ቅዱስ ኃይሉን ዛሬ ማታ አንድ ላይ እንዲያደርግ እና ወንጌልን በሰው ሁሉ ልብ ውስጥ እንዲጠቀጥቅ እንጠይቃለን፡ ይህም ለመጪው ዘመን አዲስ አቋም እና አዲስ ተሰፋ ይሰጠናል። ጌታ ሆይ፡ በለሲቱ ስታቆጠቁጥ፡ እስራኤልም አገር ስትሆን፡ የአሕዛብ ዘመን እልቆ እየተቆጠረ መሆኑን ተረድተን፡ የታላቁን አዳኝ፡ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት እየጠበቅን ነውና ይህን ሰጠን።

23 ጌታ ሆይ፡ በመካከላችን ተመላለስ። ዛሬ ምሽት እንደተባለው፡ "በመቅረዙ መካከልም እንደምትመላለሰው፡" ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ በመካከላችን ተመላለስ። በፊታችን ካለው ክፉ ነገር ልባችንን አሰጠንቅቀህ፡ የቃልህም ግንዛቤ ሰጠን፡ በኢየሱስ ሰም፡ እንጠይቃለንና። ኣሜን። መቀመጥ ትችላላችሁ።

24 አሁን፡ በእያንዳንዱ ቀን እንደተናገርኩት፡ እያየን ያለነው ታሪካዊ ክስተት ስለሆነ በተቻለኝ መጠን፡ ጊዜዎች፡ ቦታዎች፡ እና የመሳሰሉትን ነገሮች ሁሉ፡ በወረቀት ላይ ለማሰፈር ሞክሬአለሁ። ታሪክ ነበረ፡ አሁን ወደ ታች በወረድን ቁጥር፡ አሁንም፡ ከጊዜው ጋር እየሰፋነው ነው።

25 አሁን፡ እሁድ ጥዋት እና እሁድ ከሰአት... ማለቴ፡ እሁድ ምሽት፡ አሰደሳች ጊዜ አሳልፈናል። ጥሩ ጊዜ እንደነበረን እርግጠኛ ነኝ። ለእኔ፡ ጥሩ ጊዜ አሳልፌአለሁ። የመገለጡ ነገር...

26 አሁን፡ ምን እያጠናን ነው? የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ። እግዚአብሔር እርሱ ማን እንደሆነ በገለጠው እና ባሳየው ነገር ምን አገኘን? በመጀመሪያ የምናገኘው፡ ከመገለጦች ሁሉ፡ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ማንነቱን ማሳወቁ ነው። ያም ደግሞ፡ ኢየሱስ የሥላሴ ሦስተኛ አካል ሳይሆን፡ እርሱ ራሱ በሙላት ሥላሴ መሆኑን ነው። እሱ ራሱ አባት፡ ልጅ እና መንፈስ ቅዱስ ነበር። መገለጡም ያ ነበረ። በዚያው ምዕራፍ ውስጥ፡ እርሱ ራሱ ሁሉን ቻይ አምላክ እንደሆነ፡ አራት ጊዜ ተናግሯል፡ የነበረው፣ ያለው፣ የሚመጣውም፣ የዳዊት ሥርና ዘር።

27 አሁን ግን፡ በእነዚህ ነገሮች ውስጥ፡ ጉዳዩን በሙሉ ለማጣራት እንሞክራለን፡ በድጋሚ መቼ እንደምንሰማው አላውቅም፡ ምናልባት ምንም ጊዜ እስከማይቀር ድረስ፡ ወደ ዘላለም እስክንሻገር ድረስ በጭራሽ ላንሰማውም እንችላለንና። እና አሁን፡ እኔ እንደምለው፡ ከእኔ ይልቅ ይህን ለመናገር ብቁ የሆኑ ብዙ ወንድሞች፡ አስተማሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡ ምናልባትም የተሻለ ትርጓሜ ሊያገኙለት ይችላሉ፡ እግዚአብሔር ግን ይህን እንዳደርግ በልቤ ላይ አስቀምጦታል ስለዚህ ትክክል እንደሆነ ያየሁትን በትክክል ካልተናገርኩት ግብዝ እሆናለሁ። አያችሁ? ስለዚህ፡ በ—እግዚአብሔር ፊት ሁሉ ጊዜ፡ ሁሌም ቢሆን፡ ጳውሎስ "ቸል አልልም" በማለት እንደተናገረ፡ እኔም ግልጽ መሆን እፈልጋለሁ፡ "ቤተ ክርስቲያን እንድትጸና፡ ቀንና ሌሊት፡ በእንባ

አስጠንቅቃችሁ ዘንድ አልታክትም።" የሚጠፋ ሰው ካለ፡ ደሙ በእጄ ላይ አይሁን፡ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ከሰው ሁሉ ደም ንጹህ መሆን እፈልጋለሁ። ካልተስማማችሁ፡ እንደው፡ በቃ፡ በጥሩ ወዳጅነት ቢሆን፡ መልካም ነው። አሁን፡ ግን፡ ምናልባት ጌታ ሁላችንንም የሚረዳን፡ አንድ ነገር ይገልጥልናል።

28 አሁን፡ የመጀመሪያው ነገር፡ ራሱን እንደገለጠ እናያለን። አሁን ማን እንደነበረ ተረድተናል።

29 አሁን፡ ሰንቀጥል፡ መርጨትን በተመለከተ፡ እና "በአብ፡ በወልድና፡ በመንፈስ ቅዱስ" ሰም መጠመቅ የሚለውን ጥቅስ ሳቀርብ የካቶሊክ ጥምቀት እንጂ የፕሮቴስታንት ወይም የአዲስ ኪዳን ጥምቀት አለመሆኑን፡ ያንን ግልጽ እንዳደረግሁ ተሰፋ አደርጋለሁ። አሁንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠመቁ ሰዎች የተጠመቁበትን የቃሉ ጥቅስ ማሳየት የሚችል ሰው ካለ እጠይቃለሁ ወይም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን እስከ መሠረቱበት የሎዶቅያ ጉባኤ ድረስ፡ "በአብ፡ በወልድና፡ መንፈስ ቅዱስ፡" ሰም የተጠመቀ አንድ ሰው ካለ እባክህ ናና አሳየኝ። ጀርባዬ ላይ፡ "ሐሰተኛ ነቢይ፡" የሚል ጽፌ ወደ መንገድ እወጣለሁ። አሁን፡ ይህን ያልኩት... ለመክበድ ፈልጌ አይደለም፡ ነገር ግን እውነት እንደሆነ ለማሳየት ነው። አያችሁ?

30 እንግዲህ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ እርሱ በመካከላችን ሥጋ የሆነ ሁሉን ቻይ አምላክ እንደሆነ፡ እዚህ ጋር ይገልጠዋል። አያችሁ? አብ፡ ወልድና፡ መንፈስ ቅዱስ ሦስት አማልክቶች አይደለም፡ ወይም በሦስት ቦታ የተቆራረጠ አንድ አምላክ፡ አይደለም። በሦስት አገልግሎት ውስጥ የሠራ አንድ አምላክ ነው፡ አብነት፣ ልጅነት፣ እና መንፈስ ቅዱስ። እግዚአብሔር መንገዱን ወደ ሰው ልብ ይመልስ ዘንድ፡ ዳግመኛም ከእርሱ ጋር ሆነን፡ የእግዚአብሔር ወንድና ሴት ልጆች እንሆን ዘንድ ከኤደን ገነት ወረደ። ያም እግዚአብሔር ከእኛ በላይ፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር፣ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ነው። ልዩነቱ ይህ ነው። አያችሁ?

31 እና አሁን እነዚያን ነገሮች፡ መጽሐፍ ቅዱስ ያንን በራእይ 1ኛው ምዕራፍ ላይ ገልጦ በደንብ ተናግሯል፡ ይህም መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ በአዲስ ኪዳን፡ ሙሉው የአዲስ ኪዳን ቀኖና የሆነ ብቸኛው መጽሐፍ ነው፡ ኢየሱስ የራሱን ማኅተም ያሳረፈበት ብቸኛው መጽሐፍ ነው። እርሱም ከሁሉ በፊት፡ እንዲህ አለ፡ "የሚያነበው እና የሚሰማውም እርሱ ብጹዕ ነው።" በስተመጨረሻም፡ እንዲህ አለ፡ "ማንም ከእርሱ አንዳች ቢያጎድል ወይም አንዳች ቢጨምርበት፡ ዕጣ ፈንታው፡ ከሕይወት መጽሐፍ ውስጥ፡ ይወሰድበታል።" ስለዚህ ለማንም ሰው ማንኛውንም ነገር ማጉደሉ እርግማን ነው፡ ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ መገለጥ ነውና። ስለዚህ እሱን ሶስት ካደረግነው፡ ምን እንደሚፈጠር ታውቃላችሁ። አያችሁ፡ ሰማችሁ ይወገዳል።

32 የትኛውም፡ ከፕሮቴስታንት ይሁን፡ ከቀድሞ ቤተ ክርስቲያን በሦስት አማልክት ያመነ አልነበረም። በኒቂያ ካውንስል፡ ሁለቱም በየፊናቸው የሄዱበት፡ **በዚህም** መንገድ የወጡበት እንደ ማለት፡ ትልቅ ጉዳይ ነበር። **ሥላሴአውያን**፡ በሥላሴ ውስጥ በሦስታዊነት ያመኑ ሰዎች፡ በመጨረሻም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተመሠረቱ፡ እግዚአብሔርን "ሦስት" ሰዎች በማድረግ፡ ወደ ፍጹም ሥላሴ ሄዱ። እንዲሁም ሌላኛው ደግሞ እግዚአብሔር "አንድ"

በማለት የሚያምን ነበረ፡ እነዚያም ደግሞ **አሃዳዊ** ለመሆን ወደ ሌላ ጥግ ሄዱ። ሁለቱም ተሳስተዋል። እግዚአብሔር እንዲህ አይደለም...

33 ኢየሱስ ራሱ የራሱ አባት ሊሆን አይችልምና፡ ኢየሱስም አባት ራሱ ሆኖ አባት ሊኖረው አይችልምና... ሦስት አማልክት ይኖራሉ። ይህ—ሊሰራ አይችልም። አባት ካለው፡ ያ አባት ከጎኑ የሚኖር ሌላ ሰው ከሆነ፡ መንፈስ ቅዱስም ሊብቻው ሌላ ከሆነ፡ እንግዲያውስ ሕገ ወጥ ልጅ ይሆናል... ሌላም አባት ይኖረዋልና። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ አባቱ እንደሆነ ይናገራልና። ስለዚህ እኛ መንፈስ ቅዱስ ያለን ከሆንን፡ እንግዲያውስ መንፈስ ቅዱስ አይደለም፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰም አገልግሎቱን፡ በእኛ ውስጥ የሚፈጽመው አብ ነው፡ ምክንያቱም ድሮ መንፈስ በሚባል ሰው ነበረና፡ አሁን ግን ያው ጆሆቫ አምላክ፡ ተመልሶ በመምጣት በእኛ ውስጥ አድሯል። አያችሁ?

34 ሦስት አማልክት የለም። ሦስት አማልክቶች ወደዚህ ተጎትቶ የገባ፡ አረማዊ እና አረማውያን ነው። በሳምንቱ ውስጥ ለመቆየት የምትፈቅዱ ከሆናችሁ፡ ጭፍን ጥላቻ አይኑራችሁ፡ ነገር ግን ተከታተሉ፡ ታሪኩን ውሰዱ። ከእኔም ይሁን ከሌላ ይህን ታሪክ፡ ወይም ከሌላው ታሪኩን አጥኑት። የታሪክ ምሁራን ሁሉ፡ በአንድነት እንደሚስማሙበት እወቁ። የታሪክ ተመራማሪዎች፡ ምን እንደተፈጠረ እውነታዎችን ለመናገር ከመፈለግ በቀር፡ ከየትኛውም ወገን ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም። እና ያ ነገር በሉተር በኩል እንዴት ሾልኮ እንደገባ እና ወደ ዌስሊ በየት በኩል እንደመጣ፡ "በአብ፡ በወልድና፡ መንፈስ ቅዱስ" ሰም ጥምቀት፡ በመጨረሻ ዘመን እንዴት እንደተጋለጠ ተከታተሉ። ወደ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከየት እንደገባ፡ በጨለማው ዘመን፡ በሉተር በኩል ሲወጣ፡ እስከ ዌስሊ ድረስ እንዴት እንደደረሰ፡ ነገር ግን በዌስሊ እና በሎዶቅያ መካከል (በመጨረሻ) እንደተጋለጠ ተመልከቱ። ትክክል ነው። እንግዲህ፡ ይህ ሁሉ ታሪክ ነው፡ ታሪክ ብቻም አይደለም፡ መጽሐፍ ቅዱስም ነው።

35 ስለዚህ አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ ስለ ሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት እንጀምራለን ይህ መጽሐፍ በተፃፈ ጊዜ በትንሿ እስያ የነበሩት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። በዛን ጊዜ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ሊመጡ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ዘመናት የሚያሳይ ገጸ ባህሪያት የነበራቸው ናቸው፡ ምክንያቱም... በዚያን ጊዜ እንደነቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን የመሳሰሉ፡ ከዚያም ይልቅ ሌሎች ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ፡ እግዚአብሔር ግን እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት የመረጣቸው በገጸ ባህሪያቸው ነው።

36 አሁን፡ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል ቆሞ፡ ሰባት ከዋክብትን በእጁ ይዞ እናገኘዋለን። ስለ እነዚያም ሰባቱ ከዋክብት፡ በ1ኛው ምዕራፍ በ20ኛው ቁጥር፡ እንዲህ አለ፡ እነዚህም "የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ሰባት መላእክት ናቸው።"

37 እንግዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህን መገለጥ አልተረዱትም ነበር። ምክንያቱም፡ ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት በሺዎች የሚቆጠሩ ዓመታት እንዳሉ ካወቁ ቢመለከቱ እና ቢጠብቁ ምን ይጠቅማቸዋል? አልተሰጣቸውም ነበር።

38 አሁንም እዚህ ላላችሁ ሰዎች፡ ለእናንተ ይህን እላለሁ፡ ለእናንተ የካቶሊክ ሰዎች፡ ለእናንተም ሉተራን፡ ለእናንተም ሜቶዲስቶች፡ ለሌሎቻችሁም እላለሁ፡ ዛሬ በቃሉ ላይ ያለው ብርሃንም፡ ለማርቲን ሉተር አልተሰጠውም ነበር።

ለጆን ዌስሊም አልተሰጠም። ጆን ዌስሊ ከሉተር የቀረውን ቅድስናን ሰበከ። ብርሃኑም ብርሃን በሚያስፈልገን ጊዜ መጣ። እግዚአብሔር ተናገረው፡ እግዚአብሔርም ሊገልጥ እስከሚችልበት ቀን ድረስ በዓይኖቻችን ተሰውሮአልና አልተከፈተልንም። ከሄድን በኋላ ምን ይሆናል ብዬ እሰባለሁ? አዎን፡ ምንም የማናውቀው፡ እጅግ በጣም ብዙ ነገር እንዳለ አምናለሁ። እውነት ነው። ሙሉውን የራዕይ መጽሐፍ ብንወስድ፡ በመጽሐፉ ጀርባ የታተሙ፡ ሰባት ማኅተሞች አሉ። በመጽሐፍም ውስጥ የተጻፈ አይደለም... እንደው የለም። እናም እነዚያ ማሕተሞች በዚህ የቤተክርስቲያን ዘመን የሚከፈቱ ናቸው፡ እናም ሰባቱ የመጨረሻዎቹ የእግዚአብሔር ምስጢሮች-... እንዲታወቁ ይደረጋል። ኦህ፡ ሙሉውን ለክረምት አቆይቼ ክረምት ሙሉ ብንማረው ደስ ባለኝ። አዎን፡ ወዳጄ! ሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት።

39 ዳንኤል ሰባቱን ነጎድጓዶች ሰምቶ፡ እንደተከለከለ፡ ዮሐንስም ድምጾቹን ሰማ፡ መጽሐፋም በማሕተም የተዘጋ ነበረ፡ የመጽሐፋም ጀርባ በሰባት ማኅተም ታትሞ ነበር፡ ነገር ግን እነዚህ ማኅተሞች በሚከፈቱበት ዘመን፡ "የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል።" በሌላ አነጋገር፡ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያኑ ይታወቃል፡ ይህም በሦስት ሰዎች ሳይሆን እንደ አንድ ሰው ይታወቃል። "የእግዚአብሔር ምስጢር ይገለጣል፡" ይህም ሙሉ በሙሉ በተገለጠ ጊዜም፡ ሰባቱ ምስጢራት ለቤተክርስቲያን ይከፈታሉ፡ ምክንያቱም፡ በዚያ ውስጥ፡ ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ትኖራለችና፡ እርሱም በእኛ ዘንድ ህያው እንደመሆኑ ምልክቶቹ እያሳየ ወደ ውስጥ እና ወደ ውጭ ይመላለሳል፡ እርሱ በመካከላችን አድሮ፡ በመካከላችን የሚኖረውን ህያው ክርስቶስን እናመልካለን።

40 ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናትን እና ትላልቅ ነገሮችን በጭራሽ አትፈልጉ። ወደ የጴንጤቆስጤ ዘመን በደረስን ጊዜ፡ የት እንደጠፉ በእርግጠኝነት ታያላችሁ። **የሎዶቅያ** ቤተ ክርስቲያን ትርጉም "ምንም የማያስፈልገው፡ ሃብታም፡" አያውቁትም እንጂ፡ ራቁት፡ ምስኪን፡ ዕውር፡ ጎስቋላ ናቸው። አያችሁ? ብዙ ገንዘብ፡ እና ታላላቅ ህንጻዎች፡ እና ሌሎች ነገሮችን ወደ ማሳደድ ጠፉ።

41 ግን'ኮ፡ ቤተክርስትያን—የምድር ሁሉ ማላገጫ ነበረች። በእነዚያም ሁሉ፡ በሰው ሁሉ የተጠሉ፡ የተወገዙ፡ በየጎዳናዎች፡ በየሰፍራው የሚኖሩ ነበሩ። ዕብራውያን 11ን አንብቡት፡ እና የመጨረሻዎቹን ስድስት ወይም ሰምንት ቁጥሮች ውሰድ፡ እንዴት "በምድረ በዳ ተቅበዘበዙ፡ እና—የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፡ ተቸገሩ፡ ተሠቃዩ፡ ተመቱ።" ያኔ የነበሩ ሰዎች፡ በፍርድ ቀን ምስክርነታችን በፊታቸው እንዴት ይቆማል? ተመልከቱ፡ በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች።

42 አሁን፡ በዚህ የቤተክርስቲያን ዘመን... ሰባት አብያተ ክርስቲያናት አሉን፡ አሁን እንዲህ እንዲቀመጥ እፈልጋለሁ። ከዚህ የሚታያችሁ አይመስለኝም፡ በጣም እጠራጠራለሁ፡ ምናልባት ከቻላልችሁ አንድ ሰው እስኪ፡ ሰባቱ የቤተ ክርስትያን ዘመናት ለማሳየት (እዚህ ተቀምጣችሁ፡ እንደማትችሉ አውቀዋለሁ)፡ የተቻለኝን እሞክራለሁ። በደንብ እንድትረዱት በእጄ እንዲህ ልያዘው።

43 የጀመረው፡ የቤተ ክርስትያን ጅማሬ በጴንጤቆስጤ ነው። ይህን የሚቃወም አለ? የለም፡ ወዳጄ! ቤተክርስቲያን በጴንጤቆስጤ የጀመረችው በጴንጤቆስጤ በረከት ነው፡ እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ ተመሳሳይ መልእክት እና በእኛ የሚሰራ ተመሳሳይ በረከት ይዛ እንድትቀጥል በኢየሱስ ክርስቶስ ተሾመች። ይህም ለቤተ ክርስትያን የሰጣት የመጨረሻ አደራ፡ ማርቆስ 16 ነው፡ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፡ ወንጌልንም ሰበኩ፡ ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።" አሁን፡ ወዴት? "ወደ አለም ሁሉ።" ለማን? "ለፍጥረት ሁሉ።" ጥቁር፡ ቡኒ፡ ቢጫ፡ ነጭ፡ የትኛውም ፍጥረት ቢሆን፡ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ሰበክ። "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።" አሁን፡ ዛሬ ማታ ጠርዙ ላይ እየገባን ነው፡ ዛሬ ማታ መከርከም እንጀምራለን፡ ወደ እኛ ቤተ ክርስቲያን ዘመን እስክንወርድ ድረስ በየምሽቱ አንድ ትልቅ ቁራጭ እንቆርጣለን። እንግዲህ፡ አደራው ይህ እንደነበረ አውቀነዋል።

44 እንግዲህ፡ የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ዘመን የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሰምርኔስ ነበር። ሦስተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ጴርጋሞስ ነበር። አራተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ትያጥሮን ነበር። አምስተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሰርዴስ ነበር። ስድስተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ደግሞ ፊላደልፊያ ነው። ሰባተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሎዶቅያ ነው።

45 አሁን፡ የመጀመርያው የቤተክርስቲያን ዘመን የተጀመረው **እ.ኤ.አ.** 53 ላይ፡ ጳውሎስ—በኤፌሶን ቤተክርስቲያንን በመሰረተ ጊዜ ነው። በወንጌል ጉዞው፡ ቤተክርስትያኒቱን በኤፌሶን፡ የኤፌሶን ቤተክርስትያንን መሰረታት፡ በ 66 ዓመተ ምህረት አንገቱ እስኪቆረጥ ድረስ በዚያ ፓስተር ነበር፡ ይህም ሃያ-ሁለት አመታት የኤፌሶን ቤተ ክርስትያን ፓስተር ያደርገዋል። እርሱም ከሞተ በኋላ እንደተባለው ቅዱስ ጳውሎስ... ወይም ቅዱስ ዮሓንስ ዘመለኮት የቤተ ክርስትያኒቱ ፓስተር በመሆን እስከዚህ ዘመን ድረስ አደረሳት፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመንም እስከ 170 ድረስ ይደርሳል።

46 ከዚያም ከኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ **እ.ኤ.አ** ከ53 እስከ **እ.ኤ.አ** 170 በኋላ፡ **እ.ኤ.አ** ከ170 እስከ **እ.ኤ.አ** 312 የጀመረው የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው። በመቀጠል ጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ዘመን በ312 ይጀምራል እስከ **እ.ኤ.አ** 606 ድረስ ይዘልቃል። ከዚያም የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ዘመን በ606 ጀምሮ እስከ ጨለማው ዘመን፡ 1520 ድረስ ነው። ከዚያም የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ከ1520 ጀምሮ እስከ 1750 ድረስ፡ የሉተራን ዘመን ቆየ። ከዚያም ከ 1750 ጀምሮ፡ የገባ ቀጣዩ ዘመን የፊላዴልፊያ፡ የዌስሊ ዘመን ነበር፡ ከ1750 ጀምሮ እስከ 1906 ድረስ። እና የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን በ1906 ጀመረ፡ መቼ እንደሚያበቃ አላውቅም፡ ነገር ግን እ.ኤ.አ በ 1977 ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። ግምቴ ነው፡ ከተወሰኑ ዓመታት በፊት ባሳየኝ ራእይ መሰረት እገምታለሁ እንጂ፡ ጌታ አልተናገረኝም፡ ከእነዚያ ውስጥም (ከሰባቱ ውስጥ) አምስቱ ተፈጽመዋል።

47 ያንን ራዕይ... በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምታስታውሱት፡ ስንቶች ናችሁ? በትክክል። እንደውም፡ ባለፈው ምርጫ ወቅት ኬኔዲ እንዴት እንደሚመረጥ

ተናግሬአለሁ። ሴቶች ምርጫ ላይ እንዴት እንደሚሳተፉ። ሩዝቬልት ዓለምን ወደ ጦርነት እንዴት እንደሚነዳት። ሙሶሎኒ የመጀመሪያ ወረራውን በኢትዮጵያ ላይ እንዴት እንደሚፈጽም፡ እና እንደሚይዛት፡ መጨረሻው እንደሚሆን ከዚያም በኋላ እንደሚሞት። እነዚህ ታላላቅ ርዕዮተ ዓለሞች እንዴት እንደሚነሱ በኮሚኒዝም እጅ እንደሚወድቁ፡ ሂትለርዝም፡ እና ሙሶሎኒ፡ እና ኮ-... ናዚሲዝም፡ እና ሌሎችም፡ ሁሉ በኮሚኒዝም እጅ ይወድቃሉ። እና ከአስራ አንድ አመት በፊት ቀደም ብሎ፡ እንዲህ ተባለ "ከጀርመን ጋር ጦርነት እንጀምራለን፡ ጀርመን በኮንክሪት ምሽግ ትመሽጋለች፡" በማጂኖት ላይን። እንደዚያውም ሆነ። ከዚያም፡ ያንን ከተባለ በኋላ፡ እንዲህ እንደሚሆን... ከዚያም በኋላ ሳይንስ እጅግ እየላቀ በከፍተኛ ደረጃ በመድረስ የሚሰራት መኪና ትኖራለች፡ መኪው ከጊዜ ወደ ጊዜ "የእንቁላል" ቅርጽ ትሆናለች። እናም ራእዩ የተነገረው አሁን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተተከለችበት፡ በኦርጌው... ወላጅ አልባ ልጆች ማሳደጊያው ነበር። ቻርሊ ከርን፡ ምናልባት ዛሬ ማታ በህንፃው ውስጥ ካለ፡ በዚያን ጊዜ እርሱ በቦታው ይኖር ነበር። አንድ እሁድ ጠዋት ወደ ሰባት ሰአት ገደማ ሆነ። እንዲህም ተባለ፡ "መሪ የማያስፈልጋት መኪና የሚያመርቱበት ዘመን ይመጣል፡ በሆነ አይነት ኃይል የምትመራ ትሆናለች።" አሁን ደርሰውበታል። አሁን አግኝተውታል፡ ማግኔጢሳዊ ኃይል በሆነው፡ በራዳር መቆጣጠሪያ። ሌላ ምንም ሳያስፈልጋቸው... ወዴት እንደሚሄዱ ራዳሩን በማስተካከል፡ መሪ መያዝ ሳያስፈልጋችሁ፡ ትሄዳላችሁ።

48 አሁን፡ በዚያም ጊዜ እንዲህ ይሆናል ተብለዋል፡ "በዚያ ዘመን፡ በዩናይትድ ስቴትስ ታላቅ ሴት ትነሣለች።" እሷም ቆንጆ ልብስ ለብሳ ነበረች፡ ልቧ ግን እጅግ ክፉ ነበረች። እናም በራዕዩ ላይ በቅንፍ ውስጥ ገባሁ፡ ቢጫ ወረቀት ላይ፡ "ምናልባትም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡" ይላል። ሴቶች ምርጫ ላይ እንዲሳተፉ ከመፈቀዱ የተነሣ ለዚህ አገር የማይጠቅም ሰው ይመርጣሉ። ያደረጉትም ይህንኑ ነው። በትክክል። አሁን፡ "ያ መጀመሪያ ይሆናል፡" አለ።

49 አሁንም ከተባለው ነገር፡ ሌላ ነገርም... ወዲያውኑ ከዚያ በኋላ፡ ይህች አገር ተሰባብራ፡ እንደ ፍም ስትሆን አየኋት። አሁን፡ እነዚያን ነገሮች ከተፈጸሙ፡ ይህ ሌላኛውም ይሆናል። እኛ ያለነውም... ዛሬ ማታ እዚህ የመጣሁበት ምክንያትም ይህንን አውጥቼ ለማስቀመጥ እና በጄፈርሰንቪል ላለው ህዝብ እንዲዘጋጅ ለማድረግ ነው፡ ምክንያቱም በቅርቡ እንደገና የመስክ ተልእኮዎች ለመጀመር እያስተካከልኩ ነው፡ እንዲሁም በምን ሰዓት ልጠራ ወይም እንድወሰድ እንደምችል አላውቅም። ያ—ያ... ያንን አናውቀውም። ቤተ ክርስትያን አሁን እየኖረችበት ያለውን ዘመን ማወቋ... እርግጠኛ መሆን እፈልጋለሁ፡ ምክንያቱም ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ለዚህ እኔን ተጠያቂ ያደርገኛልና።

50 አሁን—አሁን፡ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ፡ መጽሐፍ እንደሚል፡ መልአክ ነበራቸው። መልአኩም... **መልአክ** ማለት ምን ማለት እንደሆነ ስንቶች ታውቃላችሁ? "መልእክተኛ" ማለት ነው፡ መልእክተኛ። እና በእነዚያም—ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት **ሰባት መላእክት** ነበሩ፡ ማለት "ሰባት መልእክተኞች ናቸው።" እናም፡ በእጁ ያሉ ከዋክብት ናቸው። በእጁም እነዚህ—እነዚህ አሥራ ሁለቱ... እኛ አሁን እየኖርንበት ባለው ሌሊት የህልውናውን ብርሃን የሚያንፀባርቁ እነዚህ ሰባት ከዋክብት ናቸው። ይህም

በምሽት መንቀሳቀስ እንድንችል፡ የሰማይ ከዋክብት፡ የጸሐይን ብርሃን ለምድር እንደሚያንጸባርቁ እንዲሁ ነው።

51 እንግዲህ በዚያን ጊዜ፡ እነዚያ መላእክቶች፡ እያንዳንዳቸው ሓላፊነት እና ስፍራ እንደነበራቸው ተረድተናል። እና፡ ወንድሞች ሆይ፡ የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን መልአክ ስለምናውቀው፡ ዛሬ ማታ እንደርስበትም፡ ነገር ግን የሌሎቹን አብያተ ክርስትያናት መላእክቶች፡ ከታሪክ ማህደር ፈልገን አውጥተን፡ በፊታችሁ ስናሳያቸው፡ ምስጢራዊ እና አስደናቂ ነገር ይሆናል። የመጀመርያይቱ ቤተ ክርስቲያን መልአክ የእግዚአብሔር መልእክተኛ፡ ቅዱስ ጳውሎስ ነበር፡ የመሰረታትም እርሱ ነው። የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መልአክ ቅዱስ ጳውሎስ ነው። የቤተ ክርስቲያን... አሁን፡ ይህ ያደረግኩበት ምክንያት...

52 እንግዲህ፡ ስለ ሌሎቹ ላትስማሙባቸው ትችላላችሁ፡ ነገር ግን በኃይል እስኪነካኝ እና እስኪቀባኝ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ስር በመሆን ለአያሌ ቀናት ቆይቻለሁ። ማወቅ የቻልኩበት ምክንያትም ይህ ነው። ስለዚህ የታሪክ አዋቂ ከሆናችሁ፡ የተመረጡትን ሰዎች፡ ተመልከቷቸው... ከመገለጥ የተነሣ ለቤተ ክርስትያን የተላኩ መሆናቸውን የተናገርኳቸው፡ እነዚያ ያው መላእክቶች፡ ይሄኛው በመጀመርያ እንደነበረው አይነት አገልግሎት ነበራቸው። ያም አገልግሎት ሊለወጥ አይችልም፡ በጴንጤቆስጤነቱ እስከመጨረሻው መቆየት አለበት።

53 አሁን፡ እዚህ ላይ የታሪክ ተመራማሪዎች በዚህ ሰው ላይ ከእኔ ጋር አይስማሙም፡ በስምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ግን የዚያን ዘመን መልአክ እንደ ሆነ የማውቀው ኢራኒየስ ነው። ይልቁንም ብዙዎቻችሁ፡ ፖሊካርፕ ነበር፡ ፖሊካርፕ ነው፡ እርሱ ነበር ትላላችሁ። እንደው ፖሊካርፕ ግን፡ ያኔ እየጀመረ-ወደ ነበረው፡ ወደ ካቶሊክ ድርጅት በበለጠ የሚያደላ ነበር። ኤራኒየስ ግን በልሳኖች የሚናገር፡ የእግዚአብሔርም ኃይል፡ እና ምልክቶችም የሚከተሉት ሰው ነበር። እርሱ ፖሊካርፕ ከተሰቀለ ወይም ከተገደለ፡ ከተገደለ በኋላ፡ ብርሃኑን ያበራ የእግዚአብሔር መልአክ ብርሃን ነበር፡ ኢራኒየስ ከተማሪዎቹ አንዱ ሲሆን፡ ፖሊካርፕ ደግሞ የቅዱስ ጳውሎስ... ማለቴ የቅዱስ ዮሐንስ ተማሪ ነበር። ከዚያም ኢራኒየስ ስፍራውን ተቀበለ እና፡ ብርሃኑን አወጣው።

54 የጼርጋሞስን የብርሃን መልአክ ደግሞ—ታላቁ ቅዱስ ማርቲን ነበረ። ከኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥሎ፡ በምድር ላይ፡ ከቅዱስ ማርቲን የሚበልጥ ሰው ኖሯል ብዬ አላምንም። ኃይል? እንዴ ገዳዮቹ አንገቱን ሊቆርጡ ወደ እሱ ይመጣሉ (በምልክትና በድንቅ፡ እና በጴንጤቆስጤ በረከትም የሚያምን ነበር)፡ ሊገድሉት ፈልገው፡ በሄዱ ጊዜም፡ መጎናጸፊያውን ወደ ኋላ ነቅሎ አንገቱን ዘረጋላቸው። ገዳዩም ራሱን ሊቆርጠው ሰይፉን መዘዘና፡ የእግዚአብሔርም ኃይል ገፍትሮ ከአጠገቡ አሽቀነጠረው፡ ከዚያምም አንድ ነገር ከእርሱ ለመጠየቅ በጉልበቱ በዳዴ ወደ እርሱ ቀረበ... ? ... አሜን። የቤተ ክርስትያን መልአክ ነበረ።

55 ሌሎች ነገሮችም። እንዴት እንዳደረገ ተመልከቱ... ከወንድሞቹ ወንድሙ ታንቆ ተንጠልጥሏል፡ እና ፍለጋውን ወደ መንገድ ወጣ፡ የሆነውን ተመለከተ። እሱ በዚያ በደረሰ ጊዜ፡ አንቀው ገድለውታል። አይኖቹ ከጭንቅላቱ ጉልጉል

ብለው ወጥተዋል፡ ሞቷል፡ እንዲህ ተዘርግቶ ወድቋል። ወደ እርሱ ገባና በጉልበቱ ወድቆ ወደ እግዚአብሔር እየጸለየ፡ ለአንድ ሰዓት ያህል በላዩ ላይ ተዘረጋ። የእግዚአብሔርም ኃይል በሰውየው ላይ መጣና፡ ተነሥቶ እጁን ይዞ በዚያው ሄደ። ያ ልክ እንደ ጆርጅ ዋሽንግተን፡ አብርሃም ሊንከን፡ ወይም እንደ-ሌሎቹ ታሪክ ነው። ታሪክ ነው።

56 አዎን፡ ወዳጄ! ቅዱስ ማርቲን የጴርጋሞስ ቤተ ክርስትያን መልአክ ነበረ፡ ይህችም፡ ከዚያ ሁሉ በኋላ ወደ ካቶሊካዊነት ጋብቻ የወሰደቻቸው ቤተ ክርስቲያን ናት።

57 የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን መልአክ—ኮሉምባ ነበረ።

58 የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን፡ የሞተችው ቤተ ክርስቲያን መልአክ... **ሰርዲስ** ማለት “የሞተ” ማለት ነው። ሰሙ ሳይሆን፡ አንድ ሰም ይዞ ወጣ፡ “ህያው እንደመሆንህ ሰም አለህ፡ ሞተህማል።” በዚያ ዘመን ጥምቀትን እንዴት እንዳወጡት እዩት። አያችሁ፡ ከዚያ ርቀዋል። የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን መልአክ፡ የመጀመሪያው ተሐድሶ አራማጅ ማርቲን ሉተር ነው።

59 የፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን መልአክ፡ መልእክተኛው ጆን ዌስሊ ነበር፡ መልዕክተኛው።

60 የሎዶቅያ የቤተ ክርስቲያን መልአክ—እስካሁን አልታወቀም። አንድ ቀን ግን ይመጣል፡ ምናልባት አሁን... በምድር ላይ ይሆናል። “ጆሮ ያለው... ” [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... ይህ የምንኖርበት ባለው ዘመን እንደሆነ እወቁ። የፍርዱን ነገር እግዚአብሔር ያደርገዋል።

61 አሁን፡ አሁን እናስተውል፡ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ወደ መጀመሪያው የቤተክርስቲያን ዘመን እንመለስ። አሁን እንዲህ እንዲሆን እፈልጋለሁ... በጥሞና እንድታዳምጡኝ የምመኘው የተፃፉ ትንንሽ ነገሮች ይዣለሁ።

62 የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን፡ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን፡ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሥራዎች፡ እግዚአብሔር የፈረደባቸው፡ ፍቅር ስለሌለበት ሥራቸው ነው። ሽልማታቸው የሕይወት ዛፍ ነበር።

63 የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን በሰደት ላይ የነበረች፡ በመከራ ውስጥ ያለፈች ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ሽልማቷ የሕይወት አክሊል ነበር።

64 ሦስተኛው ቤተ ክርስቲያን፡ ጴርጋሞስ፡ የሐሰት ትምህርት ዘመን፡ የሰይጣን ውሸት፡ እና የጽጽሰና አገዛዝ መሠረት፡ ቤተ ክርስትያን ከመንግሰት ጋር የተጋባችበት ዘመን ነበር። ሽልማታቸው የተደበቀ መና እና ነጭ ድንጋይ ነበር።

65 የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳዊ አሳችነት የነበረባት፡ የጨለማው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ሽልማታቸው አሕዛብን የሚገዙበት ሰልጣን እና ሰርዓት፡ እንዲሁም የንጋት ኮከብ ነበረ። በዚያ ያለፈችው ታናሺቱ መንጋ ነበረች።

66 የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን የተሃድሶ ዘመን፣ ታላቁ ሚሰዮናዊ ዘመን የነበረበት... ወይም ሚሰዮናዊ ሳይሆን፡ ነገር ግን የተደበቁ ሰሞች፡ የራሳቸው ሰም የነበራቸው ናቸው። እና ሽልማቱ ነጭ ልብሰ እና የህይወት መጽሐፍ ሰም ነበር (ይህም በፍርድ ጊዜ ሊመጣ ያለው ነው)። ስለ ህይወት መጽሐፍ፡

ፍርዳችሁ ከህይወት መጽሐፍ እንደሚሆን፡ ባለፈው ቀን አይተነዋል። ቅዱሳን ወደ ፍርድ አይደርሱም፡ ከዚያ በፊት ይወሰዳሉና።

67 የፊላዴልፊያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን የወንድማማችነት ፍቅር ዘመን ነበር፡ ታላቁ የተልዕኮ ዘመን እና ታላቁ የሚሰዮናውያን ዘመን፡ የተከፈተው በር የነበረበት ነው። ሽልማቱም—አምድ ነበር። የእግዚአብሔር ሰሞች የተገለጠበት ዘመን—በዚህ ዘመን፡ በ1906 አካባቢ በወጣ ጊዜ ነበረ። እሺ።

68 የሎዶቅያ ዘመን ለብ ያለች ቤተ ክርስቲያን ነበረች፡ ባለ ጠጋ፡ ዕቃም የበዛላት፡ ምንም የማያስፈልጋት፡ ነገር ግን ጎሰቋላ፣ ድሃ፣ ዕውር፣ ምስኪን፣ ራቁታም ነበረች። ያንን ዘመን ለሚያሸንፋ የተሰጠ ሽልማት፡ ከጌታ ጋር በዙፋኑ ላይ መቀመጥ ነበር።

69 አሁን ዛሬ ማታ፡ ሰለ ዛሬው ጉባኤ፡ በጥቂቱ ከፋፍለን ለማየት፡ የመጀመሪያውን የቤተክርሰቲያን ዘመን 2ኛውን ምዕራፍ እንወሰዳለን። እንግዲህ...

አሁን እርሱ ሰለተገለጠ ማን እንደሆነ አውቀነዋል፡ አምላክ ነው!

70 እንግዲህ፡ አሰቀድሜ እንዳልኩት፡ ቤተክርሰትያኒቱ የጀመረችው በ53 ሲሆን፡ 170 ድረሰ ይደርሳል። እና (ሀ) የኤፌሶን ከተማ፡ ከእሰያ ከሦሰቱ ታላላቅ ከተሞች አንዷ ሰትሆን፡ ብዙውን ጊዜ ሦሰተኛዋ የክርሰትና እምነት ከተማ ተብላ ትጠራለች (አንደኛ ኢየሩሳሌም፣ ሁለተኛ፣ አንጾኪያ፣ ሦሰተኛም፣ ኤፌሶን ነበረች)... (ሐ) ታላቅ የንግድና የግብይት ከተማ... (ሠ) ገዢዋ የሮም መንግሥት ነበር... (ረ) ቋንቋዋ ግሪክኛ ነበር። የታሪክ ተመራማሪዎች ዮሐንሰ፡ ማርያም፡ ጴጥሮሰ፡ እንድርያሰ፡ እና ፊልጶሰ ሁሉም እዚያ እንደተቀበሩ ያምናሉ። ኤፌሶንም በውበቷ ትታወቅ ነበር።

71 በኤፌሶን የነበረው ክርሰትና፡ አይሁዶች በኤፌሶን የኖሩት ነበር። የተመሰረተውም **እ.ኤ.አ** 53 ወይም 55 ነበር። ክርሰትና እዚያ የተተከለው በቅዱሰ ጳውሎሰ ነው። በኋላም፡ ቅዱሰ ጳውሎሰ በኤፌሶን ሦሰት ዓመት ኖረ። የጳውሎሰ ትምህርት በኤፌሶን ባሉ አማኞች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። ቀጥሎ፡ ጢሞቴዎሰ የኤፌሶን ቤተ ክርሰቲያን የመጀመሪያ ቢሾፕ ነበር። ጳውሎሰም ለኤፌሶን ቤተክርሰቲያን ጽፏል። በጳውሎሰ ዘመን ታላቅ ቤተ ክርሰቲያን ነበረች።

72 ኤፌሶን ማለት... **ኤፌሶን** የሚለው ሰም "የተለቀቀ፡ ዘና ያለ፡ ወደኋላ የተመለሰ" ማለት ነው። በእግዚአብሔር፡ "ወደ ኋላ የተመለሰችው ቤተ ክርሰቲያን" ተብላለች። እግዚአብሔር—እግዚአብሔር ሥራቸውን፡ ድካማቸውን፡ እና ትዕግሥታቸውን ገልጿል። የመጀመሪያ ፍቅራቸውን በመተዋቸው፡ ወደ ኋላ በመመለሳቸው፡ እና ብርሃን ማብራት በመተዋቸው፡ እግዚአብሔር ሕይወታቸውን ገሥጿል። ኤፌሶን የተታለለች ቤተ ክርሰቲያን ሳትሆን፡ በፍጹም ፍቅር ባለመቀጠሏ ራሷን የጣለች ናት።

73 የኤፌሶን ማጠቃለያ፡ ፍቅር የሌለው፡ ፍሬዋ፡ ወደ ክህደት አመራ። የተገባው ተሰፋ ቃል፡ በቤተክርሰቲያን ዘመን ድል ለሚነሱ የኤፌሶን ቅዱሳን የተገባላቸው ቃል፡ ገነት፡ የሕይወት ዛፍ ነው።

74 እዚህ ጋር አንድ የሚደንቅ ነገር አለ። የሕይወት ዛፍ በዘፍጥረት ሦስት ጊዜ፡ በራዕይ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል። በዘፍጥረት—ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው፡ በኤደን ነበረ፡ ዛፉም ክርስቶስ ነበረ። ክርስቶስ፡ በራዕይ ውስጥ ሦስት ጊዜ የተጠቀሰው፡ በገነት ውስጥ ነው። ኦህ፡ የሰባ ነው። ጌታ ይባርክ።

75 አሁን የኤፌሶን 1ኛ ምዕራፍ እንጀምራለን... ወይም የ2ኛ ምዕራፍ፡ 1ኛው ቁጥር፡

**በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡ በቀኝ እጁ ሰባቱን ከዋክብት የያዘው፡ በሰባት የወርቅ መቅረዞች መካከል** የሚሄደው **እንዲህ ይላል፡**

76 በዛን ጊዜ—መልእክተኛው ዮሐንስ ነው። በሰባት የወርቅ መቅረዞች መካከል የሚሄደው፡ ሁሉን ቻይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። ምን እያደረገ ነው? **በአንድ** መቅረዝ ውስጥ እራመዳለሁ አላለም፡ በሁሉም መካከል ይመላለስ ነበር። ይህ ምንን ያመለክታል? እርሱ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ዘለዓለም ድረስ፡ በሁሉም የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ለአማኝ ሁሉ ያው አምላክ መሆኑን ያሳያል። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለዘመናት ሁሉ እና ለእያንዳንዱ ሰው፡ ትላንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘለአለም ድረስ... ያው ሆኖ ይመጣለታል።

77 "በቀኝ እጁም ይዟል።" **ቀኝ እጅ** ማለት "ሥልጣኑ እና ኃይሉ ነው።" የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ዘመናት ሰባቱን መልእክተኞች በቀኝ እጁ የያዘ (በቁጥጥር፡ ስር) ያዋለ። ኦህ፡ ይህ ደስ ይለኛል። በእነዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ሲመላለስ፡ ክርስቶስ፡ በጨለማው ዘመናት፡ በሁሉም ዘመናት እራሱን ለሕዝቡ እያስተዋወቀ ሲታይ፡ ቤተ ክርስቲያን ተራ ወደ መሆን ሆና ስትሄድ፡ ከፊሎቹም በአንድ መንገድ ሌሎችም በሌላ መንገድ ሲሄዱ፡ ትንሿ የቤተክርስቲያን መንጋ ግን አሁንም እንደቀጠለች፡ ክርስቶስም ቃሉን እያጸና፡ አጠቃላይ ነገሩን እየፈጸመ፡ ከእነርሱ ጋር ሥራውን ይሰራል።

78 ይህንን ማጥናት ስትጀምሩ፡ ዛሬ ያለንን ነገር እንዴት እንዳገኘነው ማየት በጣም ቀላል ነው። አሁን፡ እዚህ መጀመሪያ ላይ... ሁላችሁም ይህንን ከፍ አርጋችሁ ማየት እንደምትችሉ አምናለሁ። [ወንድም ብራንሃም ስሌዳው ላይ አሳየ—አርታዒ።] አንደኛ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ይኸውና፡ ይህም ጴንጤቆስጤ ነው። ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን፣ ሦስተኛ፣ አራተኛ፣ አምስተኛ፣ ስድስተኛ፣ ሰባተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን። አሁን ይህን ቀርባችሁ ካስተዋላችሁ፡ የቤተክርስቲያን ጅማሬ ከበዓለ ሃምሳ ነው። ስንቶች ታምናላችሁ? በበዓለ ሃምሳ የሆነውን አያችሁ? ከዚያም ቤተክርስቲያን እየወረደች እናያታለን። በጥቂቱ መደብዘዝ ጀመረች፡ እየደበዘዘች፡ መደብዘዝዋም እየጨመረ፡ በጥቂቱ፡ **ይህች** እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን እየጠፋች ሄደች።

79 አሁንም፡ ክርስቶስ... ቤተክርስቲያን ምንም ያህል ታናሽ ብትሆንም፡ "በስሜ ሁለት ወይም ሶስት አንድ ላይ በሚሰበሰቡበት፡ እኔ በመካከላቸው እሆናለሁ።" በምን ውስጥ አንድ ላይ ሲሰባሰቡ? በሜቶዲስት ስም? በባፕቲስት ስም? በጴንጤቆስጤ ስም? በኢየሱስ ስም! ምንም ያህል ታናሽ ቢሆኑም፡ ሁለት ወይም ሦስት በአንድነት በተሰበሰቡበት ሁሉ። በመጨረሻው ቀንም እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ በጣም ትንሽ ይሆናሉ፡ እርሱም ተናግሯል፡

በፍጥነት መጥቶ ስራውን ማሳጠር አለበት አለበለዚያ ግን ለመነጠቅ የሚድን ስጋ አይኖርም ብሏል። "ሁለት ወይም ሶስት በስሜ በተሰበሰቡበት!"

80 አሁን፡ የመጀመሪያው ዙር፡ ሐዋርያቶች ናቸው። አሁን፡ ይህ በመጀመሪያ፡ በዓለ ሃምሳ እንደነበረ እናያለን። ያው ታላቅ አምላክ፡ በዙሪያው ሁሉ ይመላለሳል፡ በየዘመናቱ ስለ ተመላለሰ እነዚያ ታላላቅ ምልክቶች በሁሉም ዘመናት መደረጋቸው ግድ ነው። ማንን ለመባረክ? በስሙ የተሰበሰበውን ህዝቡን።

81 በቤተክርስቲያኒቱ ስንጓዝ በዚህ ውስጥ እንድትመለከቱ እፈልጋለሁ። **ይህች** ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ስም ነበራት። **ይህች** ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ስም ነበራት። **ይህች** ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ስም ነበራት። **ይህች** ቤተ ክርስቲያን ጣለችው። ይህች የሉተራን ዘመን ቤተ ክርስትያን፡ "ሕያው እንደመሆንህ ስም አለህ፡ ሞተህማል፡" ጋር ወጣች። እናም **እስከዚህ** ዘመን መጨረሻ ድረስ ወደ ታች ወረደች፡ እና በዚህ ዘመን እና **በዚህ** ዘመን መካከል ያንን ስም እንደገና ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያመጣ የተከፈተ በር አለ። አሁን በመጻሕፍት ውስጥ ካገኘን በኋላ፡ እውነት መሆኑን ተመልከቱ እና እዩት። በዚያ—በዘመናት መካከል።

82 አሁን፡ ነገ ማታ ሁላችንም እንድናየው ይህንን ስዕል እዚህ ለማዘጋጀት እሞክራለሁ። እና ምናልባት ነገ ከሰአት በኋላ መጥቼ በደንብ እስለዋለሁ... አንዳንዶቹ—እናንተን ላናግራችሁ የምፈልጋቸውን እቅዶቼ። እና ማንኛችሁም ታሪክ ካላችሁ፡ አምጧቸው። ወይም ማስታወሻ ይዛችሁ ወደ ቤተ መዛግብት ውረዱና፡ ወይም ወደ አንድ ቦታ ሄዳችሁ ታሪኩን አንብቡት ይህ ትክክል እንደሆነ መርምሩ።

83 አሁን 1ኛ ቁጥር። ምን እየሰራ ነው? ሰላምታ እያቀረበላቸው ነው።

> **ወደ—ወደ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መልአክ**... (ለዮሐንስ) **ጻፍ፡ በቀኝ እጁ ሰባቱን ከዋክብት** የያዘው **እንዲህ ይላል፡ በሰባት የወርቅ መቅረዞች መካከል የሚሄደው**፡ (ሰላምታ ነው)

84 አሁን 2ኛ ቁጥር እና 3ኛ ቁጥር ላይ፡ አመሰግኗቸዋል፡

> **ሥራህንና፡** ድካምህን፡ **ትዕግሥትህንም እውቃለሁ፡... ክፉዎችን ልትታገሰ እንዳትችል፡ እንዲሁም ሳይሆኑ፡ ሐዋርያት ነን የሚሉቱን መርምረህ፡ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው እውቃለሁ፡**

85 ተመልከቱ፡ ያ ክህደት በዚህ በመጀመሪያው ዘመን፡ መግባት ጀምሯል። ገና ያኔ ጀማምሮታል፡ ምክንያቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዛትን እና ኢየሱስ በምስክርነቱ የተናገራቸው ቃላት፡ መጠበቅ የምትፈልገው ቤተ ክርስትያን እና የተመረጡ ወገኖች፡ ከመስመር መዛነፍ ጀምረው ነበርና። የሆነ ነገር መከሰት ጀመረ፡ እናም የውሸት አስተማሪዎች ተነሱ፡ መጻሕፍትን የሚጻረር፡ ስህተት የሚያስተምሩ ሰዎች ገቡ፡ የሆነ ነገር ለመጨመር እና ለመቀነስ ሞከሩ።

86 ለዚህም ነው ይህንን መገለጥ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው እንዲህም ያለው፡ "የሚቀንስ ወይም የሚጨምር፡ ድርሻው ከሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ይወሰዳል።" ጥፋት፡ ነው፡ ወንድሜ! ከእግዚአብሔር ቃል ጋር

አትቃለዱ! ማንም ይጕዳ ወይም ምንም ይጕዳ፡ ምንም ቢሆን እንዲሁ ተናገረው። በተጻፈበት መንገድ፡ እንዲሁ ነውና። ሌላ ታላቅ ነገር አንፈልግም፡ የሚተረጕምልን ቄስ ወይም ምንም ነገር አንፈልግም፡ እግዚአብሔር ራሱ መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚ ነው። ትርጓሜውን ይሰጣል።

87 እንግዲህ፡ ልብ ብላችሁ ካስተዋላችሁ፡ የአምልኮት መልክ ያላቸው፡ ሐሰተኞች ነብያት፡ ሐሰተኞች መሆናቸውን ከተረጋገጠ በኋላ፡ ከክፉዎች መለየት ነበር። ቤተ ክርስትያን በወቅቱ ምን ያህል ተራ ወደመሆን እንደወረደች ይታያችኋል? በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ስር የኖረ ሕዝብ ማፈራረስ ጀመሩ፡ ሰዎች እንዲሳለቁባቸው ማድረግ ጀመሩ።

88 እሺ፡ ኢየሱስ፡ "ስለ ጽድቅ ስትሰደዱ ብፁዓን ናችሁ" አላለምን? ተራ ወደመሆን እንዲወርዱ በፍጹም አላዘዘም። እርሱ ያለው፡- "ደስ ይበላችሁ፡ ሐሴትም አድርጉ፡ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን አሳድደዋቸዋልና።" በማቴዎስ ወንጌል፡ ምዕራፍ 5 ላይ፡ በብጹአን ናችሁ ውስጥ ተናግሯል፡ "ብጹአን ናችሁ!" እያችሁ፡ ጌታ ኢየሱስን በመውደዳችሁ ብቻ የሚሳለቁባችሁ ሰዎች መኖራቸው በራሱ፡ መታደል ነው። ሲረግሟችሁ፡ በእናንተ ላይ የእግዚአብሔርን በረከት እንዲመጣ እያደረጉ... ብቻ ናቸው። በዚያን ጊዜ በበለዓም ላይ እንደሆነበት ሁሉ፡ በላያቸው ላይ ይመለስባቸዋል። ወደራሳቸው—ይመለሳል። እያችሁ፡ ክርስትያን በመሆናችሁ ብቻ ሲሳለቁባችሁ፡ በራሳቸው ላይ ይመለሣል፡ ለእናንተ ግን እግዚአብሔር በረከት ያደርገዋል፡ ምክንያቱ፡- "ሰዎች ስለ ስሜ ሲያሳድዱአችሁ ብፁዓን ናችሁ።" ስለ ስሙ፡ "ብጹአን ናችሁ!"

89 አሁን እግዚአብሔርን ለመምሰል ፈልገው እንደጀመሩ ደርሰንበታል።

90 አሁን፡ እዚሁ ቆሞ ብዬ አንድ ነገር መናገር እችላለሁ፡ ማለት እንዳለብኝ አምናለሁ። በእያንዳንዱ ሪቫይቫል ላይ አስተውላችኋል... አሁን፡ እናንተ አገልጋይ የሆናችሁ ወንድሞች፡ ይህን መርምሩት። ያዕቆብና ርብቃ ኤሳውንና ያዕቆብን፡ መንታ ልጆችን እንደወለዱ ሁሉ፡ እያንዳንዱ ሪቫይቫልም መንታ ልጆች ይወልዳል። ማለቴ ይስሐቅ... ያዕቆብ ሳይሆን፡ ይስሐቅ እና ርብቃ። ይስሐቅ እና ርብቃ መንታ ልጆችን ወለዱ። አባቱ ቅዱስ ሰው ነበረ፡ እናቱም ቅድስት ሴት ናት፡ ነገር ግን ሁለት ወንዶች ልጆች፡ ዔሳው እና ያዕቆብን ወለዱ።

91 አሁን፡ ሁለቱም ሃይማኖተኞች ነበሩ። ኤሳው ግን ወደ ሥራና እና ትግበራ ሲመጣ፡ እንደ ጥሩ የሰነ ምግባር ሰው፡ ከያዕቆብ ይልቅ፡ በብዙ መንገድ፡ የተሻለ ልጅ ነበረ። ይህን ታውቃላችሁ? ያዕቆብ ሁሉ ጊዜ ከእናቱ ስር የማይለይ ትንሽ ልጅ ነበር። ኤሳው ግን ነብይ ለነበረው ለታወረው አባቱ የአደን ስጋ ያበላው ዘንድ የሚወጣ፡ የሚሰራ ነበር፡ ይንከባከበው ነበር። ያዕቆብ ግን በአእምሮው አንድ ነገር ብቻ ነበረው፡ ብኩርናውን ተመኘ! ለምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለበት ወይም ምን ማድረግ እንዳለበት ግድ አልሰጠውም፡ በሕይወቱ ውስጥ ዋናው ነገር ብኩርና ነበር! ኤሳው ግን ናቃት።

92 ፍጥረታዊው ሰው አይታያችሁምን—ፍትረታዊው ሰው? ሪቫይቫል በመጣ ቁጥር፡ ከእያንዳንዱ ሪቫይቫል ሁለት አይነት ሰዎች ይወጣሉ። ፍጥረታዊ ሰው ይመጣል፡ ወደ መሠዊያውም ወጥቶ እንዲህ ይላል፡- "አዎን፡ ጌታዬ፡ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኜ ተቀብያለሁ።" ከዚያም ይወጣል፡ ምን ያደርጋል? በመጀመሪያ

የሚያደርገው፡ የአንድ ተራ፡ እና ቀዝቃዛ ቤተ ክርስትያን አባል ይሆናል፡ ምክንያቱ እሱ እንደሚመስለው፡- “እንደው፡ የቤተ ክርስትያን አባል ከሆንኩ፡ እንደ እከሌ ጥሩ ሰው እሆናለሁ። እንደ **እከሌ-እና-እከሌ** ጥሩ ሰው አይደለሁምን? የቤተክርስቲያን አባል እስከሆንኩ ድረስ እና በአፌ እስከመሰከርኩ ድረስ ምን ልዩነት አለው?” እንዴ፡ ብዙ ልዩነት አለው እንጂ። ዳግም መወለድ ይኖርብሃል። ብኩርናን መቀበል አለብህ።

93 እና ያዕቆብ ምንም ያህል ቢሳቅበትም ግድ አልሰጠውም። እሱ የሚፈልገው ብኩርናዋን ብቻ ነው፡ እንዴት እንደሚያገኛት ጉዳዩ አይደለም።

94 እንደው፡ ብዙ ሰዎች ብኩርናውን ለማግኘት አይፈልጉም ምክንያቱም በሰዎች ዘንድ ተወዳጅነት የጎደለው ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው። በመሠዊያው ላይ ወርደው ትንሽ ማልቀስ፡ ወይም ጥቂት መጾም፡ ወይም—ወይም ሌላ ነገር አይፈልጉም። ይህን ማድረግ—አይ—አይ—አይፈልጉም። ብዙ ሴቶች... ታውቃላችሁ፡ በብዛት፡ መዋቢያ-... ሜክአፕ ይለቀለቁና፡ እንባ ካለቀሱ እንደሚለቅባቸው፡ እና እንደገና መስራት እንዳለባቸው ያሰባሉ። ለምን፡ እነዚህ... ’ኮ... ለማቃለል ብዬ አልናገርም፡ እንደዚያ እንዳይመስልብኝም ተሰፋ አደርጋለሁ፡ እውነቱ ግን ያ ነው። አይፈልጉትም። አዲሱ ልደትን አይፈልጉም፡ ምክንያቱ አዲስ ልደት ምስቅልቅል ነው። ልክ እንደሌላው ልደት ነው። ማንኛውም ልደት ምስቅልቅል ያለ ነው፡ የትም ይሁን ግድ የለኝም። በአሳማ ጉሮኖ ይሁን በጋጣ ውስጥ፡ ወይም በሮዝ ባጌጠው፡ በሆስፒታል ክፍል ውስጥ፡ ምስቅልቅል ነው።

95 አዲስ ልደትም እንዲሁ መመስቃቀል ነው! ኣሜን። ያላሰብከውን ነገር እንድታደርግ ያደርግሃል፡ ጥግ ላይ ቆመህ ከበሮ እንድትደበድብ፡ ወይም እንድትዘምር ያደርግሃል፡ “ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! ሃሌ ሉያ! እግዚአብሄር ይመስገን! ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!” ለምንድነው፡ እንደ እብድ ትሆናለህ። በሐዋርያቱ ላይ ያደረገው እንዲህ ነው፡ ድንግል ማርያም ላይ ያደረገው እንዲሁ ነው፡ እንደ ሰከረ ሰው ሆነች። በማህበረሰብ ዘንድ ምስቅልቅል ነበረች፡ ህይወት እንዲገለጥ ግን ምስቅልቅል ይጠይቃል። አሜን!

96 ምንም ነገር ካልሞተ እና ካልበሰበሰ፡ ህይወት ከእሱ ሊወጣ አይችልም። ሰው ካልሞተ እና በራሱ ሀሳብ ካልበሰበሰ በቀር፡ ክርስቶስ ወደ ልቡ ሊገባ አይችልም። ስለ ራስህ እንዲህ ማሰብ ስትጀምር፡- “ለምሳሌ፡ ወደ መሰውያው ቀርቤ እንዲህ ማለት ከጀመርኩ፡ ‘አዎን፡ ጌታ ሆይ፡ እኔ—መልካም ሰው ነኝ፡ እቀበልሃለሁ። አሰራቴን እከፍላለሁ። እንዲህ አደርጋለሁ፡’” ስለ አሳቦችህ እዚያ መሞት እና መበስበስ አለብህ። መንፈስ ቅዱስ ይያዝህና የወደደውን ያድርግብህ። አብረህ ተመስቃቀል። ለማንቋሸሽ አይደለም፡ ሰቅጣጭ ነገር ቢመስልም፡ እውነት ነው። ይሄን ለእናንተ ለማስረዳት የማውቀው ብቸኛው ቡጢ ይህ ብቻ ነው።

97 በዚያ ቀን ከነበሩ ከተከበሩ የአይሁድ ጉባኤ በበለጠ፡ ሰዎች በተብታባ ልሳኖች ከማየት የበለጠ ምን መመስቃቀል አለ? መንተባተብ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? “ሃህ፡ ሃህ፡ ኡህ፡ ኡህ፡ ኡህ፡ ኡህ... ? ... ” እንደሰከረ ሰው፡ ሌላ ልሳን። “ሃህ፡ ሃህ፡ ኡህ፡ ኡህ፡ ኡህ።” በእውነት እነርሱም የመሰሉት ያንኑ ነው። ዝርክርክ መሰሉ!

98 እንዲህ አሏቸው፡ “ሰዎቹ ወይን ጠጅ ጠጥተው ሰከሩ እንዴ? ”

ነገር ግን አንዱ ተነስቶ፡ እንዲህ አለ፡ “ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፡ ቃሌንም ስሙ፡ እነዚህ እናንተን እንደመሰላችሁ የሰከሩ አይደሉምና።” እርሱ ግን ወደ ቅዱስ ቃል ዞር አለና፡ “**ያ** በነቢዩ በኢዩኤል የተነገረው **ይህ** ነው፡ ‘በመጨረሻው ቀንም ይሆናል፡’ ይላል እግዚአብሔር፡ ‘መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ።’”

99 ቤተክርስቲያን መጀመሪያ የተወለደችው በዚያ መንገድ ነበረ። እግዚአብሔር ፍጻሜ የሌለው መሆኑን ስንቶች ታምናላችሁ? ስለዚህ ሊለወጥ አይችልም። ስለ ቤተክርስትያን የመጀመሪያው አሳቡ ያ ከሆነ፡ በመጨረሻው ላይ የምትኖረው ቤተክርስትያንም ያው ናት። ሊለወጥ አይችልም። ታዲያ እጅ በመጨባበጥ፡ ውይም ውኃን በመርጨት፡ ወይም—በዚያ ከተፈጸመ በሌላ ነገር እንዴት ትቀይሩታላችሁ? ሐዋርያት ሁሉ ወደዚያ መንገድ ሄደዋል።

100 ይህ ሁሉ ካደረጉ በኋላ... መንፈስ ቅዱስ በላያቸው ወረደ፡ ጴጥሮስም እንዲህ አለ፡ “ውሃን መከልከል እንችላለንን፡ እነዚህ እንደ እኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን መቀበላቸውን እያየን ውኃን እንከልክላለንን? ” በጌታ በኢየሱስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው። ትክክል ነው።

101 ጳውሎስም ወደ ሌላ ቦታ ወርዶ፡ ጥቂት ባፕቲስቶች እግዚአብሔርን እያከበሩ፡ እየጮኹ ደስ ሲላቸው አገኛቸው፡ እንዲህም አላቸው፡ የሐዋርያት ሥራ 19 ላይ፡ እንዲህ አላቸው፡ “ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስ ተቀበላችሁን? ”

እነርሱም፡ “አልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ሰንኳ አልሰማንም አሉት።”

“እንኪያስ በምን ተጠመቃችሁ፡” አላቸው?

“እኛ የተጠመቅነው እየሱስን ባጠመቀው ሰው፡ በመጥምቁ በዮሐንስን ነው፡” አሉት።

102 “እዋን፡ እሱ አሁን አይጠቅምም፡” አላቸው። አያችሁ? ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ቀን አትሞታል። እርሱ ቁልፉ ነበረውና። አያችሁ?

“ከአሁን በኋላ አይሰራም፡ እንደገና መጠመቅ አለባችሁ፡” አላቸው። ዳግመኛም፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠመቃቸው። እጆቹን በላያቸው ላይ ጫነባቸው፡ በዚያ በመጀመሪያው ላይ ያገኛቸው አይነት ፍሬ አገኛቸው። መንፈስ ቅዱስ በላያቸው ወረደ፡ በልሳኖች መናገርና መተንበይ ጀመሩ።

103 አሁን፡ ቤተክርስቲያን በዘመናት ውስጥ እንዲህ ነበረች። በመጀመሪያ፡ እዚህ ላይ ተጀመረች።

“ትዕግስትህን አውቃለሁ። በጣም ታጋሽ ነህ፡ አውቃለሁ... አሁን ይህን አሰብ፡ በመቅረዞች መካከል የምሄደው እኔ ነኝ። ትዕግስትህን፡ እና ስራህን፡ እና ድካምህን፡ እና ፍቅርህን፡ እና የመሳሰሉትን አውቃለሁ። ያደረጋችሁትን ሁሉ አውቃለሁ። እና እራሳቸውን ‘ነቢያት፡ ሐዋርያት’ ነን የሚሉትን መርምረህ፡ ሃሰተኞች ሆነው እንዳገኛሃቸው አውቃለሁ።” ኦህ፡ እንደወረደ ነው፡ አይደለም’ዴ? ለዚህ ነገር ተጠያቂው እርሱ እንጂ፡ እኔ አይደለሁም። ውሸታሞች ናቸው አላቸው።

104 መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ ይላል፡ “ሰው መርምራችሁ። ከእናንተ መንፈሳዊ ወይም ነቢይ የሆነ፡ ወይም እኔ ነኝ የሚል ማንም ቢኖር፡ እኔ እግዚአብሔር ራሴን ለእርሱ እገልጥለታለሁ። በራእይ፡ እና በሕልም እናገረዋለሁ። እርሱ የተናገረው ነገር ከተፈጸመ፡ እኔ ከእርሱ ጋር ነኝና፡ አያችሁ፡ እርሱን አትፍሩ፡ ሰሙት። ያ ካልተፈጸመ ግን፡ ቃሌ በእርሱ ዘንድ አይደለምና፡ እርሱን አትሰሙት።” አያችሁ፡ ቃሉ ከሆነ፡ ይፈጸማል።

105 አሁን፡ እነዚህ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት እየሄዱ እንዳልሆኑ አወቋቸው። አያችሁ፡ ሌላ ነገር ለማግኘት እየሞከሩ ነበር። (ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደ ቅልጥሞች ስለምንወርድ፡ አሁን አስተሳሰባችሁን በደንብ ቃንታችሁ እንድትጠብቁኝ እፈልጋለሁ።) እንግዲህ፡ እንዲህ አላቸው፡ “ማን እንደሆንክ... ታጋሽ መሆንህን፡ ትዕግሰት እና... ሌላው ሁሉ እንዳለህ አይቻለሁ። መርምረህ፡ ሐዋርያት አለመሆናቸውን አግኝተሃቸዋል። ሃዋርያት አይደሉም።”

106 አሰቀድሜ፡ እንደተናገርኩት፡ በዚህኛው ውሰጥ ከመጀመራችን በፊት፡ እያንዳንዱ ሪቫይቫል መንትዮችን ይወልዳል። አንደኛው መንፈሳዊ ሲሆን፡ ሁለተኛው ግን ከመሬት ፍጥረታዊ ሰው ነውና፡ “የቤተ ክርሰትያን አባል ሆኛለሁ፡ እንደሌሎቹ እኔም ጥሩ ነኝ ባይ ነው።” ይህ ሪቫይቫል የሚያፈራውም ያው ነው። እያንዳንዱ ሪቫይቫል፡ እንዲሁ ነውና። ሉተር ያፈራው ይህ ነበር፡ ኢራንየሰ ያፈራው ይህ ነው፡ ቅዱስ ማርቲን ያፈራው ያን ነበር፡ ኮሉምባ ያፈራው ይህ ነው፡ ዌሰሊ ያፈራው ይህ ነው፡ ጴንጤቆስጤም ያፈራው ያው ነው። በትክክል።

107 እንዴት ዘር ወደ መሆን እንደደረሱ አያችሁ? ቤተክርሰቲያናቸውን፡ እና ጥሩ ቦታዎችን ይገነቡና፡ ወደ ውብ ድንቅ ሰፍራዎች፡ እየሄዱ፡ ቆመው የሐዋርያት የሓይማኖት መግለጫ ጽሑፍ ይደግማሉ፡ “በቅድሰት ሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርሰቲያን፡ እና በቅዱሳን ኅብረት አምናለሁ።” በጻድቃን መካከለኛነት የሚያምን ሁሉ መናፍሰታዊ ሰው ነው። ከሙታን ጋር የሚገናኝ ማንኛውም ነገር የዲያብሎሰ ነው። ይህ ትክክል ነው። በእግዚአብሔርና፡ በሰው መካከል፡ አንድ መካከለኛ አለን እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱሰ ክርሰቶሰ ነው። ትክክል ነው። ጴጥሮሰ የተናገረው ይህ ነው። እናንተም የተወደዳችሁ ካቶሊኮች “የመጀመሪያው ጳጳሰ ትሉታላችሁና፡ ይህ ጴጥሮሰ የመጀመሪያው ጳጳሰ እርሱ ከኢየሱሰ ጋር ተመላለሰ።”

108 እርሱም እንዲህ አለ፡ “በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል ሌላ መካከለኛ የለም።” እናንተ ግን ዛሬ፡ ሌሎች አሰር ሺዎች አሏችሁ። ቤተ ክርሰቲያን የማትሳሳት እና የማትለወጥ ከሆነች፡ ይህ ሁሉ ለውጥ ለምን ሆነ? ቅዳሴአችሁ ሁሉ በላቲን አድርጋችኋል ይህም እንዳይለወጥ ነው። ምን ሆነ? በመጽሐፍ ቅዱሰ ውሰጥ የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ ከየት አገኛችሁት? ሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ጽሑፍ አላቸው ካላችሁ'ማ፡ እንደሚከተለው ይሆን ነበር “ንሰሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱሰ ክርሰቶሰ ሰም ተጠመቁ።” እኔ ሌላ መግለጫ ሲኖራቸውም ይሁን ሲደግሙ አይቻቸው አላውቅም።

109 ይሁን እንጂ “ወደ ሮማውያን ቅዱሳን አብያተ ክርሰቲያናት” እና ወደ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሰንመጣ ግን፡ እና “ሰማይንና ምድርን የሚጠብቅ ሁሉን የሚገዛ

እግዚአብሔር አብ፡" ይህ ከንቱ ነው። አያችሁ? ትክክል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንደዚህ ያለ ነገር የለም። ሰው-ሰራሽ የሃይማኖት መግለጫ ነው። ሌላው... ጸሎት ሁሉ እና ነገር ሁሉ ሰው-ሰራሽ ነገር ነው።

110 ዛሬ የእኛዎቹ ፕሮቴስታንቶችን፡ እዚህ ወርደን ካየናቸው፡ ልክ እንደነሱ ተወስደዋል። እና ቢሊ ግራሃም እሁድ እንዳለው፡ "ሰዎቹ ተሳስተው ሳሉ ደህና እንደሆኑ እስኪያስቡ ድረስ በጣም ተሳስተዋል።" ትክክል ነው። እውነቱን ነው። እኔ ግን በዚህ ደስ ይለኛል... እርግጥ ነው ቢሊ ግራሃም መንፈስ ቅዱስን በጆርጅ ጄፍሪስ ስር እንደተቀበለ አውቃለሁ፡ ከዕለታት አንድ ቀን ከዚያ ይወጣል። እግዚአብሔር አሁን እየተጠቀመበት ነው፡ ምክንያቱም ማንም ሊደፍራት የማይችል ያቺን መንግሥትን ሊያናውጥ ስለሚችል ነው። ነገር ግን ከጀርባው የሆነ ነገር እንዳለው፡ ሰብከቱን ማየት ትችላላችሁ፡ ምክንያቱ እነዚህ ባፕቲስቶች አንዳንዶቻቸው እጅ-የሚጨባበጡ ናቸውና። አዎን፡ ወዳጄ!

111 አሁን፡

> ***ሥራህን አውቃለሁ... እና ትዕግሰትህ፡... እንዴት ያን እንደማትችል...***

112 አግኝቼዋለሁ፡ አሁን እንየው...

> ***ሥራህንና፡ ድካምህን፡ ትዕግሥትህንም አውቃለሁ፡... ክፉዎችን*** እንዴት ***ልትሸከም እንደማትችል፡ እንዲሁም ሳይሆኑ፡ ሐዋርያት*** ነን ***የሚሉቱን፡ መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ፡***

113 ሐሰተኞች ሆነው አገኛቸው። ያንን እንዴት አወቁ? ቃል በመጥቀስ አይደለም።

114 ለምሳሌ፡ አንድ ሰው እንዲህ ቢል፡ "መጽሀፍ ቅዱስ በዕብራውያን 13፡8 ላይ እንዲህ ይላል፡ 'ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡'" ሰውዬው ግን "አይ፡ የተአምራት ዘመን'ኮ አልፏል፡" ቢል፡ ሰውዬው ሐሰተኛ ነው።

115 መጽሃፍ ቅዱስ፡ "ንሰሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለኃጢአታችሁ ስርየት ተጠመቁ ካለ፡" መጽሐፍ ቅዱስ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተመሳሳይ ነገር ይናገራል፡ እናም በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የተጠመቁ ሁሉ—በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ እንዲጠመቁ፡ እንዲረጩም አዟቸዋል፡ ወይም የመሳሰሉ ነገሮች ካመጣ፡ ሰውዬው ሐሰተኛ ነው፡ ሐሰተኛ ነቢይ ሆኖ ተገኘ።

116 ስሜቶችን እንዳልጎዳው ተስፋ አደርጋለሁ፡ ግን እንደው... ወንድሜ፡ ጊዜው አሁን ስለሆነ፡ ዕቃ—ዕቃ መጫወት አትችልም፡ ጓንቱን አውልቀህ ወንጌልን ያዘው፡ አየህ? እውነቱ ይህ ነው።

117 አሁን፡ እስኪ ሌላ ነገር አሳዩኝ። ከካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ውጪ አንድ ሰው በኢየሱስ ስም በቀር በሌላ መንገድ የተጠመቀበት፡ አያችሁ፡ አንድ ቦታ ካለ እስኪ አሳዩኝ። ስለዚህ በዚህ መንገድ የተጠመቅክ ከሆንክ በክርስቲያን ቤተክርስቲያን ውስጥ አይደለህም፡ በዚያ ስለተጠመቅክ በካቶሊክ ቤተ

ክርስትያን ውስጥ ነህ። የራሳቸው **የሰንደይ ቪዚተር፡** የካቴኪዝም ሲጠይቅ፡ እንዲህ ይጠይቃል፡ "ፕሮቴስታንቶች ይድኑ ይሆን? " "ብዙዎቹ፡ የእኛ ዓይነት ጥምቀት ስላላቸው እና ወዘተረፈ አዎን፡" ይላሉ። ይላሉም፡ "መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳሉ፡ መጽሐፉ ሲናገር ግን 'በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ' ይላል፡ እኛም ከዚያ ተነስተን 'አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ' በመተካት ወደዚያ ሁሉም ገብተዋል።" በትክክል። አያችሁ? ይህ—የክርስትያን ጥምቀት... አይ—አይደለም፡ የካቶሊክ ጥምቀት እንጂ።

118 አንድ ምሽት፡ "**በክርስትና** ጥምቀት ተጠምቀሃልን" ስል ሰምታችሁኝ ታውቃላችሁን? **የክርስትና** ጥምቀት፡ ክርስቶስ፡ "በኢየሱስ ክርስቶስ፡" እንጂ በአንዳንድ መጠሪያዎች አይደለም።

119 አሁን 3ኛው ቁጥር፡ እሺ፡ 2ኛው እና 3ኛው ቁጥር። አሁን 3ኛው ቁጥር፦

**ታግሠህማል፡** ስለ **ስሜም ብለህ፡ ጸንተህ፡ አልደከምህም።**

120 "ስለ ስሜ።" ትዕግስት እንደነበራቸው አስተውላችኋል? የደከሙት ለምንድነው? ስለ ስሙ። ስሙን በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳጸና አያችሁ? አሁን እዩት፡ እንዴት እንደጠፋ፡ እና ወደ ሌላ ስም እንዴት እንደሄደ በሳምንቱ ውስጥ እናየዋለን። አያችሁ? "**ስለ ስሜ፡ ታግሰሃል፡ ደክመሃል፡ ወዘተረፈ።**" እሱን... የኢየሱስ ክርስቶስን ስሙን ከማንኛውም ቤተ ክርስቲያን፡ እና ከማንም በላይ ከፍ ለማድረግ ስለ ስሙ ደከሙ።

121 መጽሐፍ ቅዱስ በሚለው፡ "ነገር ሁሉ፡" እርሱ ይቅደም፡ "በቃልም ሆነ በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አድርጉት።" ልክ ነው? "በቃልም ሆነ በተግባር የምታደርገውን ሁሉ።" ካጋባህ፡ ሰዎችን አጋባቸው፡ ካልቻልክ፡ በጋብቻቸው የተበላሸ ነገር ካለባቸው፡ በጭራሽ አታጋቧቸው። አያችሁ? "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ባል እና ሚስት እንደሆናችሁ አውጃለሁ፡" ብለህ በነጻነት ማወጅ የማትችል ከሆነ፡ ተዋቸው። እሺ። ልታጠምቃቸው ከፈለግህ፡ በኢየሱስ ስም አጥምቃቸው።

122 የምታደርገውን ነገር በኢየሱስ ስም ማድረግ የማትችል ከሆንክ፡ ተወው! አንድ ሰው "ትንሽ መጠጥ ጠጣ፡" ይልሃል። በኢየሱስ ስም ይህን ማድረግ አትችልም፡ ስለዚህ ተወው! አንድ ሰው "ካርታ እንጫወት፡" ይልሃል። በኢየሱስ ስም ይህን ማድረግ አትችልም፡ ስለዚህ ተወው! በካርታ ጨዋታ ፓርቲህ ላይ፡ የማይረባ፡ አስቂኝ ቀልድ፡ በኢየሱስ ስም መናገር አትችልም፡ ስለዚህ ተወው! አየህ? በኢየሱስ ስም ቁምጣ መልበስ አትችልም፡ ስለዚህ ተወው! መቀጠል እችል ነበር ግን... የምናገረውን ነገር አውቃችኋል። እሺ። ማድረግ አትችሉም። በስሙ ማድረግ የማትችሉት ነገር ሁሉ፡ ተውት! ምክንያቱም፦ "በቃልም ሆነ በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አድርጉት፡" ብሏልና። አሁን፡ ጥሩ ነው።

123 አሁንም እንቀጥላለን... ይህም... እርሱ እንዲህ አዘዛቸው። አሁን ስለ ነቀፌታው በ 4ኛው ምዕራፍ ውስጥ እናገራለሁ... ወይም 4ኛው ቁጥር፡ ማለቴ ነው።

**ነገር ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፡ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና።**

124 አቤት! “የምነቅፍብህ ነገር አለኝ። ታግስሃል፡ ስለ ሰሜ ብለህ አልደከምህም።” ይህ ዛሬ የዚህ ተበርናክል ጥሩ ምሳሌ አይሆንም? አዎን፡ ወዳጄ! “ጥሩ ነበርህ፡ እና ብዙ ትዕግስት ነበረህ፡ ረጅም ጊዜ ችለህ ቆይተሃል፡ ዋናው ነገሩ ግን... ስለ ሰሜም ጸንተሃል። ያን ሁሉ አደንቀዋለሁ። ለ—ለዚያ አመስግንሃለሁ፡ በጣም ጥሩ ነው። ሐዋርያት ነን የሚሉትንና የመሳሰሉትን እንደመረመርካቸው አይቻለሁ፡ ሐሰተኞች ሆነው አግኝተሃቸዋል፡ ከቃሉ ጋር አይሄዱምና። ይህ ሁሉ—አድንቄዋለሁ። ነገር ግን የምነቅፍብህ አንድ ነገር አለ፡ ይህም የመጀመሪያውን ፍቅርህን ትተሃል። ድሮ ለመልካም፡ የጥንት-ዓይነት፡ መንፈስ ቅዱስ ላላቸው ጉባኤዎች የነበረህ ፍቅር ትተሃል፡ እንደው ተራ ወደ ሆነው ነገር ወደ ኋላ ተንሸራተሃል፡ ወደ ‘አባታችን ሆይ... ’” ከንቱነት ነው! አያችሁ?

125 ይህ ሁሉ የማህብረሰብ፡ አንድ ሰው ትልቅ ልብስ ለብሶ በመካከላቸው ይመጣል (ታውቃላችሁ፡ በመዘምራን ውስጥ ለመዘመር እኮ ነው፡ ታውቃላችሁ)፡ መላ ሰውነታቸው እና ጸጉራቸው ሁሉ አሸንክታብ ነው፡ ፊታቸው ሁሉ ሜክ አፕ ሞልቶታል፡ የሚዘምሩት ዝማሬ ምን እንደምላችሁ አላውቅም።

126 እዚህ በቅርብ ጊዜ ነው፡ በኦራል ሮበርትስ ሰብሰባ ባይሆን ኖሮ፡ እንደው ብዙ አንጃ ያስነሣ ነበር። እኔም ያኔ በተዘጋጀው የቢዝነስ ሜን ኮንቬንሽን—በዚያ ነበርኩና... ገና ምንም አልነበረንም... እና ያን ምሽት ሰባኪው እኔ ነበርኩ። በሆቴሉ ውስጥ እዚያው ሊያደርጉት ስላልቻሉ፡ ወደ ኦራል ሮበርትስ ሕንፃ—ወሰዱኝ። እና በኦራል ጥናት ክፍል ውስጥ ቁጭ ብዬ፡ በዚያም ብዙ የጴንጤቆስጤ ልጆች ነበሩ ((ኦህ፡ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች፡ አሥራ ስድስት፡ አሥራ ሰባት ዓመት፡ አሥራ ስምንት) ከሁሉም አይነት በዚያ ቆመዋል፡ ሠላሳ ወይም አርባ የሚያህሉ ሰዎች የሆነ ዓይነት ዝማሬ—ሊዘምሩ ነው... እንደ ቤኪ ያለ ሰው አይነት የመክፈቻው ንግግር የሚመስል ይመስላል፡ እንጃ ብቻ፡ ቻይኮቭስኪ ወይም እንደነዚህ ዓይነት ነገሮች፡ ክላሲካል ዝማሬ አይነት፡ ዝማሬ ይመስላል። እና ወንድሞች ከጉባኤው መባ ለመሰብሰብ፡ ተዘጋጅተዋል፡ ሁሉም ወደዚያ ወጡና እንደ ትንንሽ ኩባያ መሣይ ነገር ያዙ፡ በወንዶቹ እና በሴቶቹ መካከል እየሄዱ፡ ዕውር በመምሰል ቀልዳቀልድ እና የማያስፈልጉ ነገሮች ማድረግ፡ እና ሁሉንም አይነት ንግግር መናገር ጀመሩ። ልጃገረዶቹም፡ የኦራል ህንጻን መቀባት የሚያስችል ቀለም፡ ፊታቸው ላይ ተቀባብተው ነበር። እንደው እራሳቸውን በዚህ መልኩ ሆነው፡ “ጴንጤዎች” ነን ይላሉ። የመጀመሪያ ፍቅራቸውን ትተዋል።

127 ዴቪድ ዱፕሌሲስ ከተናገረው ጋር እስማማለሁ፡ “እግዚአብሔር የልጅ ልጆች የሉትም።” የለውም፡ ጌታዬ! ሜቶዲስት የልጅ ልጆች አላቸው። ባፕቲስት የልጅ ልጆች አላቸው። ጴንጤቆስጤ የልጅ ልጆች አላቸው። እግዚአብሔር ግን ምንም የለውም! እናንተም ወንዶች እና ሴቶች ልጆቹ ናችሁ። አባትህ እና እናትህ መልካም ሰዎች ስለነበሩ መግባት አይቻልህም፡ እነርሱ የከፈሉትን ተመሳሳይ ዋጋ አንተም መክፈል አለብህ። ልክ እንደነሱ መወለድ አለብህ። እግዚአብሔር የልጅ ልጆች በፍፁም የሉትም። ወንድ ወይም ሴት ልጅ ብቻ ናችሁ፡ ቢያንስ፡ የልጅ ልጅ አይደላችሁም፡ ይህ አንድ ነገር እርግጠኛ ነኝ።

128 እዚያ ውስጥ፡ ጥሩ የጴንጤቆስጤ ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን... ወደዚያ ስብሰባ ሄድኩ። አቤት፡ እኔ ስገባ አይተው ሴቶቹ ወዲያ ወዲህ ሲበተኑ

ባያችኋቸው፡ በአጭር ቀሚስ፡ ጸጕራቸው የተላጨ፡ እንደው እንደ ዌነር አይነት፡ እንደምታውቁት፡ አኍል-ልብስ በሚባሉ፡ በዚያ አይነት ልብሶች ውስጥ ተጠቅጥቀው፡ የጴንጤቆስጤ ሴቶች፡ የምንዝር ልብስ ለብሰው ነበር።

129 በፍርድ ቀን ግን፡ መልስ ትሰጡበታላችሁ። በምንዝርና ጥፋተኛ ትሆናላችሁ፡ ኢየሱስም አለ፡ “ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም፡ ያኔ በልቡ ከእሷ ጋር ዝሙትን ሰርቷል።” እራስሽን በዚህ መልኩ በወንድ ፊት የምታቀርቢ ከሆንሽ፡ ጥፋተኛው ማን ነው? አንቺ ወይስ ሰውዬው? ታረሚ! የክፉ ምሳሌ ሁሉ አስወግጂ! አየሽ? ተመልከቺ እንግዲህ።

130 ምንስ ታደርጉታላችሁ? የመጀመሪያ **ፍቅራቸውን** ትተዋል። ኦህ፡ ከበሮ አስይዛችሁ እግዚአብሔርን በጭብጨባ እና በምስጋና ከፍ እንዲያደርጉት ልታዟቸው አትችሉም። ኦህ፡ በፍፁም! ላያቸው ላይ ካባ መሳይ ነገር ደርበው ክላሲካል ዓይነት ይዘፍናሉ። አያችሁ፡ **የመጀምሪያ** ፍቅራቸው ትተዋል። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስትያን ጉዳይ ያ ነበረ። አያችሁ?

131 ከአለም ጋር መመሳሰል ወደዱ። እንደ አለም መልበስ፡ አለምን መምሰል፡ እንደ አለም መንቀሳቀስ ሆነባቸው። የሚወዷቸውን የቴሌቪዥን ሰታር ይኖራቸዋል፡ ታውቃላችሁ፡ እሱን አለማየት አይሆንላቸውም። **ዊ ላቭ ሱዚ** ወይም ሌላ ሌላውን፡ አያችሁ፡ ማየታቸው ግድ ይሆንባቸዋል። እነዚያን ለማየት ከጸሎት ጉባኤዎች እና ከሌላ ነገሮች ይቀራሉ። ቤት ካልቀሩ፡ ፓስተሩን በጩከት በደንብ ያውኩታል፡ ፕሮግራም እስኪተላለፍ ድረስ ወደ ቤታቸው እንዲደርሱ በጊዜ እንዲለቃቸው ይረብሹታል። ከእግዚአብሔር ፍቅር ይልቅ የዓለም ፍቅር ይበልጥባቸዋል!

132 አቤት፡ በጣም ተራ፡ ከመሆናቸው የተነሣ፡ “አሜን!” ማለት አይችሉም። እንደው፡ ይገርማል፡ ሜክ አፑን ያሰለቅቅባቸዋል። አያችሁ? ከእንግዲህ ጥለውታል። ጴንጤቆስጤ ነው። ባፕቲስት አይደሉም። እነርሱ’ማ ከመጀምሪያም ጀምሮ ምንም አልነበራቸውም፡ እነ—ፕሪስባይቴሪያን። እኔ የምለው ስለ ጴንጤቆስጤ ነው። ትክክል ነው። ወንድሜ፡ በጣም እንደሚያሳምም አውቃለሁ፡ ነገር ግን ከዚህ ነገር መወለድ እንፈልጋለን፡ ከመወለዳችሁ በፊት ግን ሞትን ያመጣ ዘንድ ይገባል። አያችሁ? አያችሁ? እውነት ነው። አሁን ግን ይኸው፡ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃል። እ…

133 እግዚአብሔር በዚህ ጉዳይ ላይ **ይህች** ቤተ ክርስትያን የተቃወማት ከሆነ፡ **ያቺን** ደግሞ ይቃወማታል! “የመጀመሪያ ፍቅርህን ትተህ ስለሄድክ፡ የምነቅፍብህ ነገር አለኝ። የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፡ ቅሬታዬ ያ ነው። በአንድ ወቅት ጥሩ ጊዜ ነበረህ፡ አሁን ግን—ዓለም ወደ ውስጥህ እንዲዘልቅ ፈቅደሃል፡ ሰራህም በመጠኑ ተራ እየሆነ ነው። አሁንም ሰሜን ይዘሃል፡ አሁንም ትክክል የሆኑትን ነገሮች ታደርጋለህ፡ እና ብዙ ትዕግስት ወዘተ አለህ፡ ትደክማለህ፡ ልክ እንደ በቅሎ፡ ትደክማለህ ትሰራለህ።”

134 አቤት! አቤት! አቤት! አያችሁ፡ ጸጋ እና እምነት እና ኃይል ትተሃል፡ በሥራ እና በድካም ተክተሃቸዋል። “ይኸውልህ፡ ወንድሞ ብራንሃም ልንገርህ፡ እኔ—የቻልኩትን ያህል መበለት ሴቶች አግዛለሁ።” አዎን፡ ያ ጥሩ ነው፡ ስለዚያ አመሰግናችኋለሁ። ግን የመጀመሪያው ፍቅር የት አለ? ኧሃ-እህ፡ ኧሃ-እህ። ቀድሞ የነበረው ደስታ የት አለ? ዳዊት በአንድ ወቅት “አቤቱ የመዳኔን ደስታ

መልስ፡” ብሎ እንደ ተናገረ። ሌሊቱን-ሙሉ የአዳር የጸሎት ስብሰባዎች፡ እና በጉንጮቻችሁ የሚወርዱ እንባዎች የት ገቡ? አቤት፡ እንደው፡ መጽሐፍ ቅዱስ በብናኝ እና በድር ተሸፍኗል። የድሮ የፍቅር ታሪኮች፡ እና ዜናዎችን ወዘተረፈ ታነባላችሁ፡ በቆሻሻ እንዲጣል እንጂ—እንዲታተም እና እንዲወጣ እንኳን ሊፈቀድላቸው የማይገባቸው ነገሮች፡ እኛ የጴንጤቆስጤ ሰዎች ግን ዝንቦች በቆሻሻ መጣያ እንደሚሰፍሩ አንስተን በላያቸው ላይ ሰፍረናል። ትክክል ነው። አቤቱ ማረን! የሚያስፈልገን፡ ወደ መጀመሪያው ፍቅራችን መመለስ ነው! ወደ ጴንጤቆስጤ መመለስ! አቤት፡ እንደው ከዚያስ ብሄድ ይሻለኛል። እሺ። “የመጀመሪያውን ፍቅር መተው፡” ግን፡ ገብቷችኋል።

135 4ኛው ቁጥር፡ 5ኛ ቁጥር አሁን። ማስጠንቀቂያ፡ 5ኛው ቁጥር፡ ማስጠንቀቂያ፦ “አሰበው እና ንስሐ ግባ!” አያችሁ?

> **እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አሰብ፡**... (ከወዴት መጣህ? ከበዓለ ሃምሳ አሁን ወዳለህበት ወድቀህ፡ ሰተሃል)... **ንስሐም ግባ፡ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፡** (ወደ ጴንጤቆስጤ እንደገና ተመለስ)... **አለዚያ ቶሎ እመጣብሃለሁ፡ መቅረዙንም** ከቦ-ታ-ው **አሰወግዳለሁ**... (ማንን እንደሆነ አይታችኋል፡ አይደል? )... **ንስሐ ካልገባህ በስተቀር ቦታውን።**

136 በሌላ አነጋገር፡ በእግዚአብሔር-የተሞላ ፓስተር ሲኖራችሁ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ከሆነ፡ እናንተ ግን ጣታችሁ መካከል ልታስቀሩት ወዳችሁ፡ እሱን እንዲህ ለመናገር፡ “እንደው፡ የመዘምራን ልብስ ስለ መልበሳችን፡ አንዳች ነገር ከተናገረን፡ ወይም ሜክ አፕ ስለማድረጋችን ከተናግረን፡ እሱን እናወግዘዋለን።” ግድ የላችሁም፡ ከእናንተ በፊት እግዚአብሔር ስራውን ይሰራል። ከእንደዚህ አይነት ነገሮች ጋር ከመስማማቱ በፊት ወጥቶ በመንገድ ላይ ድንጋዮችን ይሰብካቸዋል። እውነትን የሚነግራችሁ ፓስተር ካገኛችሁ፡ እግዚአብሔርን እያከበራችሁ በመንፈስ ልትኖሩ ይገባችኋል፡ ካላመለከው እንደምትጠፋ እያሰብክ፡ እግዚአብሔርን አምልከው። አየህ?

137 ዛሬ ግን ሰዎች እንደሚጠፉ ሆነው ይኖራሉ... ያለው ነገር ይህ ብቻ ነው፡ “ምድር ላይ ኖረን፡ አበቃ።” ይህን ትቶ ወደ ሌላ ሰፍራ የሚሄድ ነፍስ እንዳለን አታስተውሉም። እናንተ ግን መዳረሻችሁን እዚህ አድርጋችኋል፡ አኗኗራችሁ ስራችሁ ሁሉ፡ ቂመኞች፡ እና ከባዶች፡ ወዘተረፈ፡ ከዚያ በኋላም ወደ ቤተ ክርስትያን የምትቸኩሉ ናችሁ። አቤቱ፡ ማረን! አቤት! ታሳፍራላችሁ።

138 በክርስቶስ ስራ ላይ—ነቀፌታ ታመጣላልችሁ። ልክ አይደለምን? እንዲሁ አናደርግምን? ሕገ ወጥ ነጋዴ ቤተክርስቲያንን አይጎዳም፡ **ያ** አይደለም። ቤተክርስቲያንን የምትጎዳው ሴተኛ አዳሪዋ አይደለችም። ቤተክርስቲያንን የሚጎዱ ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች ናቸው። ሕገ ወጥ ነጋዴ እና ሴተኛ አዳሪ ምን እንደሆኑ ይታወቃሉ። እህቶቻችን እንደ ሴተኛ አዳሪ ሲለብሱ ግን፡ ይህ የተለየ ነው፡ ቤተክርስቲያንን የሚጎዳው **ይህ** ነው። ሰውዬው እንደ ሕገ ወጥ ነጋዴ ሲጠጣ፡ እንደው፡ ቤተክርስቲያንን የሚጎዳ፡ ያ ነው። ክርስቲያን ነን ብለው ይናገራሉ ያንን ግን ያደርጋሉና። ሰዎች ያንን ሰም ይፈልጉባችኋል... “የኢየሱስ ክርስቶስን ሰም የሚጠራ ሁሉ ከኃጢአት ይራቅ።” አያችሁ? ከዚያ ራቁ።

139 ኧረ እኛ፡ በጣም ጎደሎ ነን፡ ወንድሞች። እኔ፡ እናንተ፡ ሁላችንም፡ ክርስቶስ እንድንሆን ከሚፈልገን ነገር—ጎድለናል። እናም በዚህ ዘመን በቀላሉ የሚይዘንን ኃጢአት ሁሉ ወደ ጎን የምንጥልበት፡ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግስት የምንሮጥበት ጊዜው አሁን ነው። ሰባኪዎች፡ ወንድሞቼ፡ ይህ ልክ ነው። በትክክል እውነት ነው።

140 "አሰበውና ንሰሐ ግባ፡ ካልሆነ ግን የኮከቡን ብርሃን ከሰፍራው አሰወግደዋለሁ።" ሰፍራው ምንድነው? በቤተክርስቲያን ውስጥ። "ንሰሃ ባትገቡና ወደ ነበራችሁበት ባትመለሱ፡ ፓስተራችሁን ከእናንተ ወሰጄ ከሰፍራው አሰወግደዋለሁ፡ ወደ ሌላ ቦታ አሰቀምጠዋለሁ... የሚያበራ ብርሃኔን በሚያንፀባርቅበት ሰፍራ።" እምም! የከበረ ነገር አልነበረምን?

141 አብያተ ክርስቲያናት ንሰሐ የሚገቡበት ጊዜ አሁን ነው። ጴንጤቆሰጤ እነዚህን የተለሰኑ ሰባኪዎችን ከመድረክ የምታወጣበት በፈንታውም፡ እውነቱን የሚናገሩ የጥንቱ-መንገድ ሰባኪዎችን የምትይዝበት ጊዜ አሁን ነው፡ ቤተ ክርስቲያንን ለምግብ ትኬት፡ ለትልቅ ደሞዝ፡ እና ለሥነ ልቦና፡ እና ለመሳሰሉት ነገሮች፡ ለፈረሰ ግልቢያ፡ ለሾርባ እራት፡ እና ወዘተረፈ ለመጠቀም መዞር አይገባም። ወደ ወንጌል ለመመለሰ ጊዜው አሁን ነው። ምን ያህል ትንሽ ብትሆኑ ግድ የለኝም "ሁለት ወይም ሦሰት በተሰበሰቡበት፡ እኔ— በመካከላቸው እሆናለሁ።"

142 "መጥቼ መቅረዙን ከሰፍራው እንዳልወሰደው፡ ብርሃኑን ያበራ ዘንድ፡ ወደ ሌላ ሰፍራ እንዳልከው፡ ንሰሐ ግቡ።"

አሁን 6ኛው ቁጥር። አሁን እኛ የምንቸገርበት አንዱ ነገር ይህ ነው። እንግዲህ፡ ንሰሐ ካልገባችሁ፡ ይመጣል ፓሰተሩንም ገለል ያደርገዋል።

**ግን ይህ አለህ፡...**

143 አሁን፡ አሰታውሱ። አቤት፡ እንዲያመልጣችሁ አሁን። ሌላውን የቀረውን ሁሉ፡ አሁን እኛ ወዳለንበት... ወደዚህ ዘመን ሰብሰብ የሚያደርገው ይህ ነውና። መጀመሪያ፡ ሁላችሁ ደሰተኞች ናችሁ? [ጉባኤው ሁሉ፡ "ኣሜን።" አለ—አርታዒ።] ትቸኩላላችሁ? ["አይ።"] እሺ፡ ይሁን። እሺ፡ እንግዲያውሰ ትንሽ ታገሱኝ። [አንድ ወንድም፡ "ሌሊቱን ሙሉ ቆይ" አለ።] እሺ.... አመሰግናለሁ።

**ግን ይህ አለህ፡** (ያኔ አንድ ነገር ነበራቸው፡ አይደል? ሌላ፡ ምን ነበራቸው? ) **እኔ ደግሞ የምጠላውን፡ የኒቆላውያንን ሥራ ጠልተሃል።**

144 "እነዚያን የኒቆላውያንን ሥራዎች ጠልተሃል።" ዛሬ እዚያ ላይ ተቀምጬ ጥናቱን ሳዋቅር፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ ነገር ጻፍኩኝ፡ አሁን በደንብ እንድታዳምጡኝ እፈልጋለሁ፡ ሁለት ገጽ ብቻ ናት። 6ኛው ቁጥር፡ ያመሰግናል እንዲሁም ይሰማማል፡ ይህ ማለት፡ እግዚአብሔር እና ቤተ ክርስትያን አንድ ነገር ላይ ተሰማምተዋል ነው፡ እርሱም "ሁለቱ የኒቆላውያንን ሰራዎች መጥላታቸው ነው"፡ በዚህ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረች እውነተኛ ወይን ግንድ፡ እውነተኛዋ የወይን ግንድ፡ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን።

145 አሁን፡ እያንዳንዳቸው ተራ ቤተ ክርስቲያን የሚሆኑበት እና መንፈሳዊያን ቤተ ክርስትያን የሚሆኑበት የየራሳቸው ነገር እንደነበራቸው፡ አሰታውሱ።

እነዚህም በእያንዳንዱ ሪቫይቫል የሚወለዱ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስትያን ውስጥ የሚኖሩት መንትዮች ናቸው። ልክ **በዚህ** ዘመን ጀምረው **በዚህ** ዘመን ያበቃሉ። በመጨረሻም፡ ተራዎቹ በትያጥሮን ዘመን ተቆጣጠሯት፡ ሉተር ግን እንደገና ጎትቶ አወጣት። አሁንም እንደገና ለመውረድ እየተወዛወዘች ትገኛለች። ተራው ኃይማኖት ይታያችኋልን? በዚያ እና በካቶሊካዊነት መካከል ምንም ልዩነት የለም። ሁለቱ ያው ናቸው። ድርጅት የሆነ ሁሉ በዚያ ውስጥ የሚቆጠር ነው። እግዚአብሔር ቤተ ክርስትያኑን አደራጅቷት አያውቅምና። በዚህም ሊሰሩት የሞከሩት ነገር ይህ ነበርና። እና ያ ትክክል ካልሆነ አሁን ተመልከቱት እና እዩት፡ ድርጅት ምን ያህል መርገምት እንደሆነ ብቻ ታያላችሁ። ያ ነገር ለአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስትያን—ለአዲስቷ ቤተ ክርስትያን እንግዳ ነገር ነበረ። አያችሁ?

## ግን... አንተ... ነገር ግን ይህ አለህ፡ እኔ ደግሞ የምጠላውን፡ የኒቆላውያንን ሥራ ጠልተሃል።

146 እውነተኛው የወይን ግንድ የኒቆላውያንን ተራ ተግባር ጠላች፡ እግዚአብሔርም እንዲሁ። በኤፌሶናውያን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥራ የነበረው ነገር፡ በጴርጋሞስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትምህርት ሆነ። በኤፌሶን በመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ይህ ሥራ ነበር፡ በሚቀጥለው ቤተክርስቲያን ደግሞ ትምህርት ሆነ። ይሰማል? አሁን ገብቷችኋልን? በኤፌሶን ሥራ የነበረው ነገር፡ አሁን በጴርጋሞስ ስታዩት፡ ትምህርት ሆነ። እዚህ የጀመረው በትንሹ በህጻን መልክ ነው። አሁን፡ በጥቂት ደቂቃ ውስጥ ምን እንደ ሆነ ወደ ማወቅ እንሄዳለን። የጳውሎስ **ተኩላዎች** እነዚህ ናቸው፡ "የኒቆላውያን ሥራዎች።"

147 አሁንስ ምን... ቃሉን እንቍረሰው፡ ከማለፋችን በፊት ያገኘነውን እንወቀው። **ኒቆላውያን** የሚል ቃል ለእኔ እንግዳ ነው። ስለሆነም የግሪክ መዝገበ ቃላት ሁሉ አመጣሁ። **ኒቆላውያን** የሚል ቃል **ኒቃኦ** ከሚል የመጣ፡ n-i-c-k-o፡ ቆይ፡ እዚህ የጻፍኩት ይመስለኛል፡ n-i-c-k-o፡ ኒቃኦ፡ "ማሸነፍ፡ ወይም መጣል" ማለት ነው። **ኒቆላውያን**፡ "አማኞችን ማሸነፍ፡ ወይም መጣል።" እዚህ ሊሠሩት ይሞክሩት የነበረው ነገር ምንድነው እግዚአብሔር ፓስተሮች የሾመባት ቤተክርስትያን፡ የእግዚአብሔር መንፈስም በስጦታዎች የሚሠራባት የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን፡ ካሃናት፣ ቢሾፖች፣ ጳጳሳት፣ ወዘተረፈ እንዲኖራቸው በሚፈልግ አዲስ ነገር ለመተካት፡ የጀመሩት ትምህርት ይዘው ነበር። ይህም፡ እግዚአብሔር ራሱ፡ እጠላዋለሁ ብሏል! ዛሬም ይጠላዋል። **ኒቆላውያን**፡ **ኒቃኦ**፡ ምእመናንን "ማሸነፍ፡ ወይም መጣል" ነው። **ምእመናን** ማለት "ቤተ ክርስቲያንን ነው።" ምእመናን ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች ስንቱ ያውቃል? እሺ፡ "መጣል፡ ማሸነፍ፡ ወይም የምእመናንን ስፍራ መውረር።"

148 በሌላ አገላለጽ፡ ቅድስናን ሁሉ፡ ኃይልን ሁሉ ከቤተክርስቲያን ወስዱ እና፡ ለካህናቱ ስጡት፡ "ጉባኤው በፈለገው መንገድ ይኑር፡ ካህኑ ግን ቅዱስ ነው።" ድንቅና ተአምራት ይከተላቸው የነበሩትን ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ከላያቸው ላይ በመለየት፡ ያንንም ለይተው ቅዱስ የክህነት ስርዓት ሰጧቸው። መንፈስ ቅዱስን አስወግደው በክህነት ሰርዓት ለወጡት። ምን እንደነበረ አያችሁ? ይህ ነበረ... በመጨረሻ እንዲህ ሆነ... በዚህች ቤተክርስትያን፡ ሥራ ነበር፡ **እዚህ** ላይ ግን ትምህርት ሆነ፡ ከዚያ በኋላ ቲያጥሮን፡ ሁሉንም ተቆጣጠረች። ሉተር

ሲወጣ፡ በዚያ መንገድ መቆየት አልቻለም፡ ወደ ኋላ ተመለሰ እና እንደገና ተቆጣጠረ፡ ጳጳሳት፣ ካርዲናሎች፣ ሊቀ ጳጳሳት። በአለም ላይ እሱ ራሱ ካልሆነ በቀር የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን የሚመራ ማን ነው? አሜን! ዊው! አሁን ሃይማኖት ተሰማኝ። መንፈስ ቅዱስ የተላከው ቤተክርስቲያንን እንዲገዛ ነው፡ ሰባኪው ብቻ አይደለም፡ መላው ጉባኤ እንጂ!... ሰባኪው ብቻ ይቀደስ፡ አይ፡ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ አላት።

149 በሱ ፈንታ፡ መንፈስ እንዲሰራው ከመጠበቅ ይልቅ፡ ትንሽ ህብስት እና ብስኩት፡ እንዲሁም በጥቂት ወይን ተኩት፡ መጠሪያውም “**ቅዱስ ቁርባን** አሉት ‘መንፈስ ቅዱስ’” ማለታቸው ነው። ምንም ቢሆን ትንሽ ቁራሽ ብስኩት እና ወይን እንዴት መንፈስ ይሆናል? እንግዲህ፡ ይህ—እንዲህ ከሆነ’ማ፡ የሐዋርያት ሥራ 2 ማንበብ ያለባችሁ እንዲህ ነው፡ “የበአለ ሃምሳው ቀን በደረሰ ጊዜ፡ አንድ ሮማዊ ካህን ከመንገድ ላይ ወጥቶ፡ ‘ምላሳችሁን አውጡ’ አላቸውና ህብስቱን አጎረሳቸው፡ ወይኑንም ጠጣና፡ ‘አሁን መንፈስ ቅዱስ ተሞልታችኋል፡’ አላቸው።” አሁን፡ ይህ ሰቅጣጭ እንደሆነ እናሰባለን። እንዲሁም ነው።

150 ከዚህ ወረድ እንበልና፡ እኛን ባብቲስቶችን እንውሰድ፡ እኔ ራሴ የተሾመ የባብቲሰት አገልጋይ ነበርኩና። ኧሃ-ሃህ። እህም? ሜቶዲሰቶችስ፡ እንዴት እናደርገዋለን? “‘ኢየሱሰ ክርሰቶሰ የእግዚአብሔር ልጅ ነው’ ብለህ ከመሰከርክ፡ ድነሃል።” ዲያብሎሰም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምኖ፡ ይንቀጠቀጣል፡ ምናልባትም ከብዙ የቤተ ክርሰቲያን አባላት በበለጠ ያምናል። ዲያቢሎሰም ያምናል ይንቀጠቀጥማል፡ ምክንያቱም እንደተወገዘ ያውቃልና።

151 አሁን ደግሞ የሜቶዲሰት መንገድ እንያቸው፡ እነዚህም—እንደሚሉት “ዮሐንሰ ረጨ እንጂ፡” “አላጠመቀም፡” ይላሉ። እንዲህም ይላሉ፡ “ያኔ በዚያ አገር ላይ ብዙ የጉድጓድ ኤሊዎች ሰለነበሩ፡ ውኃው—የሚወጣው ከእነዚያ ጉድጓዶች ነበረ። እና በሙሰል ዛጎል የኤሊው ጉድጓዶች ይቆፈርበታል።” ሰብከታቸው ይህ ነበር። “እና በኤሊው ቅርፊት፡ ወይም በሙሰል ዛጎል፡ ከኤሊው ጉድጓድ ውኃ ይቀዳሉ፡ ከዚያ ህዝቡ ላይ ይረጩት ነበር።” ከንቱነት! ኡህ፡ ወንድሜ!

152 እሺ፡ በዚህ ደግሞ እንየው፡ “በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፡ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው፡ በአንድ ሰፍራ ነበሩ። ፓሰተሩም ወርዶ ጥሩ ሰብከት ሰበከ፡ እንዲህም አለ፦ ‘በኅብረት ቀኛ እጅ ጨብጡኝ፡ ሰማችሁም በመጽሐፉ ላይ እንጽፈዋለን።’” ምንም ትክክል አይመሰልም፡ ይመሰላል’ዴ? ሊመሰላችሁ ይችላል... እንዲህ አይነቱ ነገር በአልማናክ መካከል እንኳን አታገኙትም፡ ከዚህ በተሻለ መልኩ ያውቁታልና። ከዚህ ነገር ይልቅ የአሮጉቶች **ሴቶች የአልመኒክ የልደት ቀን** እጅግ ትክክል ነው።

153 እሺ፡ ይህ ሁሉ፡ ያመጣው ምንድነው? ኒቆላውያን መጻሕፍትን የሚያጣምሙ ብዙ ሰዎች ሰላመጣ ነው፡ በዚያም እግዚአብሔር የማይንቀሳቀሰበት የሐይማኖት ተቋም አሰራር አሰተዋወቁ። ወዲያው ሞቱ! ሰለዚህም ሲናገር፡ “ሞተህማል! ህያው እንደመሆንህ ‘ሰም’ አለህ፡ ሞተህማል! አለው” ብዙዎቹ፡ ሞተዋል፡ ነገር ግን አያውቁትም።

154 እኔ እና ወንድሜ ህጻናት ሳለን፡ እዚያ ማዶ፡ ዓሣ እናጠምድ ነበር። እና ስናፒንግ ተርትል የተባለ ኤሊ ያዝኩና፡ ጭንቅላቱ ቆረጥኩት፡ ከወጥመዱ አላቅቄው፡ ምንም ማድረግ ስላልፈለአግኩት፡ ዳርቻው አጠገብ ጣልኩት። ታናሽ ወንድሜም መጥቶ፡ "ቅድም የያዝከው ምን ነበር፡" አለኝ?

"ስናፒንግ ተርትል ነው፡" አልኩት።

"ታዲያ ምን አደረግከው፡" አለኝ?

"ወድቋል፡ **እዚያ** ጥዬዋለሁ፡ ጭንቅላቱ **እዚያ** ነው፡" አልኩት።

ወደዚያም ወጣና፡ "ሞቷል እንዴ፡" አለኝ?

እኔም "አዎን! ጭንቅላቱ ከሰውነቱ ከተለየ፡ መሞት አለበት፡" አልኩት።

155 ከዚያም ዱላ አነሳና፡ የኤሊውን ጭንቅላት ወደ ወንዙ ወይም ወደ ውኃው ውስጥ ለመወርወር ፈለገ፡ ፈልጎ... እጁን መዘርጋት ጀመረ። እሱም በዘረጋት ጊዜ፡ ኤሊው ነከሳት። ለአንድ ለሁለት ሰዓታት መንከስ እንደሚችሉ፡ ታውቃላችሁ። እና ወደ ኋላው ፈንጠር አለና፡ "ሄይ! 'ሞቷል' አላልከኝም ነበር'ዴ፡" አለኝ።

እኔም "ሞቷል፡" አልኩት።

"እንዴ፡ መሞቱን አላወቀም'ዴ፡ አላወቀውም።" አለኝ።

156 ስለዚህ ብዙ ሰዎችም እንደዚህ ናቸው፡ ሞተዋል ግን አያውቁትም! ኒቆላውያን! ኦህ፡ ማይ! ኦህ፡ "አንተም ትጠላዋለህ፡" አለ። እነዚህን ቅዱስ ካህን፣ ቅዱስ ካርዲናል፣ ቅዱስ ቢሾፕ በሙሉ እየወሰድኩ ነው።

157 አንዳንዶቻችሁም ጴንጤዎችም፡ "ታላቁ ሊቀ ሊቃውንቱ፡ ይምጣ። የበላይ ጠባቂው፡ እዚህ የፈውስ አገልግሎት ማድረግ የሚገባችሁ መሆኑን እና አለመሆኑን እርሱ ይነግራችኋል። ሃ፡ ሃ።" ሃሌ ሉያ! ይሁን አይሁን የሚለን መንፈስ ቅዱስ፡ ራሱ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቃል ነው።

158 "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ጥምቀት 'በኢየሱስ ስም' እንደሚያስተምር እናምናለን፡' የበላይ ጠባቂው ግን፡ በቤተ ክርስቲያናችን ይህ ከጀመርን፡ ሁላችንም እንደሚያባርረን ተናግሯል።" ትክክል ነው። ቀጥሉበት። እዚያ ከምባረር እዚህ ብባረር ይሻለኛል። ስለዚህ፡ **ከዚህም** አንዳች ብታገኙ፡ አንደው፡ ከዚያ መባረራችሁ የማይቀር ነገር ነው፡ እንግዲያውስ እዚህ ቢያባርሯችሁ ይሻላል። እዚህ ወደ ውጭ ከተባረራችሁ፡ በዚያ ወደ ውስጠኛው ትባረራላችሁና። ስለዚህ ያው ስለሆነ፡ ጸንታችሁ ብትይዙት ይሻላል።

159 መቃናት ይገባናል። ኦህ፡ ማይ፡ ወንድሜ ሆይ፡ ይህ ወሳኝ ነገር ነው። ይህ ነገር ማስተካከል ይገባናል። እግዚአብሔር መሠረት መጣያ ካላገኘበት በቀር ቤተ ክርስቲያን ሊኖረን በፍጹም አንችልም። ቤተክርስቲያኑን በከንቱ ነገሮች ላይ ፈጽሞ አይገነባትም። የሚመጣው በቃሉ ላይ ብቻ ነው፡ በቃሉ ላይ ካልመጣ በሌላ ነገር ፈጽሞ አይመጣም።

160 በቅርቡ፡ አንድ ሰው፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ወደ ቻታኑዋ፡" ወደዚያ ውጣ፡ አለኝ። እስኪ ቻታኑዋ የነበራችሁ ሰንቶች ናችሁ? እንዴ፡ ተመልከቱ፡ የቤተ ክርስትያኒቱ አንድ ሶስተኛ ቻታኑዋ ነበረ። በዚያም... ያኔ፡ ሰውዬው ከከሰዓት ላይ ወጣና፡ እኔ ራሴ ስለጉዳዩ እንደማውቅ ሳታውቁ፡ ሁላችሁም ሰምታችሁታል።

እግዚአብሔር እዚያ የሚናገሩትን እዚያ ክፍል ውስጥ ሊገልጥ ችሏል፡ እና፡ ይህን እንዳደረገም፡ ታውቃላችሁ። ወደዚያ ወጣና፡ እንዲህ አለ፡ “እንግዲህ፡ ስለ ወንድም ብራንሃም፡ ኦህ፡ እርሱ የጌታ ባርያ ነው። እሱ የተቀባ ነቢይ ነው፡ መንፈሱ በላዩ ሲመጣ፡ በእርግጠኝነት ይገለጥለታል፡ እግዚአብሔር ምን እና ምን እንደሚሆን ይነግረዋል፡ ቲኦሎጂውን ግን፡ ያንን አትሰሙ።”

161 እንዴት ያለ ብልሹ አሳብ ነው! ሰው እንዴት እንዲህ ይላል! ለምን፡ እኔ'ኮ... እንዴ፡ የተከፈለ ባቄላ ከቡና መለየት የማትችሉ ከሆናችሁ፡ ታዲያ—የበለጠ ማወቅ ይጠበቅባችኋል። እንደዚህ ያለ ነገር እንዴት ማሰብ ይቻላል? ለምን? ለምን ቢባል፡ **ነቢይ** የሚለው ቃል ራሱ “የቃሉ መለኮታዊ ገላጭ” ማለት ነው። ምን ብትሆኑ ነው... ? “የጌታ ቃል ወደ ነቢዩ ይመጣልና።” እነርሱ ራሳቸው እንጂ፡ አንድም ቀን ስለራሴ ነኝ ብዬ አላውቅም። ይሁን እንጂ ተመልከቱ። አያችሁ?

162 ሰው እንዴት፡ ቤተ ክርስትያናቸው ከዚህ ጋር ስለማትስማማበት ብቻ፡ ትንሽ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ለመጠበቅ፡ እንደ ዔሳው፡ ስለማይረባ ምስር ወጥ ብኩርናችሁን እንዴት ትሸጣላችሁ፡ እናንተ ጎሰቋሎች ግብዞች! አዎን። ለማይረባ ምስር ወጥ ብኩርናችሁን ሸጣችኋል፡ እግዚአብሔር ለሚጠላው፡ ለማይረባ የሐይማኖት ተቋም ለማይረባ ድርጅት። አስታውሱ፡ “ድርጅት፡” ብትሉት፡ እግዚአብሔር ይጠላዋል! ወንድሞችን ያለያየ፡ እና የፈራረሰ ነገር ይህ ነው... ዛሬ ማታ ብዙ ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት እና ፕሪስባይቴሪያን፡ በእግዚአብሔር ማዕድ ዙሪያ ኅብረት እንዲኖራቸው ይወዳሉ። እንዲህ ካደረጉ ግን፡ ገና ይህን ማድረግ የጀመሩ ለታ ወዲያው ይባረራሉ። ይህ ትክክል ነው።

163 “እማማ የእነዚህ አባል ናት፡” እንደው ከጅምሩም የልጅ ልጆች ናቸውና። ኦህ፡ ማይ! የእማማ አባል መሆን አይገደኝም፡ እማማ በዘመኗ በበራው ብርሃን ሁሉ ኖራለች፡ እናንተ ግን በሌላው ዘመን ውስጥ ናችሁ።

164 ሳይንስ በአንድ ወቅት፡ ከሶስት መቶ ዓመታት በፊት፡ በዓለም ዙሪያ ኳስ በማሽከርከር አረጋግጧል፡ እንዲህ ብለዋል፡- “የትኛውም ተሽከርካሪ በሰዓት ሠላሳ ማይልን አስፈሪ ፍጥነት ቢበር: ስበት ከምድር ላይ ያነሳው እና ወደ ጠፈር ያወጣው ነበር።” ዛሬ ሳይንስ ያንን ያምናል ብላችሁ ታስባላችሁ? አሁን በሰዓት ዘጠኝ መቶ ሺ ማይሎች እየበረሩ ነው። ድሮ የተናገሩትን ለማየት ወደኋላቸው ዞር አይሉም፡ ወደ ኋላቸው ዞር የሚሉት፡ ወደፊት የሚመለከቱትን ለማየት ነው።

165 ቤተክርስቲያን ግን ዌስሊ የተናገረውን፡ ሙዲ የተናገረውን፡ ሳንኪ የተናገረውን ለመመልከት፡ ሁል ጊዜ ወደ ኋላ ማየት ትፈልጋለች። “ለሚያምኑ ሁሉ ይቻላል፡” ወደ ፊት እንመልከት! በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደ ኋላ የተመለከተች ብቸኛ... ምን ዓይነት እንስሳ ሁልጊዜ ወደ ኋላ እንደሚመለከት ታውቃላችሁ? ከፍጥረት ሁሉ ዝቅተኛ ህይወት። ከሚንቀሳቀሱ ፍጥረታት ሁሉ ከሁሉ ዝቅተኛ ህይወት ስንቶች ታውቁታላችሁ? እንቁራሪት። እንቁራሪት በጣም ዝቅተኛው ህይወት ሲሆን፡ ሰው ከፍተኛው ህይወት ነው። እንቁራሪት ወደ ኋላው ያያል። ያንን ዝቅተኛ ህይወት አይመቸኝም። : ታምኜ፡ እርሱ ብርሃኑን ባበራ መጠን፡ እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን መመላለስ እፈልጋለሁ፡ አሜን።

166 አንድ ጊዜ ኬንታኪ ውስጥ ስብሰባ እያደረግሁ ነበር፡ አንድ ሽማግሌ ወጣና፡ “ኦህ፡ ያ ፈውስ የሚሉት ነገር አላምንበትም፡” አለ።

“ይሁን፡ ችግር የለም፡ አሜሪካዊ ስለሆንክ ነው፡” አልኩት።

“እኔ—ራሴ ካላየሁት በቀር ምንም አላምንም፡” አለ።

“ይሁን፡ ችግር የለውም፡” አልኩት።

“አሁን፡ እኔ ከአንተ ጋር ምንም ችግር የለብኝም፡የምትናገረው ነገር ግን—አላምንም፡” አለኝ።

“አሜሪካዊ መብትህ ነው፡ ግዴታ የለብህም፡” አልኩት።

እንዲህ አለ፡ “አሁን፡ በግልፅ በአይኔ ካላየሁት በስተቀር ምንም አልቀበልም።” እምም!

“እንግዲህ፡ ምናልባት እ... ጥሩ—ጥሩ ነው፡ ከሚዞሩ መሆን አለብህ” አልኩት።

“አይ፡ እኔ ከኬንታኪ ነኝ፡” አለኝ። ዊው!

“በጭራሽ ከኬንታኪ አትመስልም፡” አልኩት። “ግን፡ ለማንኛውም፡” “አንተ... የምታስበው እንደዛ ነው፡ ቀጥልበት፡” አልኩት። እርሱም እንዲህ አለ—እንዲህ አለ... እኔ እንዲህ አልኩት፡ “ወደ ቤት በየት በኩል ትሄዳለህ? ”

167 “ኮረብታውን አቋርጬ እሄዳለሁ። የምኖረውም በዚያ ነው... እሺ፡ ከእኔ ጋር እንሂድ።” ጥሩ ሰው። “ወንድም ብራንሃም፡ ወደ ቤቴ አብረን እንሂድ፡ ሌሊቱን በዚያ ታድራለህ፡” አለኝ።

“ብችል፡ ደስ ይለኛል ወንድሜ፡” አልኩት። ይሁን እንጂ፡ “ከአጎቴ ጋር ወደዚህ እሄዳለሁ፡” አልኩት። እርሱም አለ... እንዲህ አልኩት፡ “እየነዳህ ለመሄድ ፈልገህ ነው? ”

እርሱም፡ “አይደለም፡ በዚያ በኮረብታው በኩል እወርዳለሁ፡ በዚህ መንገድ ወደ ላይ፡ ከዚያ ወደ ታች፡ እና ወደ ላይ፡” እንዴት እንደሆነ ታውቁታላችሁ።

እኔም አልኩት፡ “ታዲያ፡” አልኩት፡ “እንዴት ትደርሳለህ? ”

“ያንን መንገድ እይዛለሁ፡” አለኝ።

“እንዴት፡” አልኩት፡ “እጅህን እንኳ ከፊትህ'ኮ አይታይህም፡” አልኩት። “ታዲያ እንዴት ትደርሳለህ? ”

“ፋኖስ ይዣለሁ!” አለኝ፡

እኔም፡ “እንዴ፡ እንዴት ታደርጋለህ... ምን ታደርገዋለህ፡ ፋኖስ ለኩሰህ ትጓዛለህን? ”

“አዎን፡ ጌታዬ፡” አለኝ።

እኔም “ፋኖሱን ስታበራው፡ **እንዲህ** ከፍ አድርገህ ትይዘዋለህን? ቤትህን ማየት ስለፈለግኩ፡” አልኩት።

“ልታየው አትችልም፡” አለኝ።

“ታዲያ ወደዚያ እንዴት ትደርሳለህ? ” አልኩት፡

“ኦህ፡” አለ፡ “ፋኖሱን አበራዋለሁ፡ በዚያም ሰራመድ፡ በዚያ... በብርሃኑ ልክ እጓዛለሁ... ”

እኔም “እውነቱ ይህ ነው። አሜን፡ በብርሃን ተመላለስ፡” አልኩት።

168 ጉዞህን ቀጥል! እንዳታቆም፡ አትጠፋም። የዳናችሁ ከሆናችሁ፡ ወደ ቅድስና ተጓዙ። “እንዴት እንደርሳለን? ” ብላችኋልን፡ ጉዞአችሁን ቀጥሉበት። “የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የማገኘው ከቅድስና በኋላ ነውን? እንዴት አገኘዋለሁ? ” በብርሃን ውስጥ መሄድህን ብቻ ቀጥል። “ምልክቶች፡ ድንቆች፡ እና ተአምራት ናቸውን... ? ” በብርሃን ውስጥ መሄድህን ብቻ ቀጥል። አያችሁ? ዝም ብላችሁ ቀጥሉ! አንድ እርምጃ በተራመዳችሁ ቁጥር ብርሃኑ ከፊታችሁ ይራመዳል፡ ሁል ጊዜ ከፊት ነውና። ይመራል እንጂ፡ አይገፋም። ብርሃን ነው። ኦህ፡ ስለሱ እጅግ ደስ ይለኛል። እናንተስ? እርሱ ብርሃን ነው፡ ጨለማም በእርሱ ዘንድ የለም።

169 “የኒቆላውያንን ሥራ ጠልተሃልና።” አስተምህሮ ሆነ። አሁን ጳውሎስ ያረገውን እንመልከት... አሁን፡ የማን ቤተ ክርስቲያን ነው... ይህንን ቤተ ክርስቲያን የመሰረተው ማን ነው? ኤፌሶን፡ ጳውሎስ ነው።

170 አሁን ወደ ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 20 እንመለስ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 20 ላይ፡ ጳውሎስ እነየው... ጳውሎስ ነቢይ ነበር ብላችሁ ታምናላችሁ? በእርግጥ፡ ነበር። ያለጥርጥር፡ ነብይ ነበር። በዚያ በሌሊት ራዕይ በባሕር ማዕበል ሲናወጥ፡ ወዘተረፈ ትዝ ይላችኋል? ያንን፡... እና ሌላው ሁሉ። አሁን ደግሞ 20ኛው ምዕራፍ የቅዱስ... የ-... ሐዋርያት ስራ፡ አሁን ከቁጥር—27ኛው አካባቢ እንጀምር፡ አሁን ሲነበብ በደንብ ተከታተሉ። አሁን፡ ይህ ጳውሎስ ነው፡ ነብይ ነው፡ ወደፊት ሊሆን ያለው እየተናገራቸው ነበር።

**የእግዚአብሔርን ምክር** ሁሉ **ነግሬአችኋለሁና ምንም አላስቀረሁባችሁም።**

171 ያ የተባረከ ሰው! አቤት፡ በዚያ ቀን ቆሜ የሰማዕቱ አክሊል በራሱ ላይ ሲቀመጥ ማየት እፈልጋለሁ። እንባን ማፍሰስ የምችልበት አጋጣሚ ካለ፡ ያኔ አነባለሁ። ጳውሎስን እያየሁ፡ ዕልል እላለሁ።

> ታላቁ ሐዋርያ፡ ቅዱስ ጳውሎስ ሰናየው፡
> መጎናጸፊያው ከብርሃን የተሰራ ውብ ድንቅ ነው፡
> ዕልልታ ይሆናል አንድ ቀን
> ሁላችንም በዚያ ተገኝተን። (እናንተስ? )

172 አሁን፡-

**... የእግዚአብሔርን ምክር** ሁሉ **ነግሬአችኋለሁና... ምንም አላስቀረሁባችሁም።**

173 ልክ ነው? እንግዲህ ክርስቲያኖች ሆይ ይህን ተመልከቱ፡ የሆነ ነገር እጠይቃችኋለሁና። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሳይሆን በሌላ መንገድ ተጠምቀው የነበሩትን እነዚያን ሰዎች እንደገና እንዲጠመቁ ያዘዛቸው ሰው ማን ነበረ? [ጉባኤው “ጳውሎስ፡” ነው አለ።—አርታዒ] ምክሩን ሁሉ ሰበከላቸው። ልክ ነው? ኦህ? ጳውሎስ ምን አላቸው... ባልሳሳት

ይመስለኛል... ተሰሎንቄ 1ኛው ምዕራፍ ከቁጥር 8 ይሁን አይሁን አሁን እርግጠኛ አይደለሁም። "እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ የመጣ መልአክ ሌላ ወንጌል ቢሰብካችሁ፡ መልአክ ከሰማይ ወርዶ ከዚህ የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ" (ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ዳግመኛ እንዲጠመቁ ከማዘዝ፡ እና ጳውሎስ ከሰበከው ወንጌል በቀር)... "ከሰማይ የመጣ መልአክም ቢሆን" (እንኳንስ... ቢሾፕ ወይም፡ ካርዲናል ይቅርና፡ ወይም ዋናው አስተዳዳሪ፡ ወይም ፓስተር፡ ወይም—ወይም ሌላው ይቅርና)... "መልአክ ከሰማይ ወርዶ ሌላ ወንጌልን ቢሰብክ፡ የተረገመ ይሁን።" ትክክል ነው። ልክ ነው? የተናገረው፡ በገላትያ 1:8 ነው። አሁን ትዝ አለኝ። እሺ፡ መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ ገላትያ 1:8 ነው፡ ጳውሎስ የተናገረውን ተመልከቱ።

174 አሁን፡ እዚህ ላይ እንዲህ ይላል... አሁን 27ኛው፡ 27ኛውን ቁጥር እንደሆነ አምናለሁ፡

**የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁና... ምንም አላስቀረሁባችሁም።**

175 አሁን ይህ ምን እንደሆነ ስሙት... ይህ ትንቢት ነው፡

**በገዛ ደሙ የዋጃትን፡ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ፡ መንፈስ ቅዱስ... እናንተን... ጳጳሳት አድርጎ፡ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና፡ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።**

176 የዋጃት ማን ነው? ደሙ የማን ደም ነበር? መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ደም እንደሆነ ተናግሯል። እግዚአብሔር፡ በገዛ ደሙ። ልክ ነው?

**... በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን መግቡ።**

177 መጽሐፍ ቅዱስ ድንናል ያለው በእግዚአብሔር ደም ነው። ይህን ያውቁ ኖሯል? ያለጥርጥር፡ አድኖናል። እሺ፡

... **በገዛ ደሙ የዋጃትን።**

**ከሄድሁ በኋላ፡ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች፡ እንዲገቡባችሁ አውቃለሁና።**

**እናንተም ለራሳችሁ...** (ንቁ፡ ሰውዬው በዚያ አልፎ በማየትያ ነገር እየመጣ እንዳለ ማየት ይችላል።) ... **ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ** ዘንድ፡ **ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች፡ በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ።**

178 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] ከብዙ ዓመታት በኋላ... ድርጅት ለመፍጠር የሚፈልጉ የሰዎች መንጋ መንፈስ ቅዱስን እና ቅድስናውን ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን—አስወግደው፡ በኤጲስቆጶሳትና በሊቃነ ጳጳሳትና በካህናት ላይ አኖሩት፡ ይህም... እነርሱ ቅዱሳን ተደርገው፡ ጉባኤው ግን በዘፈቀደ—እንደወደደ እንዲኖር ነው። ሰዎች ለካህናት ገንዘብ ይከፍላሉ እነርሱም ከገሃንም ፍትሃት ጸሎት፡ እና ልዩ ልዩ ነገሮች ያደርጉላቸዋል። ኒቆላዊነት ማለት ይህ ነው! እግዚአብሔርም አለ፡ "እኔ እጠላዋለሁ!" አሁን ተከታተሉ።

"እሺ አንተ፡ 'እግዚአብሔር ይጠላዋል' ብለሃልና፡ እስኪ እንየው? "

179 እሺ እንዲሁ ከሆነ እንየው፡

**ነገር ግን ይህ** አለህ፡ **እኔ ደግሞ የምጠላውን፡ የኒቆላውያንን ሥራ ጠልተሃልና።**

180 እግዚአብሔር ድርጅትን ይጠላል። ልክ ነው? አሁን በትክክል ምን ሊያደርጉ እንደነበሩ ተመልከቱ፡ ምን እንዳደረጉ አይታችኋል። አሁን በቤተክርስቲያን ዘንድ ያንን ካላደረጉ ተመልከቱ። ድርጅትን ይጠላል!

**መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ** ያለው **ይስማ፡...**

181 የጳውሎስ **ተከላዋች**፡ አሁን "ኒቆላውያን" ሆኑ። ለአዲስ ኪዳን ትምህርት እንግዳ የሆነ ክህነት፡ እንደ ሌዋዊያን የሆነ ክህነት ለመመስረት እየሞከሩ ነበር። አሜን! **ኒቃኦ** የሚለው ቃል፡ የግሪክ ቃል **ኒቃኦ** ማለት "ማሸነፍ፡ ድል መንሳት" ማለት ነው። ማንን ድል መንሣት? ምእመናንን፡ መንፈስ ቅዱስን። ከሞት የተነሣውን በአማኞች መካከል በምልክቶችና በድንቆች የሚመላለሰውን ጌታ ኢየሱስን ከቤተክርስቲያን አውጥተው፡ በሰዎች ምርጫ ጳጳስ ወይም ካርዲናል፡ ወይም አስተዳዳሪ፡ በመተካት መንፈስ ቅዱስ ከአማኞች ነጥቀው ሊቃውንት ብለው ለሚጠሩት ለሰዎች ስርዓት እንዲገዙ ያደርጋሉ፡ **ፓስተሮች** ትርጉሙም "እረኞች፡" እንዲሏቸው ሳይሆን፡ **አባት** ብለው እንዲጠሯቸው በአማኞች **ላይ** ይሾሟቸዋል፡ ኢየሱስ ግን "በዚህ ምድር ላይ ማንንም **አባት** አትበሉ፡" ብሎናል። ያንን ክፉ ነገር አያችሁት? እኛስ ምን አደረግነው?

182 አቤት፡ ማቆም በቻልን! እነዚህ ሁሉ ምሽቶች እንደዚህ ባይዙን ጥሩ ነበር፡ ነገ ምሽት ራዕይ ምዕራፍ 12 ላይ ሰብኬ አሮጊቷ አመንዝራ ሴት፡ ጋለሞታይቱን አሳያችሁ ነበር። ይህም... እንዲህ የተባለችበት ምክንያት... በእግዚአብሔር ፊት፡ ዝሙት ሠርታ፡ ራሷን መበለት ብላ ስለጠራች፡ እና የጋለሞታዎች እናት ስለሆነች ጭምር ነው። ልክ ነው ወይ? ያ፡ ሮም እንደሆነ እናውቃለን፡ ምክንያቱም በሰባት ኮረብቶች ላይ የተቀመጠች፡ እንደው ሌላ ነገርዋ ሁሉ በትክክል፡ በእሷ ውስጥ ያለው ሰው እና የአውሬው ቁጥር፡ ወዘተ። ከቀደሙት ትምህርቶቻችን ማን እንደሆነች፡ ሁላችንም እናውቃለን። የሚያሳዝነው ግን፡ የጋለሞታዎች እናት መሆኗ ነው። የእርሷ ጅማሬ እዚህ ጋር ነው፡ እንደ ክርስትያኖች በሮም ተሰብሰበው፡ ክርስቲያን-ተብዬዎች ሆኑ።

183 ተከታተሉ! በትክክል ማሳየት እንድችል እግዚአብሔር ይርዳኝ! በእንደዚህ አይነት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ ብዙ ክርስቲያኖች። ከመንገድ ወጥተው፡ ተራ እና፡ ግድ የለሽ ሆኑ፡ የራሳቸውን ድርጅት አቆሙ። ከዚያም በጨለማው ዘመን፡ ከመንግስት ጋር፡ አንድ እንድትሆን አደረጉ። መንግሥት እና ቤተ ክርስቲያን አንዲት ምን ሆኑ? አንዲት የክርስቲያን ቤተክርስቲያን፡ "ቅድስት ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን" ተባለች፡ (**ካቶሊክ** የሚለው ቃል፡ የቃሉ ትርጓሜ "ዓለም አቀፋዊት") ማለት ነው፡ "ታላቋ ዓለም አቀፍ የክርስቲያን ቤተክርስቲያን።" በልሳን የሚናገሩትን፡ የሚጮኹትን፡ የታመሙ የሚፈውሱ ሰዎችን፡ እና ወዘተ "መናፍቃን፡" ብለው ሰም አወጡላቸው። በመጨረሻም ካቶሊካዊነትን አልቀበልም ብሎ፡ በዚያ መንገድ ሲያመልክ የተያዘ ማንም ሰው ወደ አንበሶች ጉድጓድ እስኪጣል ድረስ፡ እጅግ አስጨናቂ አደረጉት። ይህ ሁሉ

በዚያ መከራ ውስጥ ለብዙ መቶዎች ዓመታት እንዲሁ እየቀጠለ ሄደ። ያቺ ቤተ ክርስትያን ግን በፍጹም አልሞተችም። እግዚአብሔርም እስከ ፍጻሜ ትኖራለች የሕይወትን አክሊልም ይሰጣታል ብሏታል። እሷን መግደል አትችሉም። እና በመከራ ዘመናት አለፈች።

184 ከዚያም ማርቲን ሉተር ዘመኑን ለመቀጠል መጣ እና ቤተ ክርስቲያንን በጽድቅ ወዘወዛት። ሉተር ሲሞት ምን ሆነች? አደራጅተው፡ የሉተራን ቤተ ክርስቲያን አደረጓት፡ የራሳቸው ትምህርትም አደረጉባት። ሲያደራጇት፡ ምን አደረጉ? ሮማዊነትን እንደገና ወለዱ። ይህ እውነት ነው።

185 ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ከዚያ ሸሸና እና ዌስሊ አየ። እነ ዌስሊ፡ እነ ዋይትፊልድ፡ ጆርጅ ዋይትፊልድ፡ እና ሌሎች ብዙዎቹ፡ እና—እነ አስበሪ፡ እና ብዙዎቹ ታላቅ ሪቫይቫሊስቶች ነበሩ። በዚያ ዘመን ዓለምን አዳኑ። በፊላደልፊያ ዘመን እንግሊዝን፡ እና ዩናይትድ ስቴስትስን ያዳነ ሪቫይቫል ነበራቸው። "ሆሊ-ሮለርች" እየተባሉ የሚሰደዱበት ጉባኤዎች ያደርጉ ነበር። እናንተ ሜቶዲስቶች፡ እንደዚያ ነበራችሁ፡ የእግዚአብሔር ኃይል ሲነካቸው ወለል ላይ ይወድቃሉ፡ እና ውኃን በፊታቸው ላይ እየረጩ ያራግቡባቸው ነበር። ትክክል ነው። እስኪ... ያኔ እነዚህ "ተንቀጥቃጭ እስኪባሉ ድረስ፡" በዚያ ስር ይንቀጠቀጡ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ስር የሚንቀጠቀጡ እና የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ነበሩ። ይህም የሜቶዲስት ታሪክ ነው። ከእነዚያም አሁን ይህን ያደራጁ፡ ኳከሮች እና ሌሎች መጡ።

186 **ይሄኛው** አይነት ሜቶዲስት፡ የጥንት ሜቶዲስት፡ እና **ይህ** አይነት ሜቶዲስት፡ እና **ያኛው** አይነት ሜቶዲስት አደረጉ፡ የሜቶዲስት ሰዎች ከመዝሙር መጽሐፋቸው ውስጥ "ደም" መቅዳት እስኪያምራቸው ድረስ በጣም-ታች ወረዱ።

187 በቀደም ምሽት፡ በቴሌቭዥን ፕሮግራም (እናቴ ጠራችኝ።) እዚሁ ኢንዲያና ውስጥ፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሮክ-እና-ሮል የሚያስተምር፡ የሜቶዲስት ፓስተር መጥቶ ነበር። "ወደ ቤተክርስትያን የመጣውን ይህ ውብ ጥበብ ማየት ተሰኖን መቆየታችን ያሳፍራል፡" አላቸው።

188 ዲያብሎስ በሐሰተኛ ነብይ ውስጥ ሆኖ ነው! ትክክል! ስሜታችሁን መጉዳት አልፈልግም፡ ግን ወንድሜ፡ ይህ የእግዚአብሔር እውነት ነው። መጨረሻ ላይ ከምትጠፋ በዚህ መንገድ እናንተን ትንሽ አስቆጥቼ፡ ምናልባት መጻሕፍት እንድታጠኑ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ባስታርቃችሁ እመርጣለሁ። አሁን ላትወዱኝ ትችላላችሁ፡ አንድ ቀን ግን ክንዳችሁ በእኔ ላይ አርጋችሁ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ይህ እውነት ነው" ትላላችሁ። ይኸው እዚሁ ነው፡ እነርሱም ይገቡባታል። መገኛቸው ያ ነው... እዚሁ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን እንደሚያደርጉ ተናግሯል።

189 ከዚያም ከዌስሊ በኋላ፡ ዌስሊ ያንን ካደረገ በኋላ፡ ጴንጤዎች አብረው መጡ። የጸጋ ስጦታዎችንም ተሐድሶ ይዘው መጡ፡ በልሳኖች መናገር፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጀመሩ።

190 ልክ ከመሬት እንደሚወጣ የበቆሎ ቅንጣት። ከሁሉ በፊት፡ ትበስብሳለች። ከዚያም ጥንድ ቅጠሎችን ብቅ ታደርጋለች። ከዚያም... የበቆሎ ማሳ ያላችሁ፡ አስቡት። ቅጠሉ አድጎ ዝራረት ያወጣል። ይህ መጀመሪያው፡ ሉተራን ነበር።

ከዚያም ዝራረት፡ ምን ነበር? ሜቶዲስት፡ አበባው፡ የወንድማማችነት ፍቅር፡ የወንጌል ስራ፡ የአበባው ጽጌ ወደ ሌሎች የተዘራበት ነበር።

191 እንዴ፡ ተፈጥሮ እንኳን እነዚህን የቤተ ክርስቲያን ዘመናትን ይናገራል። ሜቶዲስት ከግርግር ወጣ... ወይም፡ ማለቴ፡ ሉተራን ከግርግር ወጣ። ሜቶዲስት ወንድማዊ ፍቅሩን መበተን፡ ይህ ማለት—የወንጌል አገልግሎት ዘመን ነው፡ እና—የሚሰዮናዊነት ዘመን ነበረ። በዓለም ላይ የሚታወቀው ታላቁ የሚሰዮናውያን ዘመን የሜቶዲስት ዘመን ነው። ትክክል ነው። የአበባውን ጽጌ መበተን ነው።

192 ከዚያስ ምን ወጣ? ከዚያ ከአበባው ጽጌ የበቆሎው ሽፋን ወጣ፡ ጴንጤቆስጤዎች ናቸው። ሰብሉ፡ ወደ ተመሳሳይ አይነት ደረሰ። ቅጠል ሳይሆን፡ ዝራረት ሳይሆን፡ ሰብል ሆነ። አሁን ግን—እንደው... ሰብሉን ለመለየት አስቸጋሪ እስኪሆን ድረስ፡ ጴንጤቆስጤዎች በሰብሉ ሁሉ ላይ ፈንገስ ይዘው መጡ። እሱን ለማፅዳት ጊዜው አሁን ነው! አሜን! ምን አደረጉ? ሜቶዲስቶች ያደረጉትን ተመሳሳይ ነገር አደረጉ። አንደኛው ጥቂቶቹን አደራጅቶ፡ "እኛ የአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ነን፡" ይላል። ሌላው፡ "እኛ ጴንጤቆስጣል ሆሊነስ ነን።" ሌላኛውም፡ "ዋንነስ ነን።" "ቱነስ ነን።" **እንዲህ** አይነት ነገሮች—እጅግ ብዙዎች፡ ሌሎችም ብዙዎች አሉ። አቤት! ባለ አንድ-ሻኛ-ግመል ጋላቢዎች፡ ባለ ሁለት-ሻኛ፡ ባለ ሶስት-ሻኛ ጋላቢዎች ወዘተረፈ። ኦህ፡ ከእነዚህ መካከል ሰልሳ፡ ወይም ሰላሳ፡ ወይም አርባ የተለያዩ የድርጅት አይነቶች አሉ።

193 ምን አደረጓት? እንደገና ወደ ሮማኒዝም ወረወሯት፡ በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጥምቀት ተጠመቁ። የትኛውም ጴንጤቆስጤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድም ሰው "በአብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ" ስም የተጠመቀበትን እንዲያሳየኝ እጠይቃለሁ። በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በቀር፡ ጳጳስ፣ ካርዲናል፣ ወይም መምህር፣ የተደረጉበት ሰፍራ ከነበረ እንዲያሳዩኝ እጠይቃለሁ። እና ሉተር ከእሱ ጋር ካቴኪዝም፡ እና ሌላው ነገር ሁሉ ከእሱ ጋር አወጣ። ሜቶዲስቶች በዚሁ ቀጠሉ። ጴንጤዎች ሆይ፡ ልታፍሩ ይገባችኋል! አጽዱት! ወደ ቃሉ ተመለሱ! ንስሐ ግቡ አለዚያ እግዚአብሔር ብርሃናችሁን፡ መቅረዙን ከእናንተ ያነሳዋል። አሜን! እሺ።

194 መንፈስ ቅዱስ መሪ ከመሆን አስወግደው፡ የሰውን ሊቃውንት ገዢዎች ሰጧቸው፡ በምእመናን ላይ አስቀመጧቸው። "ፓስተር፡ እረኞች፡" አይሏቸውም (መጠርያችን **ፓስተሮች**፡ "እረኞች" መባል አለበት፡ ትርጉሙም **ፓስተር** ማለት ነው።) "አባት፣ ካርዲናል፣ ሊቀ ጳጳስ፣ ወይም ዋና አስተዳዳሪ።" እውነተኞቹ ግን ይህን ነገር ይጸየፉታል! እግዚአብሔርም፡ "እኔም፡ እጠላዋለሁ፡" በማለት አጸደቀላቸው! ምክንያቱ ዋና አስተዳዳሪ፡ ሊቀ ጳጳስ፡ እና ጳጳስ መሆን የተገባው እሱ ብቻ ነው። ከእያንዳንዱ ግለሰብ ጋር ይሠራል፡ ከድርጅት ጋር ሳይሆን፡ ከአንድ ሰው ጋር።

195 አሁን፡ በሚገርም ሁኔታ... ወደ ወደ ፍጻሜ ስንቃረብ። አንድ ተጨማሪ ቁጥር ብቻ ቀርታናለች።

196 እዚህ ላይ የካቶሊክ እምነት መጀመሪያ፡ የሐዋርያዊ መተካካት ዶግማ ሆኖ እናገኛለን። ሰንቶች ታውቃላችሁ? ሐዋርያዊ። አሁንም ካቶሊኮች "አሁን ያለው ጳጳስ በሐዋርያዊ ሹመት መተካካት፡ የጴጥሮስ ተተኪ ነው"

ይላሉ። እንዲህ ብሎ ነገር የለም። ሥጋዊ፡ የስጋ ሩካቤ ፍላጎት እንዴት ነው... ኤሳውና ያዕቆብ ከቅዱስ አባትና ከቅድስት እናት ተወለዱ፡ አንደኛው ክርስቲያን ሁለተኛው ሰይጣን እንዴት ሆኑ? ኧሃ-ሃም። እንዴት ሊሆን ይችላል? ምክንያቱም ኃጢአት ኃጢአት ነው፡ ሩካቤም ሩካቤ ነው፡ ልደትን የሚሰጥ ግን እግዚአብሔር ነው።

197 እግዚአብሔር ከዓለም ምስረታ ጀምሮ መርጦናል። ይህን ያውቁ ኖሯል? እነዚህን የታሪክ ጸሃፊዎች እስከምናነብ ድረስ እንቆይና፡ ኢራኒየስን እንመልከት... ዓለም ሳይፈጠር በፊት ስለመረጠው እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚያመሰግነው፡ እነ ቅዱስ ማርቲንና እነዚያ ሁሉ፡ እርሱን እያመሰገኑ፡ እግዚአብሔርን፡ አመሰገኑ። እንዲህ አሉ፦ “ምክንያቱም... ” ሰዎችም ስለ እርሱ ሲናገሩ፡ “ዓለም ሳይፈጠር በፊት ተመረጠ፡” ይላሉ። ያ ቅዱስ ቃል ነው። እነዚህ ወንድሞች ከእግዚአብሔር ጋር የወገኑ ነበሩ። ይህች ጥቁር ቤተ ክርስትያን ግን በአንድ ሺ አምስት መቶ የጨለማ ዓመታት ብቅ ባለች ጊዜ ግን፡ ሁሉንም ነገር እንደ መብራት ጭስ እስኪሆን ድረስ፡ ድብን አርጋ መብራቶቹን አጠፋች። ጌታ ግን “ሲመሽ ግን ብርሃን ይሆናል፡” ብሏል።

198 ሐዋርያዊ መተካካት፡ አንዱ በሌላው ራስ ላይ፡ አንድ ጳጳስ፡ ጳጳስ ለመሆን ከሁሉ በፊት የሊቃነ ጳጳሳት የዘር ሐረግ መሆን ይገባችኋል። ኦህ፡ ማይ፡ ማይ! ያ ከንቱ ነው። ቅዱስ እና ጻድቅ የሆነው—ተራው... ምእመን ሳይሆን፡ ነገር ግን... ካህናት... የሆኑትን—ካህናቱ ከጸለዩላቸው ከኃጢአታቸውም ፍትሃት ካደረጉላቸው፡ ኃጢአታቸውን ይቅር ለማለት፡ ለመናዘዝ ገንዘብ በማስከፈል ነው።

199 ፕሮቴስታንቶችም እንዲሁ ያደርጋሉ! ለመሆን ይሞክራሉ... ፓስተራቸውን ጀርባውን መታ መታ አድርገው እንደሌላው አለም ይኖራሉ። ስለ እግዚአብሔርም ከሚያውቃት በላይ አያውቅም... በቤተ ክርስቲያኑ እንዲቆዩለት የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ናችሁ ይላቸዋል። እዚያው እንዲቆዩ በማድረግ እንደዳኑ ሊነግራቸው ይሞክራል። ዳግመኛ ያልተወለዱ ከነበሩ ግን በዚያ ቀን እጅግ ያዝናሉ! ያለ መንፈስ ቅዱስ ጠፊዎች ናችሁና። በመንፈስ ካልሆነ በቀር፡ “ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው፡” ማለት አይችልም።

200 የኤፌሶን እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ግን በዚህ በተወለወለ፡ ምሁራዊ ንግግሮች አልተታለለችም። ይህም... እነርሱ ነገሩን ጠሉት። ያውቁታልና፡ አልተታለሉም፡ ቤተ ክርስትያኒቱም አልተታለለችም።

201 እነዚያ ወገኖች ይዘውት የነበረ ሐሰተኛው መገለጥ፡ ኒቆላውያን ይባላል፡ ይህም ከእግዚአብሔር ቃል የማይሄድ ነገር ነው። በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ “ካህን ሲያናዝዝ” አይቻለሁ የሚል ካለ ያሳየኝ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሐጢአት ስርየት “ውኃን መርጨት” ሲያስተምር ከወዴት አያችሁ? ለኃጢአታችሁ ስርየት “በአብ፡ ወልድ፡ እና በመንፈስ ቅዱስ” ስም ማን ሲጠመቅ አይታችሁ ነው? ይህን ከወዴት አያችሁ፡ “የሕብረት ቀኝ እጅ በመስጠት፡ ስማቸውን በቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ላይ ማስመዝገብ” እዚያ ውስጥ ነውን? ይህን ሁሉ ነገር የት አያችሁት? ምንድነው ይሄ? ክህነት ነውን ወይስ ቀ—ቀሳውስትነት ነውን ከቃሉ ጋር አይስማማም፡ ኒቆላውያን ናቸው፡ እግዚአብሔርም፡ “እጠላዋለሁ!” ወደ ቃሉ ተመለሱ ብሏል። ኦህ፡

ወንድሞች ሆይ... ይህ ነገር፡ ትንሽ ጠጣር እንደሆነ አውቃለሁ፡ ይሁን እንጂ እናንተ፡ በኢየሱስ ላይ ስለ ማፌዛችሁ፡ እኔ—እኔ—አልጠየቅበትም።

202 በቃሉ ያይደለ፡ የሐሰት መገለጥ ነው፡ እርሱም "ሐሰተኞች፡ ሐሰተኛ ሐዋርያት፡ ሐሰተኛ ነቢያት፡" አላቸው። እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን ግን የመጀመሪያውን የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት እና የመንፈስ ቅዱሰን ጥምቀት፡ ጳውሎስ ያስተማረውን ቃል ከሚያረጋግጡ ምልክቶች ጋር ተቀበለች። አሜን! ውኃን መርጨት በቃሉ ያረጋገጠበት ስፍራ አሳዩኝ። እስኪ እግዚአብሔር በልሳን መናገር እና ሌሎች ታላላቅ ነገሮችን፡ ከፓስተሩ ጋር እጅ በመጨባበጥ፡ እና ስማችሁን በቤተ ክርስትያን ሰም በማስፈር ብቻ ያረጋገጠበት አንድም ቦታ ላይ አሳዩኝ፡ እንደፈለጋችሁ እያጨሳችሁ፡ እየቃማችሁ፡ እየጠጣችሁ፡ እየዋሻችሁ፡ ጭፈራ እና ቁማር፡ ትንሽ ወዝ ወዝ እያላችሁ፡ ትወጣላችሁ... አቤቱ፡ ማረን! ወዳጄ ሆይ፡ ሰጋዊነት ነው፡ የሐሰት ነብይ ነው። አዎን፡ ወዳጄ።

203 የእግዚአብሔር መንገድ ቅድስና ነው። ይህ በክርስቶስ አካል ብልቶች ሁሉ የታወቀ ይሁን፡ የተቀደሰ ሕይወት እስክትኖር ድረስ እግዚአብሔር መሰዋዕትህን አይቀበልም። መሥዋዕቱ በተቀደሱ እጆች መቅረብ አለበት። ይህም... ?... እውነት ነው። ሊቀ ካህናቱ መሥዋዕቱን ሊያቀርብ ገና ሳይገባ፡ መሥዋዕቱን፡ በእግዚአብሔር ፊት ለማቅረብ ከመሄዱ በፊት፡ የተቀደሰ፡ የተሰጠ፡ እና የተቀባ፡ በሽቶ የተረጨ እና ሁሉም ነገር የሆነ መሆን አለበት። ልክ ነው? ታድያ እንዴት እዚህ ወጥተህ ታታልላለህ፡ ትሰርቃለህ፡ ትመካለህ፡ ከጎረቤቶችህ ጋር ትጣላለህ፡ ሌላው ሁሉ ታደርጋለህ፡ እንደገናም ያደረግከውን ሁሉ አድርገህ፡ መጥተህ ትገባና፡ "ጌታ አምላክ ሆይ! ኢየሱስ ይመስገን! ሃሌ ሉያ!" እንዴት ትላለህ?

204 ሰዎች እንዲህ ይላሉ፡ "በልሳኖች ሲናገሩ አይቻለሁ።" ያ ማለት መንፈስ ቅዱሰን አገኝተዋል ማለት አይደለም። "ሲጮኹ ሰምቻቸዋለሁ።" ያ ማለት አሁንም መንፈስ ቅዱሰን አገኝተዋል ማለት አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ነው።

205 መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ "ብዙ ጊዜ ዝናብ በምድር ላይ፡ ለተመደበችበት ስራ ሊያዘጋጃት፡ እና ሊያለብሳት ይመጣል፡" (ዕብራውያን 6) "እሾህና አሜከላ ብታበቅል ግን ለመጣል የቀረበች፡ መጨረሻዋም ለመቃጠል ነው።"

206 "ፀሐይ በጻድቃንና በሐጢአተኞች ላይ ታበራለች። ዝናብ በጻድቃንና በሐጢአተኞች ላይ ይዘንባል።" ዝናቡ የሚመጣው ስንዴውን እና በእርሻው ውስጥ ያለው እንክርዳድ ሁሉ፡ (እንደምንለው) ሰብል ለማድረግ ነው። ስንዴው ከተጠማ፡ እንክርዳዱም ይጠማል። ስንዴውን የሚያጠጣው ያው ዝናብም፡እንክርዳዱንም—ደግሞ ያጠጣል። የስንዴ ቅንጣት አንገቷን ቀና አድርጋ፡ "ጌታ ይባረክ! ሃሌ ሉያ! ሃሌ ሉያ! ዝናብ አገኝቻለሁና ደስ ብሎኛል እያለች ስትዘል!" እንክርዳድዋም እንዲሁ ትዘላለች፡ "ክብር ለእግዚአብሔር! እግዚአብሄርን ይመስገን! ሃሌ ሉያ! እኔም ሰላገኘሁ ደስ ብሎኛል ትላለች።"

207 "ከፍሬያቸው ግን ታውቋቸዋላችሁ።" ትክክል ነው። "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።"

208 7ኛው ቁጥር፡ እና እንዘጋለን፡ ይህ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመን መጨረሻ ነው። ምናልባት አምስት፡ ወይም አሰር፡ ለደቂቃ ያህል እንዘገያለን።

**መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ** ያለው **ይስማ፡ ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ ካለው፡ ከሕይወት ዛፍ ይበላ ዘንድ** እሰጠዋለሁ።

209 አሁን ተመልከቱ፡ ጓደኞች፡ ድል የምትነሱበት መንገድ ይህ ነው። በመጀመሪያ ድል መንሳት አለባችሁ፡ ከዚያም ፍሬውን መብላት ትችላላችሁ። ድል ነሺው ነውና። በቀደም ማታ ላይ፡ የበቀደም ማታ ትምህርታችን ትዝ ይላችኋል? ዮሐንስ ምንም ነገር ከማየቱ በፊት በመንፈስ መሆን ነበረበት። ታዲያ እናንተስ፡ "እሱ ከባፕቲስት ካልሆነ፡ እሱን መስማት አልፈልግም" በማለታችሁ፡ እንዴት ትወጡታላችሁ? "እሱ ፕሪስባይቴሪያን ካልሆነ፡ እሱን መስማት አልፈልግም።" "ቤተ ክርስቲያኔ የምታስተምረውን በትክክል ካላስተማረ፡ እኔ... " አንተ––አንተ––አንተ ድል አትነሳም፡ ገና በመንፈስ አልገባህም። ሁላችሁም ከትዕዛዝ ውጪ ናችሁ።

210 በመንፈስ ሁኑ፡ እንዲህም በሉት፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እወድሃለሁ፡ አሁን የምትፈልገውን ሁሉ ግለጽልኝ፡ ወደ እኔ አቅርብልኝ።" ከዚያ በኋላ––ከዚያ በኋላ መልካም ትሆናላችሁ። ትክክል ነው።

211 አሁን አስተውሉ፡ መጽሀፍ ቅዱስ ስለ ሕይወት ዛፍ––ሶስት ጊዜ በዘፍጥረት፡ ሶስት ጊዜ በራእይ መጽሐፍ ይናገራል። ትዝ ይላችኋል? ባለፈው አይተነዋል። ትላንትና፡ እሁድ። ዲያብሎስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት፡ በሙላት ይጠላል፡ ይሁን እንጂ፡ ከሁሉ አብልጦ የሚጠላቸው... ዘፍጥረትን እና ራእይን ነው። ዘፍጥረትን የሚቃወመው ስለ እውነታው ነው፡ ምክንያቱም ሰዎች እንደዚያ አልነበረም ብለው እንዲያምኑ ለማድረግ ይፈልጋል፦ "ዘፍጥረት እግዚአብሔር አደረጉ ብሎ በተናገረው መንገድ አይደለም፡ ፍጥረትን እና ሌላውን ሁሉ ያመጣው ሌላ ነገር ነበረ እንጂ።" ብበዚህ መንገድ ያጠቃዋል። በመቀጠል ሰዎችን ከራእይ መጽሐፍ ገለል የሚያደርጋቸው የሚከተሉትን ስለሚያጋልጥ ነው፦ ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ፡ እርሱ ግን ዲያብሎስ እንደሆነ፡ (እንደተፈረደበትም)፡ የቅድስቲቱ ቤተ ክርስትያን ክብር ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ክብር መወሰድ፡ እና የሐሰተኛው ነብይ ፍርድ፡ የሚዋሹ እና ክፉ የሚያደርጉትን ሁሉ ወደ እሳቱ ባሕር እንደሚጣሉ ያጋልጣል። ከሱ እንዲርቁ ማድረጉ ምንም አያስደንቅም። ሁለቱም ቦታዎች የሚናገሩት ግን፡በገነት ውስጥ ስላለው የሕይወት ዛፍ እንደሆነ፡ አስታውሱ።

212 አሁን ይህንን "ዛፍ" ለጥቂት ደቂቃዎች እንየው። መጻፍ ለምትፈልጉ፡ ቅዱስ ዮሓንስ 6ኛው ምዕራፍ፡ ኢየሱስም "የሕይወት እንጀራ––እኔ––ነኝ፡" አላቸው። አሁንም፡ አስታውሱ።

213 ስለዚህ፡ ከመዘጋታችን በፊት፡ አሁን። አሁን እነዚህን ሁለት አምዶች እንደ ምልክት እንጠቀማቸዋለን። አሁን፡ በቀኝ እጄ ያለው በገነት ውስጥ የነበረው "የሕይወት" የሚባለው ዛፍ ነው፡ በግራ እጄ በገነት ውስጥ የነበረው "የዕውቀት" የሚባለው ዛፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት ዛፍና የእውቀት ዛፍ እንዳለ እንደሚናገር ሰንቶች ታውቃላችሁ? እንግዲህ ሰው፡ የእውቀትን ዛፍ ሳይነካ፡ በሕይወት ዛፍ ግን እንዲኖር ነበር። ልክ ነው? ይህን በነካው

በመጀመሪያ ጊዜም፡ ከፈጣሪው ተለየ። ከእውቀት የመጀመሪያውን ጉርሻ በጎረሰ ጊዜ—ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ሕብረት አጣ። አሁን፡ በደንብ አሰቡት። ማስታወሻ እየፃፋችሁ ያላችሁ፡ የምትጽፉበት ጊዜ እሰጣችኋለሁ፡ ይህ እንዲያመልጣችሁ አልፈልግም።

214 ኢየሱስ፡ በቅዱስ ዮሐንስ ምዕራፍ 6። እጆቻቸውን እያወናጨፉ፡ እና እየተሳደቡ አባቶች ከጠጡት ከአንዱ፡ ማለት፡ ከመንፈሳዊው ዓለት፡ ከምንጩ ወዘተረፈ መጠጣታቸውን ተናገሩ። እርሱም "በምድረ በዳ የነበረው ዓለት እኔ ነኝ፡" አላቸው።

215 እነርሱም አንተ'ማ "'ከአብርሃም በፊት እኔ ነበርኩ' ትላለህ፡ አምሳ አመት እንኳን ያልሞላህ ሰው ነህ። 'አብርሃምን አይቻለሁ' ትላለህን? አንተ፡ እብድ መሆንህን፡ ዲያብሎስ መሆንህን፡ አሁን አወቅን።" አያችሁ?

216 እርሱም "አብርሃም ከመኖሩ በፊት፡ **እኔ ነኝ፡**" አላቸው። **እኔ ነኝ** ከሙሴ ጋር በቁጥቋጦው ዘንድ፡ በሚነደው ቁጥቋጦው፡ **እኔ ነኝ**። "እኔ ነበርኩ፡" ሳይሆን፡ "አብርሃም ከመኖሩ በፊት፡ **እኔ ነኝ**።"

217 እንግዲህ፡ እናንተ የተአምራት ዘመን አልፏል የምትሉ ሆይ፡ መጽሐፍ ቅዱሱን "እኔ የነበረው ታላቅ የነበረ ነኝ፡" ብላችሁ መቀየር ነበረባችሁ። አያችሁ?

218 "እኔ ነበርኩ፡" ወይም "እኔ ወደፊት እኖራለሁ" ሳይሆን፡ "**እኔ ነኝ፡**" ይህ ማለት ሁሉ ጊዜ ማለት ነው። እርሱ ዘለአለማዊ ነውና። "**እኔ ነኝ**" የሚል ቃል ዘለአለማዊ ነው፡ በየዘመናቱ፡ በየወቅቱ፡ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ሁሉ፡ በየአብያተ ክርስትያናት፡ በየቦታው፡ በሁሉም ሰው ልብ። "**እኔ ነኝ፡**" ("እኔ ነበርኩ" ወይም "እኔ እኖራለሁ" አይደለም፡) "እንደ ሁልጊዜው አሁንም እኔ ነኝ።" አያችሁ? "ሁል ጊዜ፡ **እኔ ነኝ**።"

219 እነርሱም "አባቶቻችን እንዲህ እና እንዲያ... አንተን ግን አናውቅህም። ሰይጣን እንደሆንክ እናውቃለን።" "አባቶቻችን አርባ አመት በምድረ በዳ መና በሉ፡" አሉት።

220 ኢየሱስ ግን "ሁሉም ሞተዋል፡" አላቸው። ልክ ነው? "ሁሉንም ሞተዋል። እኔ ግን... " ኦህ! "ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ። የ... የሕይወት እንጀራ። ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ፈጽሞ አይሞትም።"

221 "ይህ ሰው፡ ሥጋውን ለመብላት ይሰጣልን? " "አሁንስ በትክክል፡ አብዷል፡" አሉ።

222 የሕይወት እንጀራ፡ ከኤደን ገነት ጀምሮ፡ ይበሉት የነበረው የሕይወት ዛፍ ነው። እርሱ የሕይወት ዛፍ ነበር። እንግዲህ፡ የሕይወት ዛፍ አካል ከነበረ፡ የእውቀት ዛፍም አካል ነበር ማለት ነው። እንግዲህ እባቡ ዘር አልነበረውም በሉኛ! ሕይወት በወንዱ ከመጣ፡ ሞት በሴቲቱ መጣ። እሺ፡ የሞት ዛፍ እሷ ነበረች።

223 ይሄኛው—ማለት (እባቡ)፡ ልክ እንዳበላሻት፡ "እባብ አሳተኝ፡" አለች። ትክክል። ይሄኛው እባብ አይደለም፡ እርሱ ከአራዊት ሁሉ በጣም የተራቀቀ ነበረ፡ በሰው እና በቺምፓንዚ መካከል ነበረ ነው። የእንስሳ ዘር ከሰው ጋር አይዳቀልም፡ በፍጹም አይችልም፡ ይሄኛው ግን ይችል ነበር፡ ከሱ ቀጥሎ ይህ

ነበርና። እግዚአብሔርም ክፉኛ ረገመው፡ እግርም የሌለበት በሆዱ የሚሳብ አደረገው፡ አጥንቱንም ሁሉ ወሰዶ ሰውን የሚመስልበት ነገር ሁሉ ለወጠው። በሳይንሳዊ ዘርፍ ቆፍረው ለማወቅ ሞክረዋል። ይህ ግን በእግዚአብሔር ምስጢሮች ውስጥ፡ በእግዚአብሔር ገነት መካከል ተሰውሯል። መገለጡ ይህ ነው።

224 የመጀመሪያ ልጇን ቃየንን ወለደች (ልክ ነው? ) እርሱም፡ የሰይጣን ልጅ፡ የሰይጣን ልጅ ነው። እርሱ እንዲያ ካልሆነ ግን፡ እንግዲያውስ—ክፋት ከወዴት ገባ? የእግዚአብሔር ልጅ ከነበረው ከአዳም ነውን? አይደለም፡ ከአባቱ ከዲያብሎስ ነው። እርሱም ገደለ፡ የመጀመሪያው ገዳይ ዲያብሎስ ነበረ፡ የዲያብሎስ ልጅ ነበረ።

225 ከዚያ በኋላ የሆነውን ተመልከቱ፡ የቃየንን የዘር ሐረግ ተመልከቱ። ከቃየን በኋላ፡ የመጣው ትውልድ ሁሉ፡ ሳይንቲስቶች እና ታላላቅ ሰዎች ነበሩ። መጽሐፍ ቅዱስን አንብቡ። ቤቶችን ሠሩ፡ ብረት ቀጠቀጡ፡ እና ሳይንቲስቶች ነበሩ። ከሴት ወገን የተወለዱ ሁሉ ግን፡ (አቤል ሞተ፡ መሞቱ፡ የኢየሱስ ጥላ ነበረ፣ አቤል ከሞተ በኋላ፡ ሴት ሰፍራውን ተካ፡ መሞት፡ መቀበር፡ እና ትንሣኤ ነው።)… ከእርሱ ዘንድ ከዚያ ሐረግ፡ ትሑታን ገበሬዎች እረኞች ተገኙ።

226 አሁንም ኢየሱስ፡ “አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ነገር ግን ሁሉም ሞተዋል። እኔ ግን ያ የሕይወት እንጀራ ነኝ፡” (የምን የሕይወት እንጀራ? የኤደን!) “ሰው ከዚህ እንጀራ በልቶ እንዳይሞት።” አሁን፡ ማንም እንዳይነካው ይጠብቀው ዘንድ፡ እግዚአብሔር መልአክን በዙሪያው አደረገ፡ ይህም ከዛፉ በልተው በህይወት እንዳይኖሩ ነው። ልክ ነው?

227 ምክንያቱ፡ ከዚህኛው መብላታቸውን በመቀጠል እንዲሞቱ ነው። ልክ ነው? ምክንያቱ፡ ከዚህኛው እስከበሉ ድረስ፡ ይሞታሉና። እናንተ ከዕውቀት ዛፍ ስለበላችሁ መሞታችሁ እንዳልቀረ ሁሉ እንዲሁ ነው… አሁን፡ ያንን የእውቀትን ዛፍ አሁን እንየው። ምን እንደተደረገ ተመልከቱ። አሁን ምን እንደተደረገ እንይ። እስኪ፡ በመጀመሪያው፡ ይህን እንየው… እሺ እንየው፡ በዚያው… የጥይት ባሩድ ሰሩ። ጓዶቻችንን ገደለ። አዎን፡ ከእውቀት ዛፍ የተነሣ፡ እርስ በርስ አገዳደለን። በሁለተኛ ደረጃ ያደረግነው፡ አቤት፡ እስኪ እንየው፡ ከእውቀት—ከእውቀት ዛፍ፡ መኪናንን ሰራን። ባሩድ ከሚያጠፋው ጥፋት በላይ ይገድላል። ኦህ፡ አዎን! አሁንማ፡ የሃይድሮጂን ቦምብ መጣ። ሰው በገዛ እውቀቱ እራሱን ያጠፋል እንጂ፡ እግዚአብሔር ማንንም አያጠፋም።

228 የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ግን፡ እግዚአብሔር እንደገና ያስነሣዋል፡ እግዚአብሔር ምንም አይጠፋበትምና። ኢየሱስም እንዲሁ ብሏልና፡ ይህም እውነት ነው፡ “እንጀራዬን የሚበላ የዘለአለም ህይወት አለው፡ በመጨረሻው ቀንም አስነሣዋለሁ።” ቃል ኪዳኑ ይህ ነው። አሁን፡ እግዚአብሔር…

229 በእውቀት ዛፍ ላይ እየበሉ እየሞቱ፡ ቀድመዋል። ወደዚህ ዛፍ መድረስ በቻሉ ቁጥር ግን፡ ለዘለአለም ይኖራሉ።

230 ስለዚህ አሁን ከዚህ ዛፍ ከሚያርቃቸው መልአክ ፊንታ፡ **ወደዚህ** ዛፍ እየነዷቸው የሚገኙት፡ የአብያተ ክርስቲያናት፡ የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት፡ በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ ወደቆመው የሕይወት ዛፍ ወደሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይመልሷቸዋል። አቤት! ይደንቃል! እንደገባችሁ ተስፋ

አደርጋለሁ። በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ ከቆመው ከሕይወት ዛፍ ከእርሱ ተካፍላችሁ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች እንድትሆኑ ለዘላለምም እንድትኖሩ ነው። "ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፡ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ ከቶ አይመጣም።"

231 ወንድም፡ እህቶች ሆይ፣ አሁን እኔ... አይ... እርግጥ ነው፡ እኔ... ጎ—ጎድቻችኋለሁ፡ እየቆራረጥኳችሁ ነው። ግን እንደዚያ ላደርግ—ፈልጌ አይደለም። አያችሁ? እግዚአብሔር ያውቃል፡ ነገር ግን ያለንበትን ሁኔታ ማየት እንድትችሉ በዚህ መንገድ ማድረግ አለብኝ። ብዙ የምንቆይበት ጊዜ ቀርቶናል ብዬ አላምንም። የድርጅት አባል ስለሆናችሁ እናንተን ከክርስትና ልለያችሁ መሞከሬ አይደለም። ያ አይደለም። ህዝቡ የሁኔታዎች ሰለባ ነው። ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም፡ ወላጆቻቸው ሁልጊዜ የሚያደርጉት ነገር ወደ ቤተ ክርስቲያን እና ነገሮች መቀላቀል ብቻ ነውና።

232 ነገር ግን፡ ወንድሜ ሆይ፡ ከመሄዳችን በፊት፡ አንድ ነገር ይህን አንድ ተጨማሪ ጥቅስ ልናገር። ነቢዩም እንደተናገረው... ነቢያትን ታምናላችሁን? መጽሐፍ ቅዱስ ሰሚቸው ይላልና። ነቢዩም እንዲህ አለ፡ "ቀንም ሆነ ሌሊት የማይሆንበት ጊዜ ይመጣል፡ ነገር ግን የአዘን ቀን ይሆናል። ነገር ግን በማታ ጊዜ፡ ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ግን፡ብርሃን ይሆናል።" ልክ ነው?

233 የነበረን ነገር እስኪ እንመልከተው። አሁን፡ እንየው እስኪ። በጂኦግራፊካዊ አቅጣጫ... ጸሐይ፡ ከወዴት በኩል ትወጣለች? በምስራቅ በኩል። ልክ ነው? በምዕራብ ትጠልቃለች። እንደው ነገ ካርታውን አምጥቼ ባሳያችሁ ደስ ይለኛል እና... አመጣዋለሁ። መንፈስ ቅዱስ በኢየሩሳሌም በወረደ ጊዜ፡ ፍጹም የሰምንት ቁጥር፡ ጉዞ አደረገ። በቀጥታ ወደ አየርላንድ ሄደ፡ ወደ ኋላ ተመለሰና፡ ዞሮ በማለፍ፡ ወደ ምዕራባዊ ዳርቻዎች መጣ፡ ወንጌሉ በተጓዘበት ፍጹም የሰምንት ቁጥር አካሄድ፡ እንደገና ተመልሶ መጣ። እንግዲህ፡ ሰልጣኔም ከጸሐይ ጉዞ ጋር ይዞራል። ሰንቶች ታውቃላችሁ? ከዚህ በፊት ስለተማራችሁት ታውቁታላችሁ። አሁን ያለን ጥንታዊ ሥልጣኔአችን ከቻይና ሲሆን፡ ከዚያ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ትመጣለች። እና መንፈስ ቅዱስም፡ ማለት ኤሰ-ዩ-ኤን ሳይሆን ኤሰ-ኦ-ኤን...

234 ጸሀይ፡ ማለት ኤሰ-ዩ-ኤን፡ ከሌሊት እርጥበት እና ከጭጋግ በኋላ ስትወጣ፡ ዘር የትም ቢወድቅም'ኳ፡ በሕይወት ይኖራል፡ ምክንያቱም የእጽዋት ሕይወት ሁሉ መኖርያው በፀሐይ ነውና። ያንን እናውቃለን። አንድ የሣር ማሳ ኮንክሪት ብናለብሰው፡ በሚቀጥለው የጸደይ ወቅት፡ በጣም ወፍራሙ ሣር የት እናገኘዋለን? በኮንክሪቱ ጠርዝ ዙርያ። ለምን? ከሰሩ ያለው ህይወት ስለሆነ፡ ትክክለኛ ህይወትን መደበቅ ስለማይቻል ነው። ትንሿ ህይወት፡ ጸሀይ በዙርያ እያንዣበበች መሆኗን ስትረዳ፡ ከኮንክሪት ሰር ወጥታ እራሷን ቀና በማድረግ፡ እግዚአብሄርን ማመስገን እስክትጀምር ድረስ ከሰር ሰር ግማሽ ጎዳና ያህል ርቀት እየተሳበች ትጓዛለች።

235 ህይወትን መደበቅ አትችሉም። ልክ ነው፡ **ህይወት**። ዳግም ከተወለዳችሁ ልትደብቁት አትችሉም። ሕይወት ስታገኙ የሆነ ነገራችሁ ይጮኻል።

236 አሁን፡ ትንንሽ—ዘሮች ሁሉ አፋቸውን ከፍተው፡ ውስጠኛው አካላቸው ወጥቶ፡ የሞቱ ነገሮች በሙሉ፡ ሁሉም የሞቱ ናቸው፡ ይሁን እንጂ ህይወቱ

በውስጡ አለ። በጸደይ ወቅት ጸሐይ ማንጸባረቅ ስትጀምር፡ ያኔ፡ ትንንሽ አበቦች ይወጣሉ፡ ሌሎች ሁሉ እራሶቻቸውን ቀና ያደርጋሉ (ከየውዳቂው፡ ከየግንዱ ሥር፡ ከዓለቶች ሥር)፡ እንደገና እየወጡ፡ እንደገና መኖር ይጀምራሉ። ልክ ነው? ምክንያቱ ኤስ-ዩ-ኤን በማንጸባረቋ ምክንያት ነው።

237 አሁንም፡ አንድ ቀን የሕይወት ደራሲ የሆነው፡ ኤስ-ዩ-ኤን ማንጸባረቅ ይጀምራል፡ እና በእርሱ ለዘለዓለምም ሕይወት የተመደበው ሁሉ "በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ፡" ብሏል። ምን ለማለት እንደፈለኩ አያችሁ? የዘላለም ሕይወት በመጨረሻው ቀን ይነሳል። ባህር ውስጥ ቢቀብሩት፡ ወይም ገላህን አቃጥለው ወደ አራቱ የምድር ነፋሳት ቢዘሩት፡ እግዚአብሔር በመጨረሻው ቀን ያስነሳዋል። የተራበ አንበሳን ሆድ ለማጥገብ ቢወረውሩህ፡ ወይም—በአካልህ ውስጥ የሚገኙትን ንጥረ ነገሮች እና ኮስሚክ ላይቶች በሙሉ—ከ—ከውስጡ እስኪወጣ ድረስ ወደሚነድ ጉድጓድ ቢያወርዱትም፡ እግዚአብሔር ያስነሣዋል። "የራሳችሁ ጠጉር እንኳ የተቈጠረ ነው።" አሜን! እግዚአብሔር ያስነሳዋል!

238 አሁን፡ ወደዚህ ተመልከቱ። እንግዲህ፡ ሞት ለሰው ሁሉ በሴት በኩል ከገባ፡ ህይወትም ለሰው ሁሉ በአንዱ ሰው ይገባል። በእንደዚያ አይነት ህይወት ከሴት ጋር ተካፋይ መሆን፡ እንደሚገድላችሁ ታውቃላችሁ። መውጫ መንገድ የለውም፡ ትሞታላችሁ። እንዲሁም በተመሳሳይ ከእሱ ጋር በመካፈላችሁ፡ በርግጥ በሕይወት ትኖራላችሁ፡ መውጫ መንገድ የለውም፡ በሕይወት ትኖራላችሁ። አሜን! ያኛው ትክክለኛ ሞት ቢያፈራ፡ ይሄኛው ደግሞ ትክክለኛ ሕይወት ያፈራል። ህይወት እንዲሆንላችሁ፡ እናንተም መቀበል የምትችሉበት መንገድ ይህ ብቻ ነው።

239 አሁን፡ ነብይው፡ ሲናገር "ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡" አለ። አሁን ተመልከቱ። ቀንና ሌሊት የማይባል ቀን፡ እንደሚመጣ ተናግሯል። ደመናማ፣ ጭጋጋማ፣ ቀዝቃዛ ቀን ነው፣ በዚህ ሁሉ ግን ብርሃን የሚሰጥ ልጁ ነው። ከዚያ ከላይ ጭጋግ እና ደመና ከመሳሰሉት በላይ፣ ልጅ ብርሃን ይሰጣል። መራመድ የምትችሉበትን በቂ ብርሃን ይሰጣል፡ ስለዚህ እንዴት መኖር፡ እና እንዴት መንቀሳቀስ እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ፡ ግን'ኮ—ገና አልበራም፡ ሙሉ ቀን አልሆነም። አያችሁ? እንግዲህ፡ ያቺ ዘመን ችሎ የሚኖርባት አካል አይኖርም።

240 ፀሀይ በማይበራበት ቦታ ማንኛውንም ነገር ብትተክሉ፡ ይቀጭጫል። ልክ አይደለምን? እናንተ ገበሬዎችም ታውቃላችሁ። በቆሎውን በጥላ ውስጥ ወይም በሆነ ቦታ ላይ ትክሉት፡ እና ጠብቁት፡ ያቀጭጨዋል። ፍሬድ፡ ከሰንዴህ ልታውቀው ትችላለህ። አንተ የዘራኸው፡ መጥፎ በጋ፡ ወይም፡ ዝናብ እና ቅዝቃዜ ቢሆንበት፡ ያቀጭጨዋል።

241 እንግዲህ፡ በእነዚህ ዘመናት ውስጥም የቤተክርስቲያን ጉዳይ ያ ነው፡ ቀጭጫለች። ከሐይማኖት ተቋማት የተነሣ ቀጭጫለች፡ "እግዚአብሔር መኖሩን የምናውቅበት በቂ ብርሃን እኛ ጋር አለ። ስምህን በመጽሐፍ ላይ አስመዝግብ።" በዚህ ደስ ብሎኛል። "ክርስቶስ እንዳለ፡ የሚመጣው ፍርድ እንዳለ ለማወቅ በቂ ብርሃን ይዘናል። ብርሃን ነበረን፡ ስሞቻችንን በመጽሐፎቹ አስፍረናል፡ ከፓስተሩ ጋር ተጨባብጠናል፡ እንዲህ እና እንዲያ አድርገናል፡ ወዘተ።" እሺ፡ አሁን ግን ምሽት ነው።

242 አሁን፡ ስልጣኔው ከወደ ምስራቅ ወደ ምዕራብ መጣ፡ አሁንም እኛ በምዕራብ ዳርቻዎች እንገኛለን። ከዚህ በላይ መሄድ አንችልም፡ ተሻግረናል፡ እንደገና ወደ ምስራቅ ተመልሰናል። በምዕራቡ ጠረፍ ነንና፡ ከዚህ በላይ መሄድ አንችልም።

243 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ "ሲመሽ ብርሃን ይመጣል፡" ብሏል። ታዲያ፡ ሲመሽ የምትበራ ጸሐይ ምን አይነት ናት? ጠዋት ላይ ከምትወጣ ፀሀይ የተለየች ናት? ተመሳሳይ ፀሐይ ናት። ልክ ነው? ታዲያ፡ እግዚአብሔር የገባው ቃል፡ ምንድነው? አሁን በቀጥታ እንገባበታለን፡ ይህን ያዙት፡ **ለዚህ** ለአሁኑ ዘመን ነውና። መጽሐፍ ቅዱስም ይላልና፡ በአብያተ ክርስትያናት ዘመናት፡ እየቀጠልን ስንሄድ፡ አረጋግጥላችኋለሁ፡ ይህም፡ "ሲመሽ ወደ ምዕራብ የሚወጣ ብርሃን ይኖራል የጽድቅ ጸሐይ እንደገና ፈውስን በክንፎቿ ይዛ እንድትመጣ ያደርጋታል። በመጨረሻው ዘመን ከሚፈጸም ሌላኛው የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ጋር ጋር በተያያዘ መልኩ በምሥራቅ የተደረጉ እነዚያ ምልክቶች፡ እና እነዚያ ድንቆች በዚህ በምዕራብም ይፈጸማሉ።"

ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡
የክብር ጎዳና በእውነት ይገኛል፡
በኢየሱስ ክቡር ስም፡ እየተቀበርን፡
የውኃው መንገድ ለዛሬ ብርሃን ሆነልን።
ከኃጢአት ታጥበን፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲገባ፡
ታናናሽ ታላላቆች፡ ሁላችንም ንስሓ እንግባ፡
የማታው ብርሃን መጥቷል፡
እግዚአብሔር እና ክርስቶስ አንድ መሆናቸው ተረጋግጧል።

ኦህ፡ ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡
የክብር ጎዳና በእውነት ይገኛል፡
በኢየሱስ ክቡር ስም እየተቀበርን፡
የውኃው መንገድ ለዛሬ ብርሃን ሆነልን።
ከኃጢአት ታጥበን፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲገባ፡
ታናናሽ ታላላቆች፡ ሁላችንም ንስሓ እንግባ፡
የማታው ብርሃን መጥቷል፡

244 ጴጥሮስ ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል እንዲህ ሲል፡ "ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፡ እግዚአብሔር፡ ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው፡ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን። እያንዳንዳችሁ፡ ንስሐ ግቡ" "ለኃጢአታችሁም ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡" አላቸው።

245 አንድ ነገር ልንገራችሁ። ባለፈው ቀን ስለ **ሃኪም ትእዛዝ** እየተናገርኩ ነበር። እና ሰዎች የዶክተሩን ማዘዣ መውሰድ አልወደዱም። በሽታችሁን ሊፈውስ የሚችል አቅም ያለው—መድኃኒት ከሆነ፡ እናንተ-ግን... አልፈልግም ብትሉ፡ መሞታችሁ የዶክተሩ ስህተት አይደለም። አይደለም፡ ጌታዬ። ስሕተቱ የአንተ ነው፡ ምክንያቱ መድሐኒቱን አልፈልግም ብለሃልና።

246 ሌላው ደግሞ፡ ዶክተር ማዘዣ ከጻፈልህ ይህን ይዘህ... ወደ ሐሰተኛ ባለ መድሐኒት ከሄድክ፡ መስጠት የማይገባው መድሐኒት ቢጨምርልህ፡

ይህም፡ ይገድልሃል። ልክ ነው? ሐኪሙ በሰውነት ውስጥ ያሉትን ነፍሳት መግደል የሚያስችል ብዙ መርዛማ መድሐኒቶች እንዳሉ እስኪያውቅ ድረስ፡ እጅግ የተማረ ነው፡ እንዲሁም መርዛማ ነገሮችን ማምከን የሚችለውን በቂ አምካኝ እንዳለም ያውቃል። መጠነኛ መሆንም አለበት። አምካኙን አብዝታችሁ ብትሰጡት፡ በሽተኛውን አይጠቅመውም፡ ብዙ መርዝ መስጠትም፡ ይገድለዋል። መጠኑን መጠበቅ አለበት።

247 ጥያቄው፡- "በገለዓድ ውስጥ የሚቀባ የለምን? ባለ መድሐኒት በዚያ የለምን?" አለ ነቢዩ። "ታዲያ የልጄ በሽታ ለምን አልተፈወሰም?" ቤተክርስቲያን ችግሯ ምንድነው? ለምንድነው ብዙ ያረጁ የታመሙ አብያተ ክርስቲያናት የበዙብን? የተሳሳተ መድሐኒት የሚያዙ ሐሰተኞች ባለ መድሐኒቶች ስላሉን ነው። ትክክል ነው። "አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ፡" በፍጹም ብሎ አያውቅም። እሱ...

248 ማዘዣው ምን ይላል? ጴጥሮስም ቆመ። የመንግሥቱ ቁልፎች ይዞ እንደነበረ ሰንቶች ታውቃላችሁ? ኢየሱስም እንዲህ አለ። እሱ ምን አለ? በሌላ አነጋገር፡ ለመድኃኒት ማዘዣው የቀለም ብዕሩን በእጁ ይዞ ነበር ማለት ነው።

249 ይህንንም በሰሙ ጊዜ፡ (እየጮኹ፡ እልል እያሉ፡ በልሳን እየተናገሩ፡ ጥሩ ጊዜ እያሳለፉ ነበርና።) ሰምተው "እነዚህ ሰዎች ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥተዋል፡" አሏቸው።

250 ጴጥሮስም፡ "ለእናንተ እንደመሰላችሁ፡ ገና ከቀኑ ሶስት ሰዓት ነውና፡ እነዚህ ሰዎች የሰከሩ አይደሉም። ነገር ግን ይህ በነቢዩ ኢዩኤል የተነገረው፡ 'በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፡' ይላል እግዚአብሔር፡ 'መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፡ በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፡ ትንቢትም ይናገራሉ። ምልክትም በላይ በሰማይ፡ በታችም በምድር ላይ፡ እሳትና ጢስ፡ ጭጋግም፡ አሳያለሁ። እናም እንዲህ ይሆናል የጌታን ስም የሚጠራ ሰው ሁሉ ምን አይሆንም... ይድናል።'"

251 ከዚህም በላይ ስለ ዳዊት፡ እንዲህ አለ፡ "የአባቶች አለቃ ዳዊት፡ አስቀድሞ አይቶ እንዲህ አለ፡ 'ሥጋዬም በተስፋ ያድራል ነፍሴን በሲኦል አይተዋትምና፡ ቅዱሱንም መበስበስን ያይ ዘንድ አይተወውም።' ወንድሞች ሆይ፡ ስለ አባቶች አለቃ ዳዊት፡ ለእናንተ በግልጥ እናገራችሁ ዘንድ ፍቀዱልኝ፡ እርሱ ሞቷልም ተቀብሯልምና፡ መቃብሩም እስከዛሬ ድረስ በመካከላችን ነው። ነገር ግን፡ እያችሁ፡ እርሱ ነብይ ስለነበረ፡ የክርስቶስን ትንሣኤ አስቀድሞ አይቷል። እንግዲህ በክፉ እጆች፡ እናንተ እንደሰቀላችሁት፡ ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር፡ ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው በእናንተ ዘንድ ይታወቅ።"

252 ይህንም በሰሙ ጊዜ፡ ልባቸው ተነካ፡ እንዲህም አሉ፡ "ወንድሞችና ሆይ፡" ወይም፡ "ዶ.ር ሰምዖን ሆይ፡ ማዘዣውን ጻፍልን። ይህ እንዴት እናገኘዋለን? የሐጢአትን መድሐኒት እንፈልጋለን።" ኦህ!

253 አሁን እርሱ ያለውን፡ ተመልከቱት። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ከመንገድ የት እንደወጡ ታውቃላችሁ። እንዲህ አላቸው፡ "እንዴ ጠብቁኝ! ማዘዣውን እጽፍላችኋለሁ፡ እርሱም ዘለአለማዊ ማዘዣ ይሆናል። ለእናንተም፡

ለልጆቻችሁም፡ እግዚአብሔር አምላካችንም ወደ ጠራቸው፡ በሩቅም ላሉ ሁሉ ይሆናል።”

254 ምን አለ? እንዴትስ አስተካከለው? ካቶሊክ እንዳደረጉት ነውን? ባፕቲስቶች እንዳደረጉ ነውን? ልክ እንደ ሜቶዲስት ነውን? እያንዳንዳቸው አንድ ነገር ጨምረዋል ወይም የሆነ ነገር ቀንሰዋል። እንደ ጴንጤቆስጤዎች? እነርሱ ጨምረዋል ወይም ቀንሰዋል። ታዲያ ምን አለ? “ንስሐ ግቡ፡ ለኃጢአቶቻችሁም ስርየት፡ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።” ዘላለማዊ ማዘዣ ነው! “ለእናንተ፡ እና ለልጆቻችሁ ነው፡ ይህ በሁሉም የቤተ ክርስቲያን ዘመን ይኖራል፡ ለእያንዳንዳቸውም የተሰጠ ነው።”

255 አቤቱ አምላኬ፡ እጆቼን አንፃ። ጌታ ሆይ፡ ልቤን ቀድስ። ምናልባት... ጓደኞቼን በሙሉ የሚጠይቀኝ ቢሆንም እንኳ፡ ዶክተሩ ይሁን ባለው መንገድ ማዘዣውን ልስጥ።

256 ለዚህ ነው ብዙ የሞቱ አብያተ ክርስቲያናትን፡ ብዙ የሞቱ አባላትን ያሏችሁ። ማዘዣው ዋጋ እስኪያጣ ድረስ፡ ማምከኛውን እየዋጣችሁ ከዚያው እጅግ ርቃችኋል፡ እጅ መጨባበጥ፡ የቤተ ክርስትያን አባል በመሆን፡ በመርጨት፡ ምንም ነገር አይፈወስም። አቤቱ፡ ማረን፡ ማዘዣው ይህ አይደለምና፡ ይህ ሞት ነውና። ሕይወትን ከፈለጋችሁ፡ መንፈስ ቅዱስን ከተጠማችሁ፡ እግዚአብሔር የተናገረውን ተከተሉ። ማዘዣውን ውሰዱ! እርሱ በትክክል ያለው “በእሱ ላይ አንዳች አትጨምሩ ወይም ከእሱ ላይ አትቀንሱ፡” ነው። ከዚያም በራእይ ላይ መጣና እንዲህ በማለት አዘዘ፡- “ማንም የሚቀንስ ወይም የሚጨምር ቢኖር፡ (ድርሻው) ከሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ይወሰድበታል።” ኦህ፡ ማይ፡ **ዋናው** ዶክተር ይህ ነው። ኦህ፡ እወደዋለሁ። እናንተስ?

257 አቤት፡ ታላቋ ዘመን፡ የኤፌሶን ዘመን፡ ይህ ስሕተት ገብቶ፡ ድርጅት ሊሰራ ሲል። እና ፓስተሮች እና ዲያቆናት... ወይም ዲያቆናት ሳይሆኑ፡ ፓስተር... ፓስተር ሳይሆን፡ ብፁዕ ካርዲናሎች፡ ጳጳሳት፡ ሊቃነ ጳጳሳት፡ የቤተ ክርስቲያን የበላይ አስተዳዳሪዎች፡ መንፈስ ቅዱስን ይመሩታል፡ ቤተ ክርስቲያንንም ይመሯታል፡ “ይህ ነገር፡ እዚህ ጋር ማድረግ አትችሉም!” እንደው፡ አለቃው ማን ነው?

258 ጴጥሮስ አንድ ጊዜ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ነበር። እንዲህ በማለት፡ “ከንግዲህ በኢየሱስ ስም መሰበክ አትችልም። ከፈለግክ መሰበክ ትችላለህ፡ ግን በኢየሱስ ስም አይደለም።” አቤት፡ ዲያብሎስ ስሙን ይጠላዋል!

259 ጴጥሮስም፡ “እስኪ በራሳችሁ ፍረዱ.... ” መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ “ጴጥሮስ ምን ተሞልቶ... ” (የሐይማኖት ተቋም ነውን? ) አቤት፡ አህ፡ “... መንፈስ ቅዱስ እንጂ።” “ቆይ፡ የበላይ አለቃ አድርግ የሚለኝን እስኪ እያለሁ፡” ትላላችሁ።

260 ልንገራችሁ። አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ሚሽነሪዎቻቸውን በሳይካትሪስት ፊት ያቀርባሉ፡ ማለት ይህ ሰው ሚሽን ለመውጣት የተዘጋጀ አእምሮ እንዳለው ለመፈተሽ፡ መርማሪ ሳይካትሪስት እንዳላቸው ታውቃላልችሁ? የጴንጤቆስጤ አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ። ስንቶች ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? በትክክል፡ በየስፍራው አለ። ትክክል። ሚሽነሪውን መመርመር ያለበት አካል

ማን ነው፡ መንፈስ ቅዱስ ወይስ ሳይካትሪስት ነውን? አያችሁ፡ ሰውን ማመን፡ ውጤቱ ይህ ነው። አያችሁ፡ ሰው-ሰራሽ ንድፈ አሳቦች፣ ሰው-ሰራሽ አስተምህሮዎች። ወደዚያ ወደ ጴንጤቆስጤ ዘመን እስክንወርድ ድረስ ጠብቁኝ! እግዚአብሔር ያንን ነገር ልክ እንደ ዓለም ያቃጥለዋል። አዎን፡ ጌታዬ። በትክክል። ከላይ እስከ ታች ድረስ እሳት ሲነድ ታዩታላችሁ። ኧሃ፡ እም። በትክክል።

261 በከበረው ቀን ግን እርሱ ይመጣል። ይህን አስታውሱ፡ አዳምጡኝ፡ ሰባት የቤተ ክርስትያን ዘመናት አሉ። ልክ ነው? ሰባት የቤተ ክርስትያን ዘመናት። እና ሙሽራይቱን—ሙሽራውን ለማግኘት ሲወጡ ታስታውሳላችሁ፡ አንዳንዶቹ በመጀመሪያው ሰዓት አንቀላፉ (ልክ ነው?)፣ ሁለተኛው ሰዓት፡ (በእርግጥ፡ አንቀላፉ እንጂ—ሞቱ አይደለም።) ሦስተኛው ሰዓት፡ አራተኛው ሰዓት፡ አምስተኛው ሰዓት፡ ስድስተኛው ሰዓት፡ በሰባተኛውም ሰዓት ድምፅ መጣ፡ "እነሆ፣ ሙሽራው ይመጣል! እርሱን ለመገናኘት ውጡ!" ምን ሆነ? እነዚያ የተኙት ደናግል ሁሉ ተነሱ።

ጭጋግ በሌልው ጧት በጌታ የተኙ ሲነሱ፡ (ጭጋግ
የሌለው፡ የምሽት መብራቶች ይበራሉ።)
የትንሳኤ ብርሃን፡ ሲታደሉ፡
ቅዱሳን በሰማይ ቤታቸው ይሰበሰባሉ፡
ስሜ ሲጠራ፡ እገኛለሁ በዚያ።

ስሜ በተጠራ ጊዜ፡
ስሜ በተጠራ ጊዜ፡
ስሜ በተጠራ ጊዜ፡
ስሜ ሲጠራ እገኛለሁ በዚያ

ከጥዋት እስከ ማታ በርትተን ለጌታ እንስራ፡
ስለ ፍቅሩ እና ጥንቃቄው እናውራ፡
ሕይወት ከዓለም ሲያልፍ፡ ስራ ከምድር ሲፈጸም፡
ስሜ በተጠራ ጊዜ፡...

የእግዚአብሔር ልጆች የሆናችሁ ሁሉ አሁን እጆቻችሁን አንሡ፡-

ስሜ በተጠራ ጊዜ፡
ስሜ በተጠራ ጊዜ፡
ስሜ በተጠራ ጊዜ፡
ስሜ ሲጠራ፡ እገኛለሁ በዚያ። (ኦህ!)

ቅርብ ነው ጊዜው፡
ልንገናኝ በሰማይ አገር፡
ቅርብ ነው ጊዜው፡
ልንገናኝ በሰማይ አገር።

262 የቤተክርስቲያንን የድሮ መዝሙሮች ትወዳላችሁን? ኦህ!

ለባለ ጸጋው አባታችን፡
ምስጋናችንን እናቀርባለን፡
ለታላቅ የፍቅር ስጦታው፡
ስለማይለየንም ጸጋው።

ቅርብ ነው ጊዜው፡
ልንገናኝ በሰማይ አገር፡
ቅርብ ነው ጊዜው፡
ልንገናኝ በሰማይ አገር።

አሁን አጠገባችሁ ካለው ሰው ጋር፡ በዙርያችሁ ሁሉ ካለው ጋር እጅ ተጨባበጡ። በጣም ጥሩ።

… ቅርብ ነው ጊዜው፡

"ወንድሜ እንገናኛለን፡" ተባባሉ።

ልንገናኝ በሰማይ አገር፡
ቅርብ ነው ጊዜው፡
ልንገናኝ በሰማይ አገር።

በዚያ በድንቅ አገር ልንዘምር፡
የቅዱሳንን ግሩም መዝሙር…

አሁን ሁሉም ይዘምር።

መንፈሳችን ከቶ አያዝንም፡
ለዘለአለምም አንደክምም።

ሁላችሁም፡ እጆቻችሁን ወደ ላይ አድርጋችሁ፦

ቅርብ ነው ጊዜው፡
ኦህ፡ ልንገናኝ በሰማይ አገር፡
ቅርብ ነው ጊዜው፡
ልንገናኝ በሰማይ አገር።

263 አሁን አንገታችንን ደፍተን፡ እንዲህ እንላለን፦

ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እወድሃለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እምናለሁ፡ ኃጢአቴን ለማስወገድ እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ። በስራዎቼ አልታመንም፡ ምንም የለኝምና፡ እኔ ግን ዝቅ ብዬ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአምላኬ፡ በአዳኜ፡ እና በንጉሴ ስራ እታመናለሁ። እወደዋለሁ። ኣሜን።

264 ነገ ማታ በሰባት ሰአት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ የሰምርኔስን ቤተክርስትያን እንማራለን።

ቅርብ ነው…

አሁን አንገታችንን ደፍተን።

(ኦህ፡ ጊዜው!)
ልንገናኝ በሰማይ አገር፡ (ጊዜው!)
ቅርብ ነው ጊዜው፡
ልንገናኝ በሰማይ አገር።

አሁን በእርጋታ፡ ሁሉም በመልካም መንፈስ፡

ኡህ፡ ለባለ ጸጋው አባታችን፡
ምስጋናችንን እናቀርባለን፡
ለታላቅ የፍቅር ስጦታው...

**የኤፌሶን ቤተክርሰትያን ዘመን** AMH60-1205

(The Ephesian Church Age)

**የኢየሱሰ ክርሰቶሰ መገለጥ ተከታታይ ትምህርት**

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ሰኞ ማታ፡ ታሕሳሰ 5 ቀን፡ 1960፡ በዩ.ኤሰ.ኤ.፡ ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና ከሚገኘው ከብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

# የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈለጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org